በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የ2002/2003 ኦዲት ዓመት
የፌዴራል ዋና ኦዲተር ሪፖርት
አጠቃላይ ዘገባ

ጥራዝ 2

ግንቦት 2003
አዲስ አበባ

ክፍል አንድ

ክፍል ሁለት

ክፍል ሦስት

ማውጫ

ክፍል አንድ

1. መግቢያ 1

1.1 የመ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር 2

1.2 የሪፖርቱ ዓላማ 3

2. የ2002 የበጀት ዓምት ሂሣብ ኦዲት እና የ2003/03 ኦዲት ዓመት የሌሎች ሥራዎች ዕቅድና አፈጻጸም 4

2.1 ሥራ ላይ የዋለው በጀት 4

2.2 የመ/ቤቱ የሰው ኃይል ሁኔታ 5

2.3 የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ዕቅድና ክንውን 6

2.4 የሪፎርም ሥራን በተመለከተ 7

2.5 የመንግሥት ልማት ድርጅቶች፤ ፕሮጀክቶችና የእርዳታ ሂሳቦች ላይ የተከናወነው የፋይናንስ ኦዲት 9

2.6 የክዋኔ ኦዲትን በተመለከተ 9

2.7 አጠቃላይ የመንግሥት ገቢና ወጪ ሂሳብ ኦዲት 12

2.8 ሴክተር ዘለል የሆኑ ሥራዎችን በተመለከተ 12

ክፍል ሁለት

3. የ2002 በጀት ዓመት ሂሣብ የኦዲት ግኝቶችና የመፍትሄ ሐሣቦች 14

3.1 የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ ኦዲት 14

3.2 ውዝፍ የሰነድ /ተሰብሳቢ/ ሂሳብ 15

3.3 የገቢ ሂሳብ 17

3.4 የወጪ ሂሳብ 25

3.5 የተከፋይ ሂሣብ 31

3.6 የበጀት አጠቃቀም 31

3.7 የንብረት አያያዝና አጠባበቅ 32
3.8 የክትትልና የማሻሻያ እርምጃ አወሳሰድ 38
3.9 የ2002/3 የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ (PBS) ፕሮጄክት ተከታታይ ኦዲቶች አስተያየቶችና ጉልህ የሆኑ የኦዲት ግኝቶች ማጠቃለያ ሪፖርት 40
4. የክዋኔ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሣቦች 43
4.1 በውሃ ሀብት ልማት ሚኒስቴር የከሰም ተንዳሆ ግድብና መስኖ ልማት ኘሮጀክት የመስኖ ልማት (Irrigation) በተመለከተ 44
4.2 በትምህርት ሚኒስቴር የዩኒቨርስቲ አቅም ግንባታ ኘሮግራም የአሥራ ሦስት ዩኒቨርስቲዎች ግንባታን በተመለከተ 45
4.3 በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት በቡና ምርምር ኘሮጀክትን በተመለከተ 46
4.4 በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆች መከላከልን በተመለከተ 47
4.5 በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የአትሌቲክስ ስፖርትን በአገሪቱ በማስፋፋት ብቃት ያላቸውን አትሌቶች ለማፍራት የሚያደርገውን እንቅስቃሴ በተመለከተ 48
4.6 የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት አፈፃፀም እና ውጤታማነትን በተመለከተ 53
4.7 በግብርና ሚኒስቴር ፀረ-ተባይ መድኃኒቶች ግዥ፣ አጠባበቅ እና አወጋገድ የተከናወነ........ 57
4.8 በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን የቅርስ ጥናትና ጥበቃን በተመለከተ 63
4.9 በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ግዥ አፈጻጸም እና ንብረት አስተዳደርን በተመለከተ 69
4.10 የመንግሥት ተሽከርካሪዎች አጠባበቅ፣ አጠቃቀምና አወጋገድን በተመለከተ 76
4.11 ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተመደበው ሀብት ለታቀደለት ዓላማ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን በተመለከተ 85
4.12 የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን የግዥና ንብረት አስተዳደር የዕቃና አገልግሎት ግዥን በተመለከተ 90
4.13 በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የመንግሥት ኘሮጀክቶች አፈፃፀም በተመለከተ 92
4.14 በግብርና ሚኒስቴር የዳልጋ ከብል ሀብት ልማት በተመለከተ 95
5. ልዩ ኦዲት 97
6. ሌሎች ጉዳዮች 98
6.1 የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠትን በተመለከተ 98

6.2 የመ/ቤቱ የውስጥና የውጭ ግንኙነት እና ሥልጠና 99
7. ያጋጠሙ ችግሮች 103
8. የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች 103
9. ማጠቃለያ 103

ክፍል ሦስት

1. መግቢያ 105
2. የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የ2002 በጀት ዓመት የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት 106
2.1 የኮርፖሬሽኑ ዓላማ 106
2.2 የኦዲት ሪፖርት ዝግጅትና ስርጭት 106
2.3 የሥራ ዕቅድና ክንውን 107
2.4 የኮርፖሬሽኑ የሰው ኃይል ሁኔታ 108
2.5 የሰው ኃይል ሥልጠናን በተመለከተ 108
2.6 የኮርፖሬሽኑ የፋይናንስ እንቅስቃሴ 108
3. በ2002 በጀት ዓመት በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል የኦዲት ድርጅቶች ኦዲት ተደርጎ የቀረቡ ሪፖርቶች 109
4. የኦዲት ዋና ዋና ግኝቶች 110
4.1 አቋም ሊወሰድበት የማይቻል የኦዲት አስተያየት የቀረበባቸው 110
4.2 ስለድርጅቶች የሂሳብ አያያዝና ንብረት አጠባበቅ በተመለከተ 119
4.3 የችግሮቹ ምክንያቶችና መፍትሄያቸው 125
5. ማጠቃለያ 126

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በ2002/2003 የኦዲት ዓመት የተከናወኑ ኦዲቶች ሪፖርት እና እቅድ አፈጻጸም

/ከጥር 1/2002 - ታህሣስ 30-2003/

1. **መግቢያ**

የዋናው ኦዲተር መ/ቤት ቀደምትነት ካላቸው የመንግሥት መ/ቤቶች አንዱ ሲሆን፣ በአሁኑ ጊዜ ሀገሪቱ ከምትመራበት የፌዴራል ቅርጸ መንግሥትና ታዳጊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ጋር ለማጣጣም በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 55/1 መሠረት በአዋጅ ቁጥር 669/2002 የሚከተሉት ዓላማዎችን ይዞ እንደገና እንዲቋቋም ተደርጓል።

- የፌዴራሉን መንግሥት ዕቅዶችና በጀት በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን አስተማማኝ መረጃ ለማግኘት የሚረዳ የኦዲት ሥርዓትን ማጠናከር፣
- የፌዴራል መንግሥት ገንዘብና ንብረት በወጡት ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መሰብሰቡን፣ መጠበቁንና በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥና የደረሰበትን ውጤት ለምክር ቤቱ ሪፖርት ማቅረብ፣
- በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ላይ የፋይናንስና የክዋኔ ኦዲት፣ የአከባቢ ጥበቃ፣ የቁጥጥር ኦዲቶች፣ልዩ ኦዲቶች እና ሌሎች ኦዲቶች ማካሄድ፣
- አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የሂሣብ አያያዝና የኦዲት ሙያ እንዲያድግና እንዲጠናከር ጥረት ማድረግ፣
- በሂሣብ አያያዝና በኦዲት ሙያ ላይ ለተሰማሩ ለክልልና ለፌዴራል መንግሥት ሠራተኞችና ድርጅቶች ሙያዊ ዕገዛና ምክር መስጠት፣
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ሂሣብ የሚመረመርበትን የኦዲት ደረጃ /ስታንደርድ/ ማውጣትና ተግባራዊ መሆኑን መከታተል፣

ናቸው።

1.1 የመ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር

ከላይ የተገለጹትን ዓላማዎች ለማስፈጸም እንዲችል የተሰጡት ስልጣን፤ ተግባርና ኃላፊነቶች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችንና ድርጅቶችን ሂሣብ ኦዲት ያደርጋል፣ ወይም ያስደርጋል፤
- የፌዴራሉ መንግሥት ለክልል መንግሥታት የሚሰጠውን የበጀት ድጋፍና ልዩ ድጎማዎች ኦዲት ያደርጋል፣ ወይም ያስደርጋል፣
- ፌዴራል መንግሥት ከብር 1 ሚሊዮን /አንድ ሚሊዮን ብር/ በላይ የሚጠይቅ ሥራ የግል ሥራ ተቋራጮች እንዲሰሩ በውል የሰጠ እንደሆነ ይህንኑ መንግሥት ነክ የሆነ የግል ሥራ ተቋራጮች ሂሣብ ኦዲት ያደርጋል፤
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ያስገኙት ውጤት ሕጉን የተከተለ፣ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሠራር የተፈጸመ መሆኑን ተፈላጊውን ግብ መምታቱን ለማረጋገጥ እንደአስፈላጊነቱ የኘሮግራምና የአሠራር ቅልጥፍና ምርመራ ወይም ክዋኔ ኦዲት ያደርጋል፣ ወይም ያስደርጋል፣
- የመንግሥትንና የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል የግል ወይም የሕዝባዊ ድርጅቶችን ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፤
- ለፌዴራል መንግሥቱ መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች የተለገሱ እርዳታዎችን ወይም ስጦታዎችን ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፤
- ማናቸውም የፌዴራል መንግሥት መ/ቤት እና ድርጅት የውስጥ ኦዲተር ከመመደቡ በፊት ተመዳቢው አስፈላጊው የሙያ ብቃት ያለው መሆኑን አረጋግጦ ምስክርነት ይሰጣል፣
- ከሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች ጋር በመተባበር የሂሣብ አያያዝና የኦዲት ሙያ እንዲዳብር ጥረት ያደርጋል፡፡ የፌዴራሉ መንግሥት የኦዲትና የሂሣብ አያያዝ ሙያ ትክክለኛውን ፈር ይዞ እንዲዳብር አስፈላጊውን ቁጥጥር ያደርጋል፣

- ከክልል መንግሥታት የኦዲት መ/ቤቶች ጋር የኦዲት ተግባር የሚዳብርበትን ሁኔታ በተመለከተ የቅርብ የሥራ ግንኙነትና ትብብር ያደርጋል፣
- ለግል ኦዲተሮችና የሂሣብ አያያዝ ሥራ ለሚያከናውኑ የሂሣብ አዋቂዎች በሥራው መስክ ለመሰማራት የሚያስችላቸውን የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሠርዛል፣
- የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ስለመንግሥት በጀት ገቢና ወጪ፣ ሀብትና ዕዳ የሚያቀርበውን ዓመታዊ የሂሣብ ሪፖርት መርምሮ ሃሣብ ይሰጣል፣ ስለሁኔታውም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚያቀርበው ዘገባ አስተያየቱን ይገልጻል፣ የሚሉት ናቸው::

1.2 የሪፖርቱ ዓላማ

ሪፖርቱ መ/ቤቱን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 669/2002 በአንቀጽ 13/1 እና 2 መሠረት በ2002/2003 የኦዲት ዓመት በአከናወናቸው ኦዲቶች የተከሰቱ ዋና ዋና ግኝቶች፣ ምክር ቤቱ ለ2002 በጀት ዓመት የፈቀደው በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉንና ተፈላጊውን ውጤት ማስገኘቱን ለማረጋገጥና በሪፖርቱ በቀረበው መረጃ መሠረት ተገቢውን ውሳኔ ለመስጠት እንዲያስችለው፤ እንዲሁም መ/ቤታችን በአዋጅ የተጣለበትን ኃላፊነትና ተግባር በተሻለና በተጠናከረ ሁኔታ ለመወጣት እንዲችል እያካሄደ ያለውን የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም ፕሮግራም የ2002/2003 የኦዲት ዓመት እቅድ አፈፃፀም ለማመልከት ነው::

በሪፖርቱ ውስጥ የተሰጡ አስተያየቶችና የመደምደሚያ ሀሳቦች መሠረት ያደረጉት የተወሰኑ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን፣ የዓለም ባንክ እና ሌሎች ዕርዳታ ሰጪዎች የሚሰጡትን የመሰረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ ኦዲት ለማስደረግ መንግሥት በገባው ውል መሠረት በብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት የወረዳ ፋይናንስና የከተማ መስተዳድር ጽ/ቤቶችን ኦዲት በማድረግ፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 25/1984 የተቋቋሙ የመንግሥት ልማት ድርጅቶችን በተመለከተ በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽንና በሌሎች የሙያው ፈቃድ በተሰጣቸው የተፈቀደላቸው የኦዲት ድርጅቶች ኦዲት ተደርገው የተገኘውን ውጤት ነው::

የኦዲት ሪፖርቱ የኦዲቱ ሥራ ከተጠናቀቀ በኋላ ከመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ጋር በሚደረግ የመውጫ ስብሰባ ላይ የተነሱ ሃሳቦችን ያካተተ፣ ለእያንዳንዱ ኦዲት

ተደራጊና ተቆጣጣሪ መ/ቤት የኦዲት ሥራው እንዳለቀ እየተላከ፣ በአዋጅ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ መልስ የሰጡትን ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶችንና ድርጅቶችን መልስና አስተያየት ያገናዘበ ነው:: ኦዲቱ የተካሄደው በአብዛኛው የተለመደውን የአልፎ አልፎ ወይም የናሙና ኦዲት ስልት በመከተል እንዲሁም አንዳንዴም እንደ ኦዲቱ አስፈላጊነት እና ብዛት ሁኔታ እየታየ በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎች ፤ አጠቃላይ ተቀባይነት ያላቸውን የመንግሥት ሂሣብ አያያዝ ስርዓት እና ኦዲት ተደራጊ የመንግሥት መ/ቤቶችና የልማት ድርጅቶች ያቀረቧቸው የሂሣብ መዛግብት እና ሰነዶች ፤እንዲሁም የሂሣብ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች ናቸው::

መ/ቤታችን ባለው የሰው ኃይልና በተመደበለት በጀት በ2002/2003 የኦዲት ዓመት ያከናወናቸው ሥራዎች በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች ተለይተው ቀርበዋል:: የመጀመሪያው ክፍል የ2002/2003 የኦዲት ዓመት የመ/ቤቱ ዕቅድና አፈፃፀም፤ በሁለተኛው ክፍል የ2002 በጀት ዓመት ሂሳብ የኦዲት ግኝቶች፤ ልዩ ኦዲት፤ መ/ቤቱን ያጋጠሙ ችግሮችና የመፍትሄ ሃሣቦች እና ሦስተኛው ክፍል ደግሞ የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የሥራ እንቅስቃሴ እና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወኑ ኦዲቶችን የሚመለከት ይሆናል::

የመ/ቤቱን የኦዲት ሥራ በተመለከተ የቀረበው ሪፖርት የልዩ ልዩ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የፋይናንስና የሕጋዊነት ኦዲት፤በተለያዩ አካላት ጥያቄ መሰረት የተከናወኑ ልዩ ኦዲት፣ የአካባቢ እና የክዋኔ ኦዲትን እንዲሁም መንግስት ከአለም ባንክ እና ሌሎች ዕርዳታ ሰጪዎች ጋር ባደረገው ስምምነት መሠረት ለመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ (ፐብስ) ለክልል መንግሥታት የተሰጠውን ሂሳብ ተከታታይ ኦዲት ያጠቃልላል::

2. <u>የ2002 የበጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት እና የ2003/03 ኦዲት ዓመት የሌሎች ሥራዎች ዕቅድና አፈጻጸም</u>

2.1 <u>ሥራ ላይ የዋለው በጀት</u>

በ2002/2003 የኦዲት ዓመት የተፈጸሙ ሥራዎችን ለማከናወን የተመደበውና ሥራ ላይ የዋለውን በጀት በተመለከተ በመ/ቤቱ አዲስ አሠራር መሠረት

የመ/ቤቱ የኦዲት ሥራ ዓመት ከታህሣስ 1 - ጥር 30 ቢሆንም፤ የ2002 በጀት ዓመት ስራ ላይ የዋለው እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የሂሣብ መደብ	የወጪ ርዕስ	የተስተካከለ በጀት	ወጪ የተደረገ	ልዩነት	ሥራ ለይ የዋለ በመቶኛ
6100	ሰብዓዊ ለሆኑ አገልግሎቶች	6,809,600.00	6,857,757.54	(48,157.54)	101
6200	ለአላቂ እቃዎችግ አገልግሎቶች	5,370,900.00	5,223,320.63	14,779.37	98
6400	ለዓለም አቀፍ ድርጅቶች መዋጮ	35,000.00	27,998.88	7,001.12	80
	ድምር	12,215,500.00	12,109,077.05	106,422.95	99

2.2 የመ/ቤቱ የሰው ኃይል ሁኔታ

መ/ቤቱ በመሠረታዊ አሠራር ለውጥ (ቢ.ፒ.አር) ጥናት መሰረት አጥንቶ ባቀረበው መዋቅር የተያዘው የሰው ኃይል ለኦዲት ባለሙያ 381 እና ለድጋፍ ሰጪ 192 በድምሩ 573 ሲሆን፤ መዋቅሩ እስኪጸድቅ ጊዜያዊ ምደባ በማድረግ ስራውን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡

በኦዲት ዓመቱ 71 የኦዲት ባለሙያዎችና 8 የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች የተቀጠሩ ሲሆን፣ 10 ኦዲተሮችና 3 ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በጡረታ፣ 16 ኦዲተሮችና 11 ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በራሣቸው ፈቃድ የለቀቁ፣ 1 ኦዲተር በሞት፣ 1 ኦዲተር በህመም፤ 1 ኦዲተር በዝውውር እና 3 ኦዲተሮች በስንብት በድምሩ 46 ሠራተኞች መ/ቤቱን ለቀዋል፡፡ በመሆኑም በኦዲት ዓመቱ መጨረሻ በመ/ቤቱ የነበሩ የኦዲት ባለሙያዎች 150 ወንዶችና 85 ሴቶች በድምሩ 235፤ የድጋፍ ሰጪ 74 ወንዶችና 67 ሴቶች በድምሩ 141 ሠራተኞች ሲሆኑ፤ በአሁኑ ጊዜ የሚገኘው ሠራተኛ በአጠቃላይ 376 ሠራተኞችና ኃላፊዎች በሥራ ላይ የነበሩ ሲሆን፤ 197 የሥራ መደቦች በክፍትነት ተመዝግበው ይገኛሉ፡፡

2.3 የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ዕቅድና ክንውን

መ/ቤቱ በአዲሱ አደረጃጀት መሠረት የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን ኦዲት የሚያደርጉ በአራት ዳይሬክቶሬቶች እና የክልል መ/ቤቶች ኦዲት የሚያደርግ ደግሞ በአንድ ዳይሬክቶሬት የተዋቀረ ሲሆን፣ ከየካቲት 2002 ጀምሮ ወደ ሙሉ ትግበራ በመግባት ከየካቲት 1/2002 እስከ ታህሣስ 30/2003፣ 130 መ/ቤቶች የመደበኛ ኦዲት ለማድረግ በእቅድ በተያዛው መሠረት 129 መ/ቤቶች ፣እንዲሁም በተለያዩ አካላት ጥያቄ መሠረት 5 ልዩ ኦዲት ተከናውነው ሪፖርት ተደርጓል፡፡ በዕቅዱ መሠረት የተከናወነው ሥራ ልዩ ኦዲቱን ጨምሮ 103% ነው፡፡

የመሠታዊ የአገልግሎቶች ማስከበር ኘሮጀክት ተከታተይ ኦዲትን በተመለከተም ለወረዳዎች ከተሰጠው የድጋፍ ሂሣብ ውስጥ የ2002 በጀት ዓመት ሂሳብ በ256 ወረዳዎች ሂሣቡን ለማስተዳደር የተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ብቃት ያለውና አጥጋቢ መሆን ወይም አለመሆኑን ኦዲት ለማድረግ የታቀደ ሲሆን፤ በ2002/3 የኦዲት ዓመት የ276 ወረዳዎች ኦዲት ተከናውኖ ሪፖርታቸው ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ተልኳል፡፡

ይህም ክንውን ከበጀት ዓመቱ እቅድ ጋር ሲነጻፀር 108% መሆኑ ታውቋል፡፡

የኦዲቱ ሥራ የተከናወነው በአራት የፋይናንሽያል ኦዲት ዳይሬክቶሬቶችና 5 ቅርንጫፍ መ/ቤቶችን በሚመራ በአንድ የድጋፍና ድጎማ ኦዲት ዳይሬክቶሬት ነው::

የ2002 በጀት ዓመት ሂሣብን በተመለከተ መ/ቤታችን 129 በሚሆኑ የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች እና በ276 የወረዳና ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ጽ/ቤቶች ላይ ኦዲት በማድረግ የኦዲት ሪፖርት አዘጋጅቶ ለየመ/ቤቶቹ የላከ ሲሆን፣ ሪፖርቶቹም (ልዩ ኦዲትን ሳይጨምር) ከግኝታቸው ባሕርይ አንፃር ከ2001 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት አስተያየት ጋር በማነፃፀር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ተ ቁ.	መግለጫ	በፌዴራል መንግሥት ኦዲት የተደረጉ ሂሳቦች ብዛት		የመሠረታዊ አገልግሎቶች ክለላ ተከታታይ ኦዲት		አጠቃላይ	
		2001	2002	2001	2002	2001	2002
1	አጥጋቢ ሆነው በመኘታቸው ነቀፌታየሌለበት አስተያየት የተሰጠባቸው(Clean opinion)	5	49	53	4	58	53
2	ከጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶችበስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ ያለበት አስተያየት የተሰጠባቸው (Except for Opinion)	51	50	192	266	243	316
3	አቋም ለመውሰድ እንደማይቻልበመግለጽ አስተያየትየተሰጠባቸው (Disclaimer of Opinion)	5	8	0	3	5	11
4	የጎላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠባቸው (Adverse Opinion)	10	14	5	3	15	17
5	ሂሳባቸውን በወቅቱ ባለመዝጋታቸው አስተያየት ያልተሰጠባቸው	N/a	8	N/a	-	46	8
	ድምር	71	129	250	276	321	405

የኦዲት አስተያየት ተሰጥቷል፡፡

2.4 የሪፎርም ሥራን በተመለከተ

በመ/ቤታችን የተካሄደው የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናት ተጠናቅቆ፣ የኦዲቱ ከየካቲት 2002 ጀምሮ የሌሎች ደጋፊ የሥራ ሂደቶች ደግሞ ከግንቦት 2002 ጀምሮ ሙሉ በሙሉ ሥራ ላይ ከመዋሉም በላይ በመጀመሪያው የአንድ ዓመት የትግበራ ጊዜ የተገኘው ውጤት እጅግ አጥጋቢና ተስፋ ሰጪ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይልቁንም በጥናቱ እንደሚሚሉ ታሳቢ የተደረጉት ገብአቶች ቢሟሉ ኖሮ ውጤቱ አሁን ከተገኘው በእጅጉ ሊልቅ እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡

የተገኘውን ውጤት ይበልጥ ለማስፋት፣ ተቋማዊና ዘላቂ ለማድረግ ጥናቱን ተከትሎ አዲስ ተቋማዊ የአምስት ዓመት የስትራቴጂ ዕቅድ፣ የሰው ሀብት ልማት ስትራቴጂና የመረጃ ቴክኖሎጂ ስትራቴጂዎች ተቀርጸው ተግባራዊ በመደረግ ላይ ናቸው፡፡ የሰው ሀብት ልማት ስትራቴጂው ትኩረት የባለሙያዎቹን ክህሎትና እውቀት በመገንባት ከፍተኛ የሙያ ሥነ-ምግባርን የተላበሰና እሴት ያለው አገልገሎት ሊሰጥ የሚችል ፕሮፌሽናል ሠራተኛና ተቋም መፍጠር ነው፡፡ በሌላ በኩል የመረጃ ቴክኖሎጂው ስትራቴጂ ትኩረት የመረጃ አሰባሰብ፣ ትንተናና ልውውጥ እንደዚሁም የክምችት ሥርዓቱን ፈጣን፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በማድረግ የኦዲት ጥራት፣ ሽፋንና ወቅታዊነት ከፍ በማድረግ የኦዲት ወጪ በከፍተኛ ደረጃ እንዲቀንስ ማስቻል ነው፡፡

የሰው ሀብት ልማትና የመረጃ ቴክኖሎጂ ስትራቴጂዎቹ በአሁኑ ወቅት እየተተገበሩ ያሉት ከዕርዳታ ሰጪዎች በተገኙ ድጋፍ በመሆኑ የዕርዳታ ሰጪዎች ድጋፍ ሲቋረጥ አሁን የተገኘው ውጤት እንዳይስተጓጎል የዘለቄታው ጉዳይ በምክር ቤቱ ዘንድ ትኩረት አግኝቶ ተገቢው ሊመቻች ይገባል፡፡

በሌላ በኩል የሪፎርሙ አካል የሆነው የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናቱን ተከትሎ ለም/ቤቱ ቀርቦ የነበረው የመ/ቤታችን መዋቅርና የደመወዝ ስኬል በከረጅም ጊዜ በኋላ ቅርቡ ጸድቆ በመመለሱ የሠራተኛ ቋሚ ምደባ የተደረገ ቢሆንም የተፈቀደው ደመወዝ ከመ/ቤታችን ልዩ ባህርይና ባለሙያዎቹ በገበያ ላይ ካላቸው ከፍተኛ ተፈላጊነት አንፃር ችግሩን የሚያቃልል ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ ልዩ ትኩረት አግኝቶ እንደገና ሊታይ ይገባል፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናቱ ያስገኘው ውጤት እጅግ ከፍተኛ ከመሆኑም በላይ በሂደት ያሉ ግብአቶች ከተሟሉ አሁን ከተገኘውም ውጤት የበለጠ ሊገኝ እንደሚችል ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም የም/ቤቱ ድጋፍና ትብብር ይበልጥ ሊጠናከር ይገባል፡፡

2.5 <u>የመንግሥት ልማት ድርጅቶች፤ ፕሮጀክቶችና የእርዳታ ሂሳቦች ላይ የተከናወነው የፋይናንስ ኦዲት</u>

የመንግሥት የልማት ድርጅቶችንና በውጭ እርዳታ የሚከናወኑ ፕሮጀክቶችን ሂሣብ በሙሉ ኦዲት ለማድረግ የመ/ቤቱ አቅም ውሱን በመሆኑ ላለፉት ጊዜያት የነዚህ ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች ሂሣብ የኦዲት ሙያ ፈቃድ ከመ/ቤቱ በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶችና በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት እየተደረገ በተገኙት የኦዲት ግኝቶች ላይ ኦዲት ተደራጊው ድርጅት የሥራ አመራር ቦርድ፣ የፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስዱ መ/ቤቱ ክትትል ከማድረጉም በላይ የግል ኦዲት ድርጅቶችም ሆኑ የሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ተፈላጊውን የሙያ ሥነ ምግባር ሳያጓድሉ ሥራውን እንዲያከናውኑ በተወሰነ አቅም ቁጥጥርና ክትትል ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡

በዚህ መሠረት በ2002 በጀት በዓመት በመንግሥት ይዞታ ሥር የሚገኙ የልማት ድርጅቶች 99፣ ፕሮጀክቶች እና የዕርዳታ ሂሳቦች በግል ኦዲት ድርጅቶች 131 ኦዲቶች በድምሩ 230 የተለያዩ በጀት ዓመት ሂሣቦች የተከናወኑ ሲሆን፣ በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወኑትን ኦዲቶች በተመለከተ በተለይም አቋም መውሰድ ያልተቻለበትና የጎላ ችግር ያለባቸው በመሆኑ ተቀባይነት የሚይሳጣ የኦዲት አስተያየት የተሰጠባቸው የልማት ድርጅቶችን ዋና ዋና ግኝቶች በዚሁ ጥራዝ በክፍል 3 ቀርቧል፡፡

2.6 <u>የክዋኔ ኦዲትን በተመለከተ</u>

በመንግሥት የተቀረፁ ፕሮግራሞችና ፕሮጄክቶች የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋላቸውን እና የታለመላቸውን ዓላማና ግብ በብቃትና ስኬታማ በሆነ መንገድ መወጣታቸውን ለማረጋገጥ መ/ቤቱ የክዋኔ ኦዲት ያከናውናል፡፡ በዚህ መሠረት በ2002/3 በጀት ዓመት የቀድሞ የክዋኔ ኦዲት መምሪያ ከየካቲት 2002 ጀምሮ በአዲስ አደረጃጀት በሁለት ዳይሬክቶሬቶች የተደራጀ ሲሆን በሁለቱ ዳይሬክቶሬቶች 17 መ/ቤቶች የክዋኔ ኦዲት ለማከናወን እቅድ ተይዟል፡፡

በበጀት ዓመቱ ሊከናወኑ የታቀዱና የተከናወኑ የክዋኔ ኦዲት አካባቢዎች (አርእስቶች) የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ/ <u>ዕቅድ</u>

1. በእርሻ ምርምር ኢንስቲትዩት በቡና ምርምር ፕሮጀክት ላይ በ2000 በጀት ዓመት የተከናወነውን የክዋኔ ኦዲት ሥራ የሪፖርት ዝግጅት ማጠናቀቅ፣
2. በዩኒቨርስቲዎች ግንባታ ላይ የሚከናወነው የክዋኔ ኦዲት ማጠናቀቅ፣
3. በኢትዮጵያ አትሌትክስ ፌዴሬሽን ላይ ዝርዝር የክዋኔ ኦዲት ማጠናቀቀና ሪፖርት ማዘጋጀት
4. በእንስሳት ሀብት ልማት /በዳልጋ ከብት/ ላይ ዝርዝር የክዋኔ ኦዲት ሥራ ማከናወን እና ሪፖርት ማዘጋጀት፣
5. በገ/ኢ/ል/ሚ/ር የመንግሥት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ላይ የክዋኔ ኦዲት ማከናወን፣
6. በኤች አይ.ቪ. ኤድስ ፈንድ አጠቃቀም ላይ የክዋኔ ኦዲት ማከናወን፣
7. በኢትዮጵያ የቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን የዕቃ ግዥና ንብረት አስተደደር ላይ የክዋኔ ኦዲት ማከናወን፣
8. በቅርስ ጥናት እና ጥበቃ ባለሥልጣን የክዋኔ ኦዲት ማከናወን፤
9. በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክና ኃይል ኮርፖሬሽን የንብረት አስተደደርና የግዥ አፈፃፀም ላይ
10. በትምህርት ሚ/ር የከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት ላይ የክዋኔ ኦዲት ማከናወን፣
11. በግብርና ሚ/ር የፀረ ተባይ መድኃኒቶች ግዥ አጠባበቅ አጠቃቀምና አወጋገድ የክዋኔ ኦዲት ማከናወን፣
12. በመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር የመንግሥት ተሽከርካሪዎች አጠባበቅ አጠቃቀምና አወጋገድ ላይ የክዋኔ ኦዲት ማከናወን፣

13. የኢትዮጵያ የዱር እንስሣት ጥበቃና ባለስልጣን ላይ የክዋኔ ኦዲት ማከናወን፣
14. የአርብቶ አደር ማህበረሰብ ልማት ፕሬጀክት ላይ የክዋኔ ኦዲት መጀመር፣
15. የብዝሀ ህይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት ላይ የክዋኔ ኦዲት መጀመር፣
16. የመጠባበቂያ የምግብ ክምችት ላይ የክዋኔ ኦዲት መጀመር፣
17. የምግብና የመድኃኒት አስተዳደር ላይ የክዋኔ ኦዲት መጀመር፣

ናቸው።

በዕቅዱ መሠረትም 14 የክዋኔና አካባቢ ኦዲቶች እና አንድ ልዩ ኦዲት ሥራቸው ተጠናቆ ሪፖርቱ በም/ቤቱ ለሚመለከታቸው አካላት ተልኳል። /የተጠናቀቁት ኦዲቶች ግኝትና የማሻሻያ ሃሳቦች በዚሁ ጥራዝ ተራ ቁጥር 4 ላይ በዝርዝር ቀርቧል/

<u>ወደ 2003/2004 የኦዲት ዓመት የዞሩ</u>

- በግብርናና ገጠር ልማት ሚ/ር የዳልጋ ከብት ልማት በአርብቶ አደሩ አካባቢ የክዋኔ ኦዲት የዳሰሣ ሥራው ተጀምሯል፡፡
- በፓርክ ልማትና ቱሪዝምን አስመልክቶ መ/ቤታችን በገባው ዓለምዓቀፍ ግዴታ መሠረት እንዲሠራ በተሰጠው መመሪያ መሠረት የዳሰሣ ኦዲቱ ተጠናቋል፡፡
- በብዝሀ ህይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት ላይ በመከናወን ላይ የሚገኝ የክዋኔ ኦዲት የዳሰሣና የቅኝት ሥራው ተጠናቅቆ ዝርዝር ኦዲት በመሠራት ላይ ይገኛል፡፡
- በመድሀኒት አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን የመድኃኒት ጥራትና ደህንነት አግባባዊ አጠቃቀም ቁጥጥርና የአወጋገድ ሥርዓት ላይ የክዋኔ ኦዲት ተጀምሮ የዳሰሣና የቅኝት ሥራው ተጠናቆ ዝርዝር የኦዲት ሥራው በመከናወን ላይ ይገኛል፣

- በመጠባበቂያ የምግብ ክምችት ላይ የክዋኔ ኦዲት ተጀምሮ የዳሰሣና የቅኝት ሥራው ተጠናቅቆ ዝርዝር የኦዲት ሥራው በመከናወን ላይ ይገኛል፣

2.7 አጠቃላይ የመንግሥት ገቢና ወጪ ሂሳብ ኦዲት

በገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ የሚቀርብ የመንግስት አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሳብ የ2002 በጀት ዓመት ኦዲት የተጠናቀቀ ቢሆንም የመዉጫ ስብሰባ ባለመካሄዱ ውጤቱን በዚህ ሪፖርት ውስጥ ማካተት አልተቻለም፡፡

2.8 ሴክተር ዘለል የሆኑ ሥራዎችን በተመለከተ

በሥርዓተ ጾታ፤ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እና የአከባቢ ጥበቃ ዙሪያ ከተከናወኑት ተግባራትን በተመለከተ፤

- በረጅም ጊዜ ውስጥ ኤች.አይ.ቪ ኤድስን፣ የሥርዓተ ፆታ ጉዳይንና የአካባቢ ጉዳዮችን በመ/ቤታችን ውስጥ የሚከታተል መዋቅር እንደፈጠር ተደርጓል፡
- እንደአዲስ ከተቋቋሙት ኮሚቴዎች መካከል የሴቶች ጉዳይ በአጭር ጊዜ ከፍተኛ እንቅስቃሴ በማድረግ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ለሁለተኛ ጊዜ በመ/ቤታችን የማርች 8 ቀን እንዲከበርና በተጋባዥ የሴቶች ጉዳይ ባለሙያ በቀረበ የሥርዓተ ፆታ ትምህርት ሠራተኛው ግንዛቤ እንዲያገኝ አድርጓል፡፡
- የዓመቱ የአለም የኤድስ ቀን መሪ ቃል "የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ አገልግሎቶች ሁሉ አቀፍ ተደራሽነትና ሰብአዊ መብት (Universal Access & Human rights)" መልእክት በማስተላለፍ ሠራተኛው የዓመቱ የዓለም የኤድስ ቀን መሪ ቃልና የቀይ ሪቫን መልዕክት በደረት ላይ በማድረግ እርስ በእርስ እንዲወያዩ ተደርጓል፣
- መታቀብ፣ ካልሆነም አንድ ለአንድ መወሰን እንደሚቻል በመመርመር እራስን በማወቅ ጤንነታችንን ለመጠበቅ የሚያስችል ጽሑፍና ሌሎች

ብዛት ያላቸው ብሮሸሮችና በራሪ ወረቀቶች በላይብረሪ እንዲቀመጥና በመ/ቤቱ ህንፃዎች ላይ እንዲለጠፉ ተደርገዋል፣

- በሶሻልና ኢንቫሮሜንት ኮሚቴ አስተባባርነት የመ/ቤቱ ሰራተኛ በሙሉ የተሳተፈበት የ2002 የችግኝ ተከላ ፕሮግራም በኦሮሚያ ክልል ገላን ከተማ ተከናውኗል፡፡

- ሰራተኛው ስለማህበራዊ ግንኙነት ፣ስለስራውና ሌሎች ጉዳዮች በየተራ ከምስሉ ጋር በጽሁፍ መልዕክቱ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡

3. የ2002 በጀት ዓመት ሂሣብ የኦዲት ግኝቶችና የመፍትሄ ሃሣቦች

በዚህ ክፍል የሚነሱ አብዛኞቹ ግኝቶች ባለፉት ዓመታት ሪፖርታችን ደጋግመን ያቀረብናቸው ቢሆንም፣ በርካታ ጉድለት የታየባቸው መሥሪያ ቤቶችና የሚመለከታቸው አካላት አጥጋቢ እርምጃ ወስደው ባለመገኘታቸው አሁንም ደግመን ለማቅረብ አስፈላጊና ግዴታ ሆኖ በመገኘቱ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን::

መ/ቤታችን በ2002/2003 የኦዲት ዓመት በ129 የፌዴራል መ/ቤቶች መደበኛ የፋይናንስና ህጋዊ ኦዲት፣ በክልል መንግሥታት ደግሞ በ276 የወረዳና የከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ጽ/ቤቶች ላይ የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ (PBS) ተከታታይ ኦዲት እና 5 ልዩ ኦዲት ያከናወነ ሲሆን፣ በዚሁ መሠረት የታዩ ጉልህ የአሠራር ስህተቶችና ግድፈቶች ከመፍትሄ ሃሣቦች ጋር እንደሚከተለው ቀርበዋል::

3.1 የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ ኦዲት

3.1.1 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ትክክለኛነት አያያዝና አጠባበቅ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የውስጥ ኦዲተሮች ባደረጉት ምርመራ ብር 113,266.41 በ3 መ/ቤቶች የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ 6 ተመልክቷል/

በጉድለት ከታየው ገንዘብ ብር 309.09 መተካቱ የታወቀ ሲሆን፤ ቀሪውም ሂሳብ እንዲተካ ተገቢው ክትትል መደረግ እንዳለበት ለየመ/ቤቶቹ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.1.2 የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመት የታባቸው መ/ቤቶች

የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ባዘጋጀው የሂሣብ አያያዝ መመሪያ መሠረት የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የተደረገ መሆኑን፤ የቆጠራውም ውጤት ከመዝገብ (ሌጀር) እና በሂሣብ ማመዘኛው ሪፖርት ላይ ከተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ጋር የሚመሳከር መሆኑንና በባንክ ሂሳቦች ላይም ተገቢ ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ24 መ/ቤቶች የተለያዩ የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ጉድለቶች እንዳሉ ተረጋግጧል፡፡ /የመ/ቤቶቹ ዝርዝሩ በአባሪ 7 ተመልክቷል/

ከታዩት ዋና ዋና የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያየዝ ጉድለቶች፤

- የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ከመዝገብ (ሌጀር) ጋር የማይመሳከር መሆኑ፤
- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በቆጠራ ከተገኘው ጥሬ ገንዘብ በማነስ ሪፖርት የተደረገ መሆኑ፤
- የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የማያደርጉ /የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ አድርገናል ቢሉም ማስረጃ ያላቀረቡ/ መሆኑ፤
- በባንክ ሂሣብ ገቢ ለሆኑ ሂሣቦች፣ የገቢ ደረሰኝ አለማዘጋጀትና ያለመመዝገቡ፤
- የባንክ ሂሣብ ማስታረቂያ የማያዘጋጁ መሆኑ፤
- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በባንክ ሂሣብ መግለጫ ዜሮ ከወጪ ቀሪ እየታየ አላግባብ በባንክ ያለ ገንዘብ ተብሎ ሪፖርት የሚደረግ መሆኑ፤
- በውጭ ምንዛሪ ባንክ ያለ ገንዘብ /4102/ ተብሎ ሪፖርት የተደረገውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የባንክ ሂሣብ መግለጫ ያልቀረበለት መገኘቱ፤

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳቦች ላይም ተገቢ ቁጥጥር አለማድረግ ለገንዘብ ጉድለትና ምዝበራ የሚያገለጥ በመሆኑ፤ የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ በየወቅቱ ተቆጥሮ ከመዝገብ ጋር እንዲመሳከርና በሂሣብ ማመዛዘኛው ሪፖርት ላይ ከተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ጋር ሊመዛዘንና ትክክለኛነቱ ሊረጋገጥ እንደሚገባ እንዲሁም የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ በየወሩ እንዲዘጋጅ አሳስበናል፡፡

3.2 ውዝፍ የሰነድ /ተሰብሳቢ/ ሂሳብ

ስለመንግሥት ሂሳብ አያያዝ የወጣው ደንብ የደመወዝ ሰነድ ሂሳብ የወሩ ደመወዝ በሚከፈልበት ጊዜ የሥራ ማስኬጃ የሚመለከተው ደግሞ በተለይ የግዢ ሰነድ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ እንዲጠናቀቅ ያዛል፣ ይሁን እንጂ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ በ43 የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች

ብር 887,495,154.98 የሰነድ ሂሳብ በደንቡ መሠረት ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ 8 ተመልክቷል/

ውዝፍ ሠነድ /ተሰብሳቢ/ የተገኘ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት የትምህርት ሚኒስቴር ብር 340.92 ሚሊዮን፣ ግብርና ቴክኒክ ሙያና ትምህርት ስልጣና ብር 121.70 ሚሊዮን፣ የመከላከያ ሚ/ር ብር 117.06 ሚሊዮን፣ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ 114.31 ሚሊዮን፣ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ 78.63 ሚሊዮን፣ መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ብር 25.03 ሚሊዮን፣ ግብርናና ገጠር ልማት ሚ/ር የምግብ ዋስትና ዳይሬክቶሬት ብር 12.32 ሚሊዮን እና ማዕከላዊ ስታስቲክስ ብር 12.16 ሚሊዮን ይገኙበታል፡፡

ስለተሰብሳቢው ሂሳቦች ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ከሰጡት ምላሽ በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የአስተዳደርና ፋይናንስ መምሪያ በተሰብሳቢ ሂሣበ ከታየው ከውጭ ጉዞ አበል ጋር ተያይዞ ሰነድ ያለባቸው ከደመወዛቸው 1/3 እየተቀነሰ እንደሚገኝ፣ እንዲሁም ለሶሰት የሚ/ር መ/ቤቱ ድርጅቶች ከሠራዊቱ ደመወዝ ተመላሽ ብድር መሰጠቱ አግባብ እንዳልሆነና እንደሚያስተካክሉት፣ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሠነድ ያለባቸው እንዲያወራርዱ እና ይህን ካልፈጸሙ በሕግ ለመጠየቅ በዝግጅት ላይ መሆኑን፣ በሂሣብ ክፍል ለማወራረድ የቀረበ በርካታ ሠነዶች መቅረባቸውንና ይህም በአጭር ጊዜ ለመጨረስ በጽ/ቤቱ የፋይናንስ መምሪያ ካለው የሰው ኃይል በላይ መሆኑን በመጥቀስ ከሚመለከተው አካል ጋር በመመካከር በቂ ባለሙያ በዘመቻ መልክ እንደሚያሰማራ፣ የማዕከላዊ ስታስቲክስ ሂሳቡ የሚወራረድበትን መፍትሄ ለመፈለግ ከኤጀንሲው እና ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተውጣጣ ኮሚቴ ተቋቁሞ ባደረገው ጥረት የብር 659,314.92 ሰነድ የሚወራረድበት መንገድ በመመቻቸት ላይ መሆኑንና ሌሎችም የተለያዩ ምክንያቶች ለተላከላቸው የሥራ አመራር ሪፖርት በሰጡት መልስ ገልጸዋል፡፡

በመሆኑም ውዝፍ ሰነዱን በወቅቱ አለመወራረድ ለመንግሥት ገንዘብ መጥፋት በር የሚከፍት ስለሆነ በአስቸኳይ መወራረድ እንዳለበት፣ ለረጅም ዓመታት ሳይሰበሰቡ የተገኙት ሂሣቦች እንዲወራረዱ አስፈላጊው ክትትል እንዲደረግ፣

ሊሰበሰቡ በማይችሉት ላይ በመንግሥት መመሪያ መሠረት ከመዝገብ እንዲሰረዙ እንዲደረግ በላክናቸው ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡

3.3 የገቢ ሂሳብ

3.3.1 በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብ በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት ሳይሰበሰብ የተገኘ የገቢ ሂሳብ

የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብን በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት የመንግሥትን ገቢ የሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

በ10 መ/ቤቶች ውስጥ ብር 4,381,208.42 በተለያዩ ምክንያቶች ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ 11 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ ሳይሰበሰብ የቀረበት ምክንያት ሲጣራ ዕቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር (Harmonized System code) እና (Custom procedure code) ባለመመደባቸው ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ፣ የመነሻ ዋጋ ለተወሰነላቸው ዕቃዎች በመነሻ ዋጋው መሰረት ያልተስተናገዱ ድርጅቶች መገኘታቸው፣ በማነፃፀሪያ ዋጋ መሰረት ቀረጥና ታክስ ባለመሰራቱ፣ እና መ/ቤቶች ከሚፈጽሙት ግዢ ላይ ቀንሰው ማስቀረት የሚገባቸው ግብር (Withholding tax)፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ሥራ ግብር ሳይቀንሱ መቅረታቸው የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም ስለሁኔታው ትኩረት ተሰጥቶት የመንግሥት ህግና ደንብ ተከብሮ እንዲሠራ፣ ያልተሰበሰበውም ገቢ እንዲሰበሰብ አሳስበናል፡፡

3.3.2 በወቅቱ ገቢ ያልደተረገ ውዝፍ ሂሳብ

ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በወጣው ህግና ደንብ መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደገረግ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ስር ባሉ ሦስት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከወለድ እና ቅጣት መሰብሰብ የሚገባው ብር 212,683,707.39፤ በጉምሩክ የአዳማ ቅ/ጽ/ቤት ብር 67,862,205.83 የአዲስ አበባ ኤርፖርት

ቅ/ጽ/ቤት ሊሰበሰብ የሚገባው ብር 4,823,683.36 ከ 6 ወር በላይ የቆየ ውዝፍ ሂሣብ የተገኘ ሲሆን፣ በአዲስ አበባ የወጪ እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት የተወሰነላቸውን የጊዜ ገደብ ጠብቀው ባለማጓጓዛቸው ቅጣት ከተወሰነባቸው ሾፌሮች እና ወኪሎች ያልተሰበሰበ ብር 15,000.00 በድምሩ ብር 285,384,595.58 በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ገቢ ተገኝቷል፡፡ /ለዝርዝሩ አባሪ 10 ይመልከቱ/

በመሆኑም ስለሁኔታው ትኩረት ተሰጥቶት የመንግሥት ገንዘብ በወቅቱ እንዲሰበሰብ አሳስበናል፡፡

3.3.3 ማስረጃ ባለመሟላቱ ምክንያት የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ

የተሰበሰበውን ገቢ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ስር ባሉ ሶሰት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና በሌሎች ሶስት መ/ቤቶች በድምሩ ብር 58,642,597.86 የገቢ ደረሰኝ እና የግብር ማሣወቂያ በፋይሉ ውስጥ ተያይዞ ባለመገኘቱ ምክንያት፣ ከማን እንደተሰበሰበ ሳይገለጽ በኮድ በመሰብሰቡ የተሰበሰበው ገቢ መሰብሰብ በሚገባው ልክ መሆኑን ለማረጋገጥ ባለመቻሉ የተሰበሰበውን ገቢ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡ /የመ/ቤቶቹ ዝርዝር በአባሪ 9 ተመልክቷል፡፡/

ስለሆነም ማስረጃ ሳይሟላ በገቢ መመዝገቡ ተገቢ ስላልሆነ፣ የገቢ ማስረጃዎች በትክክል ተደራጅተው እንዲያዙ ተገቢው ማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.3.4 የገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት ሂሳብ

በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ በተደነገገው መሠረት ማንኛውም የመንግሥት ገቢ በሕጋዊ ደረሰኝ መሰብሰብና መመዝገብ ያለበት ቢሆንም በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኤጀንሲ የተሰበሰበው ብር 10,000.00 ተገቢው የገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥለት በገቢ ተይዞ ተገኝቷል፡፡

ስለዚህ የገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት ሂሳብ የገቢ ደረሰኝ ተቆርጦለት እንዲያዝ በሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.3.5 በገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ ገቢ

በበጀት ዓመቱ የተሰበሰበው ገቢ በትክክል ተመዝግቦና በሂሣብ ሪፖርታቸው ተካቶ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ 9 መ/ቤቶች ባቀረቡት ዓመታዊ የገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ብር 543.49 ሚሊዮን (በተለይ ከሰበሰቡት የውስጥ ገቢ) ሳይካተት ተገኝቷል፡፡ /የመ/ቤቶቹ ዝርዝር በአባሪ 12 ተመልክቷል፡፡/

በተጨማሪም በሚዛን ቴፒ፣ በሠመራ፣ ድሬዳዋ፣ በመደወላቡና በወሎ ዩኒቨርስቲዎች ምዝገባ ባለመከናወኑ የገንዘቡ መጠኑ የማይታወቅ የውስጥ ገቢ ሂሳብ ሪፖርት አለመደረጉ ተውቋል፡፡ ከንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች የፌደራል ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቶች በስማቸው አንጻር የተገለጸውን ገንዘብ ድሬዳዋ ከሚገኙት የፌደራል ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቶች የሰበሰቡት ገቢ አዲስ አበባ በሚገኙት ሁለት ፍ/ቤቶች የወጪ በጀት የሚላከላቸው ሲሆን፣ የወጪ ሂሣብ ሪፖርት እየተደረገ ገቢው ግን ለድሬዳዋ ገቢዎች ቢሮ እንደሚገባ መታወቁን በመግለጽ አሠራሩ እንዲስተካከል፣ እና በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የሚዘጋጁት ሂሣብ መግለጫዎች ከተለያዩ ምንጮች የተገኙትን ገቢዎች አካቶ መያዝ እንዳለበት የሰጠነው አስተያየት ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የተቀበሉት መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

3.3.6 በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች የታዩ ልዩ ልዩ የገቢ አሰባሰብና የአሠራር ድክመቶች

የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች በአዋጅ በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰባቸውንና ተገቢ የሆኑ የቁጥጥር ስርዓት የዘረጉ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የታዩት ዋና ዋና ድክመቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

3.3.7 የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ጉምሩክን በተመለከተ

- በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት በድምሩ ብር 5,094,327.00 በወቅቱ ባንክ ገቢ ሳይሆን ከ 1-11 ቀን በገንዘብ ያዥ እጅ የቆየ መሆኑ፤

- በሞጆ መቅረጫ ጣቢያ ከግል ባንኮች በቼክ በየእለቱ የሚሰበሰበዉ ገቢ ሳይመነዘር እስከ 15 ቀን የሚቆይ መሆኑ፤
- በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት በተለያዩ ደረሰኞች የተሰበሰበ ቀረጥ ሳይመዘገብ ማስረጃው በገንዘብ ያዥ እጅ እስከ 15 ቀን የሚዘገይ መሆኑ፤
- በአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት በዲክራሲዮን ቁጥር C-26028/2009 ለገባው እቃ የእያንዳንዱ ዕቃ ዋጋ ሳይታወቅ ጥቅል ዋጋውን (CIF Value) በመውሰድ በአንድ የታሪፍ ቁጥር ላይ በመመደብ በ20% የጉምሩክ ቀረጥ ምጣኔ ገቢ የተሰበሰበ ሲሆን ከነዚህ ዕቃዎች ውስጥ በ30% እና በ35% የቀረጥ ምጣኔ መሰረት ሊስተናገዱ የሚገባቸው እቃዎችም መገኘታቸው፤
- በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት በዲክራሲዮን ቁጥር C-7581,29/10/2009 እና C-24159,15/07/2009 በዋጋ ሠነድ ላይ የእያንዳንዱ ዕቃ ዝርዝር እና የእያንዳንዱም ዕቃ ዋጋ ሳይገለጽ በዝርዝር የዕቃውን ዋጋ የሚያሳይ የዋጋ ሰነድ እንደቀረበ ተደርጎ ቀረጥና ታክስ ተሰብስቦ መገኘቱ፤
- በአዲስ አበባ ኤርፖርትና በአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት ብዙ ዕቃዎችን የያዙ የዋጋ ሰነዶች ላይ እያንዳንዱ ዕቃ የተመደበበት ታሪፍ ቁጥር በተሟላ ሁኔታ በዕቃዎች መረጃ መስጫ ዲክላራሲዮን ላይ ሳይሞላ ቀረጥና ታክስ ተሰብስቦ በመገኘቱ እያንዳንዱ እቃ የተመደበበት የታሪፍ ቁጥር ትክክል መሆኑን ማረጋገጥ አለመቻሉ፡
- በአዲስ አበባ ኤርፖርትና በአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት የእቃውን ዋጋና ታሪፍ ቁጥር ለመወሰን አሻሚ የሆኑ አንዳንድ የዋጋ ሰነዶች በፍተሻም ይሁን በመረጃ መስጫ

ዲክላራሲዮን ላይ ስለእቃው ሁኔታ ተጨማሪ መረጃ ሳይቀርብ ዲክላራሲዮኑ ተቀባይነት ማግኘቱ፡፡

<u>በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት</u>

- ለማስጫኛ ከተከፈለዉ ወጪ ውስጥ 1/3ኛውን ብቻ በመውሰድ በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ (CIF Value) ውስጥ የሚካተት መሆኑ፣
- የማስጫኛ እና ኢንሹራንስ ደረሰኝ በአስመጪዎች በማይቀርብበት ጊዜ ለማስጫኛ ዋጋ የFOB ዋጋውን 10%፣ ለኢንሹራንስ ደግሞ የFOB ዋጋና የማስጫኛውን ድምር 5% በመውሰድ ቀረጥና ታክሱ የሚሰላ መሆኑ አሰራሩም ለረዢም ጊዜ የቆየ ከመሆኑም በላይ በመመሪያ ያልተደገፈ እና በልምድ ሲሰራበት የቆየ መሆኑን፣
- በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት በኩል ድሬ ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግል ድርጅት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አዲስ ከተማ ቅርንጫፍ በተሰጠ ተመሳሳይ የባንክ ፈቃድ ቁጥር ሁለት ጊዜ እቃ ወደ ውጭ አገር ልኮ መገኘቱ፡
- በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት እና በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት በ18 ዲክላራሲዮኖች ወደ አገር ውስጥ ከገቡ እቃዎች፣ የእቃው ዋጋ በባንክ ከተፈቀደው የውጭ ምንዛሪ በ USD 3,723,716.75 እና USD 610,907.27 እንደቅደም ተከተሉ ብልጫ ሚያሳይ መሆኑ፣
- በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት በኩል በE-2912, 30/01/2010 እና በ E-3475, 02/04/2010 የተመዘገቡት ዕቃዎች አሴስ ሳይደረጉ ወደ ውጭ የተላኩ መሆኑ፣ እንዲሁም ተመዝግበው ቀጣዩን የጉምሩክ ስነስርአት ሳይፈጽሙ ለረዢም ጊዜ ሳይሰረዙ የቆዩ 4 የወጪ ዲክላራሲዮኖች መገኘታቸው፣
- በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት 40 ዲክላራሲዮኖች የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ሳይፈጸምባቸው ከተከፈቱ ከአመት በላይ የሆናቸው ዲክላራሲዮኖች በትራንዚት ቡድን ክፍል ተከማችተው መገኘታቸው፣
- በአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት በኩል በቀረጥና ታክስ አሰባሰብ ላይ ግልጽ የሆነ ጥፋት በፈጸሙ አንዳንድ የጉምሩክ

አስተላላፊዎች ላይ በአፈፃፀም መመሪያ መሠረት አስፈላጊው አስተዳደራዊ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣

- በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት፣ በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት፣ በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት በጊዜያዊነት ወደ ሀገር ውስጥ ለገባ ዕቃ በዋስትና የተያዘ ሂሣብ በሰነድ አለመሟላት ምክንያት፤ እንዲሁም በአዲስ አበባ ወጪና ሌሎች እቃዎች ማ/ቅ/ጽ/ቤት በኩል በዋስትና የተያዘ ሂሳብ፣ ቦንድ ጊዜ ያለፈበትና በባለስልጣኑ ፈቃድ ጊዜያቸው ያልተራዘመላቸው፤ በድምሩ ብር 302,972,929.66 በመመሪያው መሰረት የዋስትና ጊዜ ገደቡ ቢያልፍም ወደ ቀጥታ ገቢ ያልተላለፈ መሆኑ፣
- የቫውቸር ተጠቃሚዎች ወደ አገር ውስጥ ያስገቡት የጥሬ እቃም ሆነ ወደ ውጭ የተላከውን ምርት መከታተያ ስርአት ቢኖርም ያልተተገበረ በመሆኑ በመመሪያው መሰረት ስለመፈጸሙ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ ከጠቅላላው የቫውቸር ስርዓት ተጠቃሚዎች ውስጥ 27 ድርጅቶች የተፈቀደላቸው የቫውቸር መጠን በድምሩ ብር 68,769,394.97 ቀረጥና ታክስ አለማወራረዳቸውና ቫውቸራቸውንም ያላሳደሱ መሆኑ፣
- በአዲስ አበባ ወጪና ሌሎች እቃዎች ማ/ቅ/ጽ/ቤት በኩል በዲክላራሲዮን ቁጥር E-4051/2010 አባሪ ሰነዶች ውስጥ በኖቫ ስታር ጋርመንት ፋብሪካ ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ ወደውጭ የተላኩ ተመሳሳይ ዕቃዎች በአንድ ኮሜርሺያል ኢንቮይስ ላይ ሁለት አይነት ዋጋ ተጠቅሶ ተገኝቷል፡፡ ከተላኩት 1988 ኪሎ ግራም ተመሳሳይ እቃዎች ውስጥ፡-
  - ክብደቱ 1896 ኪሎ ግራም ለሆነ እቃ የአንዱ ዋጋ በዶላር 0.85፣
  - ቀሪው 92 ኪሎ ግራም ደግሞ የአንዱ ዋጋ በዶላር 4.285፣

  በመሰላቱ በአነስተኛ የነጠላ ዋጋ የተስተናገዱት እቃዎች አገራችን ልታገኝ የምትችለውን የውጭ ምንዛሪ ያሳነሰ መሆኑ፣

የአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት

- የገቢ አሰባሰብና የዋስትና ሂሣቦች አያያዝ ቡድን ተሰብሳቢ ሂሳብን በተመለከተ ለክትትል እንዲያመች በየ15 ቀኑ ለደንበኞች አገልግሎት የሥራ ሂደት ሪፖርት ማድረግ የሚጠበቅበት ቢሆንም የደንበኞች አገልግሎት ሪፖርት የማይደርሰው መሆኑ፣
- የገቢ አሰባሰብና የዋስትና ሂሣቦች አያያዝ ቡድን ተሰብሳቢ (ቀሪ) ሂሣብን አስመልክቶ የተሟላ እና ወቅታዊ መረጃ የማይዝ በመሆኑ፣ የውዝፍ አሰባሰብ የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት እና የተዘረጋው የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት አስተማማኝ መረጃን ሊሰጥ የማይችል መሆኑ፣

የአዲስ አበባ ንግድ ዕቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት

- ተሰብሳቢ ሂሳብ በሂሳብ ክፍሉ ተቀጽላ መዝገብ ተከፍቶ በየድርጅቶቹ ስም ተመዝግቦ ያልተያዘ በመሆኑ የቅ/ጽ/ቤቱ ተሰብሳቢ ሒሳብ ምን ያህል እንደሆነ የማይታወቅ መሆኑ እና ለመክፈል ፈቃደኛ ያልሆኑ ድርጅቶች ተለይተው ህጋዊ እርምጃ ለሚወስደው የስራ ክፍል ያልተላለፈ መሆኑ፣

የአገር ውስጥ ገቢን በተመለከተ

- በሶስት ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 1,592,966.44 የተሰበሰበው ገቢ በወቅቱ ለትሬዠሪ ዝውውር አለመደረጉ፣
- በባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት ዘግይቶ በተሰበሰበ የደመወዝ ገቢ ግብር እና የቅድመ ታክስ በድምሩ ብር 3,033,014.15 በወቅቱ ገቢ ባላደረጉ ግብር ከፋዮች ላይ ቅጣትም ሆነ ወለድ ያልተጣለባቸው መሆኑ፡
- በባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት ግብር ከፋዮች በግብዓት ላይ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተቀናሽ ማስታወቂያ ሳያቀርቡ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ ላይ ተቀናሽ የተደረገላቸው ግብር ከፋዮች መገኘታቸው፡

- በምሥራቅ አዲስ አባባ ቅ/ጽ/ቤት 12 ግብር ከፋች የኤክሣይዝ ታክስ፣ በባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት 4 ግብር ከፋዮች የተጨማሪ እሴት ታክስ ግብር ከፋዮች በአዋጁ መሰረት ሪፖርት ያላደረጉ መሆናቸው፡
- በምእራብ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት ሁለት ድርጅቶች ካለፈው ዓመት የዞረውን የክምችት ሂሳብ ከወጪ ቀሪ በትርፍና ኪሳራ መግለጫ ላይ አስበልጠው በመያዛቸው ምክንያት ታክስ የሚሰላበት ገቢ በብር 581,753.86 ዝቅ ያለ በመሆኑ ሊሰበሰብ የሚገባው የንግድ ትርፍ ገቢ በዚሁ መሰረት ዝቅ የሚል መሆኑን፤

የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት

- በፍሊራንስ ዜና አንባቢነትና ዘጋቢነት በኮንትራት ቅጥር ለሚያሰራቸው ሠራተኞች የሚቀንሰው የሥራ ግብር በኮንትራት ውሉ መሰረት ድርጅቱ በሚከፍላቸው ደመወዝ ላይ ብቻ የተመሰረተ በመሆኑ በአዋጁ መሰረት ሊሰበሰብ የሚገባው ግብር ሳይሰበሰብ ሊቀር እንደሚችል፣
- በመሀል ከተማ ቢሮ በኩል በየወሩ ተጠናቅሮ የሚቀርበው የክልሎች፣ የአዲስ አበባና አካባቢው የቴሌቪዥን ፈቃድ ክፍያ የሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛነቱ እየተረጋገጠ ድርጅቱ በሚያቀርበው ወርሀዊ የሂሳብ ሪፖርት ውስጥ እንዲካተት የማይደረግ መሆኑ፤

የጎንደር የሕክምናና ጤና ሣይንስ ኮሌጅ

- ከተለያዩ ምንጮች የሚሰበስበውን የውስጥ ገቢ፣ የልዩ ፋርማሲ የመድኃኒት ሽያጭ ገቢና የፕሮጄክት ፈንድ ለይቶ መዝግቦ አልያዘም፡፡ በተጨማሪም በፋይናንስ አስተዳደር አዋጁ መሠረት ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፈቃድ ሣያገኝ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝና ሌሎች ቫውቸሮችን አሣትሞ በመጠቀም ላይ መሆኑ፡

<u>የጎንደር ዩኒቨርስቲ</u>

- የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴርን ሣያሣውቅና ፈቃድ ሣያገኝ ብዛቱ 5000 ጥራዝ የውስጥ ገቢ የገንዘብ መቀበያ ደረሠኝ አሣትሞ እየተጠቀመበት መሆኑ፣

<u>በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ</u>

- የባንክ ሂሣብ ውስጥ ገቢ ተደርጎ የተገኘው ብር 789,611.92 የገቢውን ዝርዝር ሁኔታ የሚያስረዳ ማስረጃ ማግኘት አለመቻሉ፤

ታውቋል፡፡

ስለሆነም ለወደፊቱ ደንብና መመሪያ ተጠብቆ እንዲሠራ እንዲሁም ከላይ የተጠቀሱት የገቢ አሰባሰብ አፈፃፀም እና የአሠራር ድክመቶች እንዲታረሙ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.4 <u>የወጪ ሂሳብ</u>

3.4.1 <u>የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሣብ</u>

በወጪ የተመዘገቡ ክፍያዎች ህጋዊ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ለሥልጠና ተብሎ ለወሎ ዩኒቨርስቲ የተላለፈው ተጨማሪ በጀት ብር 2,365,730.00 እና በምግብ ዋስትና ዳይሬክቶሬት በቼክ ወጪ ለሆነ ብር 4,726.00 ማስረጃ ሣይኖረው በቀጥታ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሣብ በቂ ማስረጃ እንድቀርብለት አለበለዚያ ገንዘቡ ለመንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም ማንኛውም ወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡን በማረጋገጥ እንዲመዘገብ አሳስበናል፡፡

3.4.2 <u>የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ክፍያ</u>

በወጪ ለተመዘገቡ ሂሳቦች የተሟላ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ16 መ/ቤቶች የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 1,456,245,196.24 በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩም በአባሪ 13 ተመልክቷል፡፡/

ተሚልተው ካልቀረቡት ማስረጃዎች መካከል ፣ከዕቃ አቅራቢው የተሰጠ ተገቢ ማስረጃ ሳይቀርብ፤ በቀረበው የክፍያ ጥያቄ መሠረት የተፈፀመ እንጂ የተከናወነውን ሥራ በሚየሣይ ዝርዝር መረጃ ሳይደገፍ፤ በባንክ በኩል ገንዘቡ ተልኮ ሥራ ላይ መዋሉን የሚገልጽ የወጪ ማስረጃ ሣይቀርብ በወጪ ተመዝገቦ የተገኘ ሲሆን፤የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር መረጃ አገልግሎት ወጪ የተደረገ መሆኑን የውጭ መልዕክተኞች ለተጠቀሱት ሚሲዮኖች ያለበቂ ማስረጃ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑን፤እንድሁም የዱቤ ሽያጭ ደረሠኝን እንደወጪ ሂሣብ ማስረጃ በመያዝ በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች ጎላ ያሉት ናቸው::

ስለሆነም አሠራሩ የመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ደንብ ያልተከተለ በመሆኑ፣ ለወደፊቱ ጥንቃቄ እንዲደረግና ያልተሚላውም ማስረጃ እንዲሚላ በላክነው ሪፖርት ያሳሰብን ሲሆን፣ አብዛኞቹ መ/ቤቶች የቀረበውን አስተያየት መቀበላቸውና አስፈላጊውን ማስተካከያ እንደሚያደርጉ በሰጡት ምላሽ ገልጻዋል::

3.4.3 <u>ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች</u>

ክፍያዎች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብና መመሪያዎች መሠረት የተፈጸሙ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በ22 መ/ቤቶች ብር 584,611,188.04 ከደንብና መመሪያ ውጭ ተከፍሎ ተገኝቷል:: /ዝርዝሩም በአባሪ 15 ተመልክቷል/

ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ፤ የትምህርት ሚኒስቴር አሥራ ሦስት ዩኒቨርስቲዎችን ለማስገንባት በተገባው ውልና ከ1998-2002 በጀት ዓመት ድረስ በተፈፀመው ክፍያ መካከል ብር 441,155,353.46 ከውሉ በላይ ክፍያ የተፈጸመ፤ በውሃና ኢናርጂ ሚ/ር የተሠራው ሥራ መጠን በምስክር ወረቀት ሳይረጋገጥ 112.5 ሚሊዮን እንዲሁም ከክፍያ መቀነስ የነበረበት ብር 20.2 ሚሊዮን በድምሩ ብር 132.7 ሚሊዮን ከደንቡ ውጪ የተከፈለ እና ሌሎችም ከገቡት ውል ውጭ ክፍያ በመፈጸም፤

ሂሳቡን ሁለት ጊዜ በመያዝ ወጪ የተደረገ፤ በሂሳብ ስሌትና በስምምነቱ ከተቀመጠው ዋጋ በማስበለጥ የተከፈለ ይገኝበታል፡፡

በመሆኑም አፈጻጸሙ ከመንግሥት ደንብና መመሪያ ውጪ በመሆኑ ማንኛውም ክፍያ የመንግሥት መመሪያ የተከተለ እንዲሆንና ያለአግባብ የተፈከለውም ከሚመለከታቸው ተመላሽ እንዲሆን አሳስበናል።

3.4.4 <u>ደንብና መመሪያ ያልተከተሉ ግዢዎች</u>

የዕቃና አገልግሎት ግዢ በመንግሥት ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ33 መ/ቤቶች ብር 83,383,007.31 የመንግሥትን የግዢ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዢ ተፈጽሞ ተገኝቷል። /ዝርዝሩም በአባሪ 14 ተመልክቷል፡፡/

ከደንብና መመሪያዎች ውጭ ግዥ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል ትምህርት ሚ/ር ብር 27.80 ሚሊዮን (ለአምቦ ዩኒቨርስቲ ማስፋፊያ ግንባታና የኮምፒዩተር ግዥ)፤ ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ ብር 11.94 ሚሊዮን (ለሠራተኞችና መምህራን መኖሪያ ሕንፃ ግንባታ)፤ የወሎ ዩኒቨርስቲ ብር 8.92 ሚሊዮን (ለተማሪዎች ምግብ አገልግሎት)፤ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ብር 5.51 ሚሊዮን እና የኢትዮጵያ ካርታ ስራ ድርጅት ብር 5.6 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

መ/ቤቶቹ ካልተከተሏቸው የግዥ ደንብና መመሪያዎች ውስጥ የጨረታ ማስታወቂያ በማውጣት ሊፈጸሙ የሚገባቸውን ግዥዎች ያለጨረታ ማስታወቂያ መግዛት፣ በዋጋ ማወዳደሪያ /ፕሮፎርማ/ አማካኝነት መፈጸም ያለበትን ግዥ የዋጋ ውድድር ሳይደረግ ግዥ መፈጸም የሚሉት ይገኙበታል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ መንግሥት ባወጣው የግዢ ደንብና መመሪያ መሠረት መፈጸም እንደሚገባ ያሳሰብን ሲሆን፤መ/ቤቶቹም አስተያየቱን ተቀብለውታል፡፡

3.4.5 <u>በባለሥልጣን ሳይፈቀድ የተፈጸሙ ክፍያዎች</u>

ክፍያዎች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሠረት በተገቢው ባለሥልጣን እየተፈቀዱ መከናወናቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ4 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 2,024,136.74 በተገቢው ባለሥልጣን ሳይታዘዝ ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከዚህም ዋነኛው የአዲስ አበባ ንግድ ሥራ ኮሌጅ ለተፈፀመው ክፍያ ብር 1,682,850.00 በኃላፊ ሣይፀድቅ በወጪ የተመዘገበ ሲሆን በወቅቱ የኃላፊነት ዝውውር በመደረጉ ሳይፈረም መቅረቱን ኮሌጁ በሰጠው ምላሽ ገልጿል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ 18 ተመልክቷል፡፡/

ስለሆነም ማንኛውም ወጪ በሚመለከተው ባለሥልጣን እየተፈቀደ መከፈል እንዳለበት አሳስበናል፡፡

3.4.6 <u>የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሣብ</u>

በበጀት ዓመቱ መ/ቤቶች የፈጸሙት ክፍያ ትክክለኛነት ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ9 መ/ቤቶች በተለያየ ምክንያት የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሣብ ብር 1,940,811,592.24 ተገኝተቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ 9 ተመልክቷል/

የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ካልተቻለው ሂሣብ ውስጥ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ለሠራዊቱ ደመወዝ፣ አበልና ማበረታቻ ወጪ ያደረገው ብር 1,708,115,690.49 እና በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር በሰሜን እና ማዕከላዊ ዕዝ ጠቅላይ መምሪያዎች ወጪ የተደረገውን የሥራ ማስኬጃ ለማጣራት የፈራሚዎች ስምና የፊርማ ናሙና ባለመቅረቡ ብር 165,686,455.58፤ እንዲሁም የውስጥ ደህንነት ጥበቃ ዋና መምሪያ ብር 24,167,053.26 እና የኢሚግሬሽንና የዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ ብር 38,575,487.91 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የሶስቱ የደህንነት መ/ቤቶች ለደመወዝ ለነዳጅና ለስልክ ወዘተ... ወጪ ያደረጉት ሂሣብ ለማረጋገጥ በኮድ የተከፈለውን ደመወዝ የሠራተኞቹ ኮድ፤ የመኪኖች ታርጋና የስልክ ዝርዝሮች እንዲቀርቡ ተጠይቆ

ባለመቅረቡ የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ መ/ቤቶቹ ለተላከላቸው የሥራ አመራር ሪፖርት መልስ አልሰጡም፡፡ ሆኖም በመውጫ ስብሰባ ወቅት የደህንነት መ/ቤቶቹ ከመ/ቤታቸው የሥራ ፀባይ አኳያ መረጃዎቹን ለመስጠት እንደማይችሉ ገልጸዋል፡፡

የሀገር መከላከያ ሚ/ር ዘግይቶ በላከው መልስ ከመረጃው ሚስጥራዊነት አንጻር የተሰው የሰራዊት አባላትና አዲስ የተቀጠሩት ሠራዊት አባላትን ከደህንነት አንጻር ችግር ያለበት በመሆኑ፣ ለወደፊቱም ቢሆን እንደዚህ አይነት ሚስጥራዊ ሰነዶችን አሳልፎ መስጠት አስቸጋሪ መሆኑ ተገልጿል፡፡

3.4.7 የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት

በበጀት ዓመቱ የተገዛ እቃ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ የተደረገና የንብረት ገቢ ደረሰኝም የተቆረጠለት መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ9 መ/ቤቶች በብር 11,043,820.01 የተገዙ ዕቃዎች የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥላቸው ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ 17 ተመልክቷል፡፡/

ከዚህ ውስጥ በኢትዮጵያ የገጠር ኤነርጂ ልማትና ማስፋፊያ ማዕከል በብር 8,868,553.64 የተገዛ ቋሚ ዕቃና የጅማ ዩኒቨርሲቲ በብር 1,340,219.93 የገዛውን ቋሚ ዕቃ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት ሲሆኑ፤ የዚህ ዓይነት አሠራር ለንብረት ብክነት ስለሚያጋልጥ አሠራሩ ተገቢ ሆኖ ባለመገኘቱ ለወደፊቱ ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ጥንቃቄ ሊደረግና የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበላቸው ንብረቶች ለየመ/ቤተቶቹ አገልግሎት ለመዋላቸው በማስረጃ እንዲረጋገጥ ለመ/ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.4.8 አላግባብ በወጪ የተመዘገበ ቅድሚያ ክፍያ

በበጀት ዓመቱ በመንግሥት መ/ቤቶች በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ ደንብና መመሪያ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ8

መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ ኮንትራታዊ አገልግሎቶች የተከፈለ ቅድሚያ ክፍያ ብር 274,651,211.51 በወጪ የተመዘገቦ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ 15.1 ተመልክቷል/

ቅድሚያ ክፍያን በወጪ ከመዘገቡት መ/ቤቶች ውሃና ኢነርጂ ሚ/ር ብር 115.69 ሚሊዮን፣ አርባ ምንጭ ዩንቨርሲቲ 112.06 ሚሊዮን እና ጂማ ዩንቨርሲቲ 37.5 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በመሆኑም የመንግሥት ሂሳብ አያያዝ በሚያዘው መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ በማድረግ፤ ቅድሚያ ክፍያው ሥራው ተጠናቆ በቂ ማስረጃ እስከሚቀርብበት ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲመዘገብ ለመ/ቤቶቹ እናሳስበናል፡፡

3.4.9 የወጪ የሂሣብ መደባቸውን ሣይጠብቁ የተመዘገቡ ወጪዎች

የወጪ ሂሣቦች የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው ደንብ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ22 መ/ቤቶች ብር 74,834,786.42 የወጪ ሂሣብ መደባቸውን ሣይጠብቁ ተመዝግበው ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ 21 ተመልክቷል/

ወጪ ሂሣብ መደብ ሣይጠብቁ ወጪ ከመዘገቡ መ/ቤቶች መካከል የውሃና ኢነርጂ ሚ/ር ብር 31.80 ሚሊዮን፤ የእንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ 23.67 ሚሊዮንና የአማኑኤል ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ብር 13.53 ዋናዋናዎቹ ነቸው፡፡

የሂሣብ መደቡን ጠብቆ ወጪ አለመመዝገብ ከበጀት አጠቃቀም አንፃር ተፅዕኖ በመፍጠር ከበጀት በላይ ወይም በታች መጠቀምን ከማስከተሉም በላይ የሂሳብ ሪፖርቱን ትክክለኛነትም ያዛባል፡፡

በመሆኑም ሂሣቦቹ በተገቢው የወጪ ሂሣብ መደብ እንዲመዘገቡና ለወደፊትም ተመሣሣይ የአሠራር ግድፈት እንዳይፈፀም ጥንቃቄ እንዲደረግ እናሳስበናል፡፡

3.5 የተከፋይ ሂሣብ

3.5.1 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ

በገ/ኢ/ል/ሚ/ር መመሪያ መሠረት በበጀት ዓመቱ በተከፋይ ሂሣብ የተያዙት ሂሣቦች በተገቢው ጊዜ ውስጥ መከፈላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ20 መ/ቤቶች ብር 247,202,349.65 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ 22 ተመልክቷል።/

በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ከታየባቸው መ/ቤቶች በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 117.31 ሚሊዮን፣በጎንደር ዩንቨርሲቲ ብር 56.99 ሚሊዮን፣ትምህርት ሚ/ር ብር 28.15 እና መቀሌ ዩንቨረሲቲ ብር 26.99 ሚሊዮን ዋናዋናዎቹ ናቸው፡፡ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር በሰኔ 30/2002 ከሠራዊት ደመወዝ ተመላሽ ተብሎ ሪፖርት የተደረገው ብር 117,314,864.62 የሠራዊቱ አባላት ደመወዝ ባለመውሰዳቸው ለረጅም ዓመታት በተከፋይ ሂሣብ የተያዘና ሂሣቡም በወጪ የተመዘገበ መሆኑን በመጥቀስ አሠራሩ ከመንግሥት የሂሣብ አሠራር ውጭ በመሆኑ እንደማንኛውም የፌደራል መንግሥት መ/ቤት ያልተከፈለ ደመወዝ በቀጣዩ ወር መጀመሪያ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ፈሰስ መደረግ እንዳለበት ደመወዝ ካልተከፈላቸው አባላት ጥያቄ ሲቀርብ ከገ/ኢ/ል/ማ/ር እየተጠየቀ እንዲከፈልና ሌሎችም መ/ቤቶች በወቅቱ ያልተከፈለውን ተከፋይ ሂሳብ ለሚመለከተው አካል የፋይናንስ ሕጉን ተከትለው እንዲከፍሉ አሳስበናል፡፡

3.6 የበጀት አጠቃቀም

ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች የተፈቀደላቸው በጀትና በሥራ ላይ ያዋሉት ሂሳብ ሲነፃፀር በርካታ ከበጀት በላይ ወጪ የተደረገና ያልተሠራበት በጀት የተገኘ ሲሆን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

3.6.1 ከበጀት በላይ የወጣ

የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በ22 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተፈቀደላቸው በጀት በላይ በደንቡ መሠረት ሳያስፈቅዱ ሥራ ላይ የዋለ ሂሳብ ብር 763,980,084.01 ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ 19 ተመልክቷል፡፡/

በጀት ሳይፈቀድ ወጪ ማድረግ እንደማይቻል በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ የተጠቀሰ በመሆኑ፤ ለወደፊቱም መ/ቤቶቹ የበጀት ዝግጅታቸውም በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ መዘጋጀት እንዳለበትና አፈጻጸሙም የበጀት አዋጅን ተከትሎ እንዲሆን በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

3.6.2 ያልተሠራበት በጀት

መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውና በጀታቸውንም በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ33 መ/ቤቶች ብር 652,262,874.59 ያልተሰራበት በጀት ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ 20 ተመልክቷል፡፡

ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተደለደለው ውስጥ ሳይሰራበት የተገኘ ሲሆን በጀትን ከተፈቀደ በኋላ አለመጠቀም ሌሎች መ/ቤቶች ሊጠቀሙበት የሚችሉትን በጀት እንዳይጠቀሙ ከማድረጉም በላይ የብቃት ማነስን (inefficiency) የሚያመለክት በመሆኑ ለወደፊቱ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

3.7 የንብረት አያያዝና አጠባበቅ

3.7.1 የቋሚ የዕቃና ንብረት አስተዳደር ድክመቶች

መንግሥት ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች ግዥ በየዓመቱ የሚያወጣው ወጪ ከፍተኛ ቢሆንም በብዙ መ/ቤቶች የሚታየው የዕቃና ንብረት አስተዳደር አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት በእነዚህ መ/ቤቶች የተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ደካማ በመሆኑ ዕቃና ንብረት

ለምዝበራና ብክነት የመጋለጥ አጋጣሚው ከፍተኛ ነው:: መ/ቤቶች የመንግሥትን ንብረት በደንቡ መሠረት መዝግበው ቁጥጥር የሚያደርጉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት የአሰራር ድክመቶች ተገኝተል፡፡

ለቋሚ ዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ	12 መ/ቤቶች
ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ	3 መ/ቤቶች
የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ	22 መ/ቤቶች
ቋሚ ዕቃ መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም ምዝገባ ያላከናወኑ	16 መ/ቤቶች
የቋሚ ዕቃ ቆጠራ ተደርጎ ከመዝገብ ጋር ሲመሳከር በታየው ልዩነት ላይ እርምጃ ያልወሰደ	1 መ/ቤት

መሆናቸው በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ 23 ተመልክቷል/

በመሆኑም መ/ቤቶቹ የመንግሥትን ንብረት ለምዝበራና ብክነት እንዳይጋለጥ ተገቢውን ምዝገባና ቁጥጥር እንዲያከናውኑ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

3.7.2 ልዩ ልዩ የንብረት አያያዝና አስተዳደር ችግሮች

የፋይናንስና ኮሚኒኬሽን መ/ቤቶች

በፌደሬሽን ምክር ቤት

- ተገዝተው በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ የተደረጉ 445 ሲዲዎች ሆነው በንብረት መዝገብ ላይ የተመዘገቡት ግን 328 ሲዲዎች ብቻ በመሆናቸው 117 ሲዲዎች በመዝገብ ሳይመዘገቡ ተገኝቷል፡፡

- ቶነር 49-A የተባለ ዕቃ የዕቃ ወጪ መጠየቂያ (ሞ/20) እንዲሁም የዕቃ ወጪ ደረሰኝ (ሞ/22) ሣይዘጋጅለትና በኃላፊ ሳይፈቀድ በመዝገብ ላይ በወጪ መገኘቱ፤

<u>በድሬድዋ ዩኒቨርሲቲ</u>

የተለያዩ ከትምህረት ሚኒስቴር የመጡ አዳዲስ ጠረጴዛዎች እና ወንበሮች ያለምንም አገልግሎት ጥበቃው አስተማማኝ ባልሆነ ክፍል ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ፤

<u>በተወካዮች ምክር ቤት</u>

- ከ1995 በጀት ዓመት ጀምሮ ያለአገልግሎት የተቀመጠ የጥርስ ህክምና መሣሪያ እና ሌሎች ለዚሁ የሚያገለግሉ ዕቃዎች እንዲሁም ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ኮምፒዩተሮች መገኘታቸው፤

<u>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን</u>

<u>አገር ውስጥ ገቢን በተመለከተ</u>

<u>በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት</u>

- አንድ ፎርክሊፍት መኪና፣ የሞተር ቁልፍ እና የጎማ መፍቻ፣ ለበከልቻ ትራንስፖርት በነፃ የተሰጠ መሆኑ፣

<u>ጉምሩክን በተመለከተ</u>

<u>የአዲስ አበባ ንግድ ዕቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት</u>

- ተሽከርካሪዎቹ የሚገኙበት ቦታ አጥር የሌለው በመሆኑ የተሽከርካሪዎቹ የተለያዩ አካሎች ለስርቆት የተጋለጡ መሆናቸው፣
- የአንድ ተሽከርካሪ ሞተር ከሻንሲው (ቦዲው) ተለያይቶ ለብቻው የሚገኝ መሆኑ፣
- ከ1996 ዓ.ም. ጀምሮ ውርስ የሆኑ ተሽከርካሪዎች ቢኖሩም እስከአሁን ግን ሳይወገዱ የሚገኙ መሆኑና አብዛኞቹ ተሽከርካሪዎች እየተበላሹ ያሉበት ሁኔታ መኖሩ፣
- ብዙ ተሽከርካሪዎች በሞ/265 ውርስ በሚደረጉበት ጊዜ የተሽከርካሪዎቹ ዋና አካል የሆኑ የሞተር እና ሻንሲ ቁጥራቸው ተመዝግቦ ያልተያዘ መሆኑ፤

አዳማ ቅ/ጽ/ቤት

- በኬላ ላይ ከግለሰቦች የተወረሰው ንብረት (በሞዴል 270) ሙሉ በሙሉ ወደ መጋዘን (የእቃ መረከቢያ ሞዴል 265) ገቢ መደረጉ ሲጣራ በሞዴል 270 ቁጥር 887555 ኬላ ላይ የተወረሰ ንብረት በሞዴል 265 ቁጥር 317716 ወደ መጋዘን ገቢ ሲደረግ ከፊሉ ገቢ ሳይደረግ የቀረ መሆኑ፣
- በሽያጭ የተወገደና ወደመጋዘን የገባ እቃ የተለያየ ሆኖ መገኘቱ፣
- ንብረቱ ገቢ የተደረገበት እና በሽያጭ ሲወገድ ከንብረት ክፍል ወጪ የተደረገበት ደረሰኝ ቁጥር የማይጠቃቀስ መሆኑ፣
- እቃዎች ተይዘው ደረሰኝ ሳይቆረጥላቸው ለረዥም ጊዜ የሚቆዩ መሆኑ፣
- የእቃ መመዝገቢያ ቢን ካርድ ስርዝ ድልዝ የበዛበት መሆኑ፣
- የእቃዎች አቀማመጥ የተዘበራረቀ ሆኖ መገኘቱ፤

ድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት

- በልዩ ልዩ ሁኔታዎች ያልተወረሱ ወይም በፍርድ ሂደት ላይ ያሉ ዕቃዎች ወይም ንብረቶች ለመንገደኞች በሚሰጥ ደረሰኝ (ሞዴል 270) የሚያዙ ሲሆን፣ ጉዳዩ ተጣርቶ እቃው እንዲወረስ ሲደረግ በውርስ ወይም የኮንትሮባንድ እቃ ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 265) በቅድሚያ ከተያዘበት የመንገደኛ ደረሰኝ እና እንዲወረስ ከታዘዘበት ደብዳቤ ጋር የማይጠቃቀስ በመሆኑ ከመንገደኞች የተወረሱት በሙሉ በውርስ ወይም የኮንትሮባንድ እቃ ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 265) ገቢ መደረጋቸውን ማረጋገጥ አለመቻሉ ፤

አዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት

- በውርስ መጋዘን ውስጥ የሚገኙ እቃዎች አያያዝ በናሙና ሲታይ የተለያዩ ንብረቶችና እና ኬሚካሎች ሳይወገዱ ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ በውርስ መጋዘን ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፤

የአዲስ አበባ ንግድ ዕቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት

- የምግብ ውጤቶች እና መድሐኒቶች ለረጅም ጊዜ በመጋዘን ውስጥ የቆዩና በአዋጁ መሰረት ተገቢው እርምጃ ሳይወሰድ ከስድስት ወር እስከ አራት አመት የቆዩ መሆኑ፣

በብሔራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ

- መ/ቤቱን የለቀቁ ሠራተኞች በውሰት የወሰዱትን ንብረት ተመላሽ ያላደረጉ መሆኑ፤

በኢትዮጵያ የገጠር ኤነርጂ ልማትና ማስፋፊያ ማዕከል

- በመ/ቤቱ በብር 25,313.13 የተገዛ ዩኒፎርምና በብር 40,560 የተገዛ ነዳጅ በንብረት መዝገብ ያልተመዘገበ መሆኑ፤
- መ/ቤቱን የለቀቁ ሠራተኞች በውሰት የወሰዱትን ንብረት ተመላሽ ያላደረጉ መሆኑ፤

የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም

- በዕቃ መጋዘን ውስጥ ከተቀመጡ አንድ ዓመት የሆናቸው ከዩ.ኤን.ዲ.ፒ በእርዳታ ተገኝተው ርክክብ ያልተፈጸመባቸውና የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠላቸው በርካታ ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎች፣ መደርደሪያዎች፣ ሳፋዎችና የመሳሰሉት ንብረቶች መኖራቸው፤
- የቋሚና የአላቂ ንብረቶች ገቢና ወጪ በሞዴል 70/ሐ ካርዱን ኮፒ በማድረግ ብቻ የሚመዘግብ መሆኑና አልፎ አልፎ ወዲያው ገብተው ወዲያው ለሚወጡ የማይመዘገብ መሆኑ፣
- አሮጌ የተሽከርካሪ መለዋወጫዎች የመመዝገቢያ ቅጽ ተዘጋጅቶላቸው በንብረት ገቢ ደረሰኝ ንብረት ክፍሉ ተረክቦ በማስቀመጥ በሽያጭ እንዲወገዱ አለመደረጉ፣

የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት

- በግ/ቤት የዕቃ መደርደሪያ ባለመዘጋጀቱ ተደራርበው እና ለአያያዝ በማያመች ሁኔታ መቀመጣቸው፣

የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር

- በዋናው መ/ቤት በሚገኘው የወዳደቁ መጋዘን ክፍል ውስጥ ያሉ ዕቃዎች የዕቃ መደርደሪያ የሌላቸውና ዓይነት በዓይነት ሳይለዩ በመሬት ላይ የተቀመጡ መሆኑ ታውቋል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ

በክምችት ክፍል ብር 881,846.17 በድልድል ክፍል ብር 692,288.71 በድምሩ ብር 1,574,134.88 የሚገመቱ ቁሳቁሶች /ንብረት/ በጉድለት የተገኘ መሆኑና በዚሁ መሠረት ጽ/ቤቱ የወሰደው እርምጃ አለመኖሩ፤

የሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴር

- አገልግሎት የማይሰጡና የተበላሹ እንዲሁም አገልግሎት የሚሰጡ ንብረቶች በአንድ ቦታ መጠበቃቸውና መወገድ የሚገባን ንብረት ለስራ አመራሩ ጊዜውን የጠበቀ መረጃ የማይደርስ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

መሆኑም የተጠቀሱት የንብረት አያያዝና አጠባበቅ ጉድለቶች እንዲስተካከሉ አፋጣኝ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

አገልግሎት መስጠት የማይችሉ ያልተወገዱ የተለያዩ ንብረቶች

መጠገን ወይም ለሌላ አገልግሎት መዋል የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመንግሥት መመሪያ መሠረት ሳይወገዱ፤ በ14 መ/ቤቶች የተገኙ ሲሆን፤ ንብረቶቹም ኮምፒውተሮች፣ ኘሪንተሮች፣ ወንበሮች፣ የመኪና መለዋወጫዎች እንዲሁም የተለያዩ ዕቃዎች ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ ፤አገልግሎት የማይሰጡና ተጠግነው አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉት፤ ተለይተው እርምጃ ያልተወሰደባቸው የተለያዩ ንብረቶች ለረዥም ዓመታት ሳይወገዱ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ ተውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ 23 ተመልክቷል/

በመሆኑም ንብረቶቹ የበለጠ ሳይበላሹ በመንግሥት መመሪያ መሠረት አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ እንዳሚገባ አሳስበናል፡፡

ተሽከርካሪ

የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝን በተመለከተ በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

ሊብሬ ያልቀረበላቸው	በ8 መ/ቤቶች	271 ተሽከርካሪዎች
በብልሽት ምክንያት የቆሙ	በ13 መ/ቤቶች	186 ተሽከርካሪዎች
የሻንሲና ሞተር ቁጥር ከሊብሬ ጋር ተቀያይሮ ተመዝግቦ የተገኘ	በ1 መ/ቤት	2 ተሽከርካሪዎች
የቻሲና የሞተር ቁጥራቸው የማይታወቅ	በ2 መ/ቤቶች	10 ተሽከርካሪዎች
ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ	በ1 መ/ቤት	3 ተሽከርካሪዎች

መ/ቤቶቹም በሁኔታው ላይ የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በመግለጽ በብልሽት ምክንያት ቆመው የሚገኙ መኪናዎች ተጠግነው አገልግሎት መስጠት እንዳለባቸው፤ የማያገለግሉት ደግሞ በመንግሥት መመሪያ መሠረት እንዲሸጡ፤ የቻሲና የሞተር ቁጥራቸው የማይታወቅ እና ሊብሬ ያልቀረበላቸው ደግሞ ጉዳዩ ተጣርቶ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

የነዳጅ ኩፖን አጠቃቀም

የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም

ለነዳጅና ቅባቶች ግዥ ቅጽ ያልተዘጋጀና አጠቃቀማቸውን በተመለከተ ጠንካራ የቁጥጥር ሥርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፣

ለነዳጅና ቅባቶች ግዥ ቅጽ እንዲያዘጋጅ፤ ጠንካራ የቁጥጥር ስርዓት እንዲዘረጋ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.8 የክትትልና የማሻሻያ እርምጃ አወሳሰድ

3.8.1 ባለፈው ኦዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ ስለመሆኑ

ባለፉት በጀት ዓመታት መ/ቤታችን በላካቸው የኦዲት ሪፖርቶች መሠረት እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

በኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት በ2000 በጀት አመት የሳጥን ሂሳብ ብር 216,256.11 ሳይስተካከል የተገኘ፤

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዲፕሎማቲክ ሚሲዮን በ2000 በጀት ዓመትየተሰብሳቢ ሂሣብ ብር 15,291,226.54 የተከፋይ ሂሣብ ብር 7,176,654.26 ኮፒ ማስረጃ ያልቀረበለትና፤ ምንም ማስረጃ ሳይኖረው የተመዘገበ፤ በዚህ ኦዲትም ማስረጃ ያልቀረበላቸው መሆኑን በመግለጽ ማስረጃ እንዲቀርብላቸው ለድርጅቱ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት በድጋሚ አሳስበናል፡፡

የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም

- የተቋሙ ሠራተኛ አቶ ምኒሊክ አለማየሁ የሠሌዳ ቁጥር 412187 ሲያሽከረክሩ በራሳቸው ጥፋት በደረሰው አደጋ ከተቋሙ ሥራ ማስኬጃ በ2001 በጀት ዓመት ብር 32,816.88 ለካሣ ተከፍሎ በመገኘቱ ከሠራተኛው ሊተካ ስለሚገባ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም በዚህ በ2002 በጀት ዓመትም ገንዘቡ እንዳልተተካ በመግለጽ በድጋሚ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡
- በ2001 በጀት ዓመት በተቋሙ በተደረገ ኦዲት 2 ሞተር ብስክሌቶች የጠፉ በመሆኑ ክትትል ተደርጎ የንብረቶቹ ሁኔታ እንዲጣራ አሳስበናል፡፡ ሆኖም በ2002 በጀት ዓመት ኦዲት የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ እንዲታወቅ በመግለጽ በድጋሚ ክትትል ተደርጎ ሁኔታው እንዲጣራ አሳስበናል፡፡

ተቋሙ በላከው መልስ በሠራተኞች መቀያየር ምክንያት ክትትሉ ጠንካራ እንዳልነበረ ጠቅሶ ጉዳዩ እልባት እስኪያገኝ በቋሚነት የሕግ ባለሙያ መድቦ ክትትል እየተደረገ መሆኑ ተገልጿል፡፡

ይሁን እንጂ በተሰጠው የኦዲት የማሻሻያ ሃሳብ መሠረት እርምጃ አለመውሰድ አግባብ አለመሆኑን ገልፀን የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በኦዲት አስተያየቶች መሠረት እርምጃ መወሰዱን በቅርብ ክትትል እንዲያደርጉ አስገንዝበናል፡፡

3.8.2 <u>የኦዲት ማሻሻያ ሃሣቦች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ስለመወሰዱ የሚደረግ ክትትልን በተመለከተ</u>

በመ/ቤታችን ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ኦዲት ተደራጊዎች በፌዴራል ዋና ኦዲተር በተላኩ የኦዲት ሪፖርቶች የተገለጹ ግኝቶች ላይ በጊዜ ገደብ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ እንዳለባቸውና ለመውሰድ ካልቻሉም ምክንያቱን በመግለፅ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማሳወቅ እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡ ይህንኑ ድንጋጌ መነሻ በማድረግ መ/ቤታችንም አዲስ የክትትል ሥርዓት ዘርግቷል፡፡ በዚሁ መሠረት የ2002 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት እንደተጠናቀቀ ጎላ ጎላ ያሉ ግኝቶች ለተገኙባቸው 80 መ/ቤቶች የማስተካከያ መርሃ-ግብር ነድፈው እንዲያሳውቁን ጥያቄ የቀረበ ቢሆንም እስከአሁን መርሀ-ግብሩን የላኩት 34 መ/ቤቶች ብቻ ናቸው፡፡ ያለበቂ ምክንያት በፌዴራል ዋና ኦዲተሩ በቀረቡ የኦዲት ሪፖርቶች በተሰጡ የማሻሻያ አስተያየቶችና ሃሣቦች ላይ በወቅቱ እርምጃ ያለመውሰድ የሕግ ተጠያቂነትን የሚያስከትል መሆኑ ታውቆ የእያንዳንዱ ኦዲት ተደራጊ የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ም/ቤቱም በዚህ ረገድ የሚያደርገውን ክትትልና ቁጥጥር ማጠናከር ይኖርበታል፡፡

3.9 <u>የ2002/3 የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ‘PBS’ ፕሮጀክት ተከታታይ ኦዲቶች አስተያየቶችና ጉልህ የሆኑ የኦዲት ግኝቶች ማጠቃለያ ሪፖርት</u>

በአሁኑ ወቅት የሚያከናውነው ኦዲት የኢትዮጵያ መንግሥትና የዓለም ባንክ ባደረጉት ስምምነት መሠረት የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ (PBS) ፕሮጀክት ተከታታይ (Continuous) ኦዲት ሲሆን፣ ይህም ኦዲት በየሩብ ዓመቱ እየተከናወነ በስምምነቱ መሠረት ሪፖርቱ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር እና ለዓለም ባንክ በወቅቱ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡ ይህ ኦዲት የሚሸፍናቸው ሴክተሮች የመሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ የሆኑትን በወረዳና በክልል ደረጃ የሚገኙ የጤና፣ የትምህርት፣ የግብርናና ተፈጥሮ ሀብት፣ የንጹህ ውሃ አቅርቦትና የገጠር መንገድ ሴክቶሮችን ነው፡፡

በመጀመሪያው የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ (PBS I) ፕሮጀክት ወቅት (ከሚያዝያ/98 - ግንቦት/01) ድረስ በነበረው የኦዲት ስምምነት (ToR) መሠረት ተከታታይ ኦዲቱ አራት ክፍሎችን የያዘ ሲሆን፣ እነዚህም የበጀት ድልድል ቀመርን (Fairness)፣ ግልጽነትና ተጠያቂነትን (Transparency and Accountability)፣ የበጀት ዕድገትን (Additionality) እና ህጋዊነትን (Fiduciary Responsibility) በተመለከተ እንደ ነበር ይታወቃል፡፡

ይሁንና ይህ የመጀመሪያው ዙር ፕሮጀክት (PBS I) ግንቦት/2001 የተጠናቀቀ ሲሆን፣ ሁለተኛው ዙር የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ (PBS II) ፕሮጀክት ደግሞ ከግንቦት/2001 መጨረሻ ጀምሮ ተግባራዊ እንዲደረግ በተገባው የውል ስምምነት መሠረት የተከታታይ ኦዲቱም ስምምነት (ToR) በተመሣሣይ ሁኔታ የተሻሻለ ሲሆን፣ በተሻሻለው የኦዲት ስምምነት መሠረት በመጀመሪያው ፕሮጀክት ውስጥ ይቀርቡ ከነበሩት አራት ክፍሎች ውስጥ የሁለተኛው ፕሮጀክት የመጀመሪያዎቹን ሦስት ክፍሎች ከተከታታይ ኦዲቱ ውስጥ በማስወጣት በአራተኛው ክፍል ላይ ማለትም በህጋዊነት (Fiduciary Responsibility) ላይ ብቻ ተከታታይ ኦዲቱ እንዲያተኩር ተደርጓል፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው ተከታታይ ኦዲቱ የፕሮጀክቱ ሂሣብ ዓመታዊ ኦዲት አካል እንዲሆን በመፈለጉ ነው፡፡

ስለሆነም የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ሁለተኛ ዙር (PBS II) ፕሮጀክት ተከታታይ ኦዲት ዋና ትኩረት በእነዚህ መሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች (በወረዳና በክልል ደረጃ) የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ላይ በመሆኑ፣ በየሩብ ዓመቱ እየተጠቃለለ የሚላከው የተከታታይ ኦዲት ሪፖርት ግኝቶች የሚያተኩረው በገንዘብ መጠን (quantitative amount) ላይ ሳይሆን፣ በዓይነት ላይ (Qualitative) በመሆኑ፣ ዋና ዋና ግኝቶች የሚባሉት በዓይነት እንጂ በመጠን አለመሆናቸውን እንገልፃለን፡፡

በመሆኑም በ2002/3 የኦዲት ዘመን ለተከናወኑት ተከታታይ ኦዲቶች የተሰጡት የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት የኦዲት አስተያየቶችና በየመሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች የሚታዩት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች በአብዛኛው

ተመሣሣይነት ያላቸው በመሆኑ፣ ዋና ዋና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶቹ በአንድ ላይ ተጠቃለው በሚከተለው ሁኔታ ለዓይነት ቀርበዋል፡፡

ሀ/ <u>በ2002/3 የኦዲት ዘመን የታዩ ዋና ዋና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች</u>

በአሁኑ ወቅት የተወሰነ መሻሻል ቢታይም፣ ቀጥሎ የተመለከቱት ዋና ዋና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች በበርካታ የመሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች ውስጥ በመታየት ላይ ናቸው፡፡ እነሱም፣

በየወቅቱ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ እየተደረገ ከመዝገብ (ሌጀር) ከወጪ ቀሪ ጋር የማይመሳከር መሆኑ፣

- የባንክ ሂሣብ ማስታረቂያ በየወሩ የማይዘጋጅ መሆኑ፣
- የቅድሚያ ሂሣብ ክፍያዎች በወቅቱ አለመወራረዳቸው፣

ለቅድሚያ ሂሣብ ክፍያዎች መቆጣጠሪያ የሚረዱ ደጋፊ ሌጀሮች (Subsidiary ledgers) አለመቋቋማቸው፣

- የተወሰኑ ክፍያዎች በበቂና አግባብ ባላቸው ማስረጃዎች አለመደገፋቸው፣
- የሂሣብ እንቅስቃሴዎች (Transportations) በወቅቱ አለመመዝገባቸው፣
- ወርሃዊ የሂሣብ መግለጫዎች በአብዛኛው በወቅቱ እየተዘጋጁ ለሚመለከተው ክፍል አለመላካቸው፣
- የተወሰኑ የሂሣብ እንቅስቃሴዎች (Transactions) በተገቢው የሂሣብ መደብ አለመመዝገባቸው፣
- የአላቂና ቋሚ ዕቃዎች መቆጣጠሪያ መዝገብ በአብዛኛው መ/ቤት አለመቋቋም፣
- ቋሚ ዕቃዎች በአብዛኛው መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፣
- ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ እየተደረገ ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር በአብዛኛው የማይመዛዘኑ መሆኑ፣ እና
- ለኦዲት ሥራ ድጋሚ በሚኬድበት ወቅት፣ ባለፈው ኦዲት ወቅት በታዩ ድክመቶች ላይ በአብዛኛው የማሻሻያ እርምጃ አለመወሰዱ፣

ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከላይ ለተመለከቱት ድክመቶች አለመሻሻልና በወቅቱም እርምጃ ላለመወሰዱ ኦዲት ተደራጊዎች ሲጠየቁ የሚሰጧቸው መልሶች (Management Responses) ሲጠቃለሉ፤

- ከፍተኛ የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት መኖር፣
- የበጀት እጥረት መኖር፣
- የግንዛቤ ማነስ፣ እና
- የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ለጉዳዩ በቂ ትኩረት አለመስጠት፤

ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በዚህ መሰረት ኦዲት በተደረጉት 276 (አንድ ልዩ ኦዲትን ሣይጨምር) ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደሮች የሚከተለው አስተያየት ተሰጥቷል፡፡

ሀ/ አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት (Clean)	4
ለ/ ከጥቂት ጉድለቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ሐ/ ነቀፌታ ያለበት አስተያየት የተሰጠባቸው (Except for)	266
መ/ የጎላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት (Adveres)	3
ሠ/ በተለያዩ ምክንያቶች የመ/ቤቶቹን ሂሣብ ኦዲት ለማድረግ ባለመቻሉ አቋም ለመውሰድ (Disclaimer) ያልተቻለባቸው	3
ድምሩ	276

ናቸው፡፡

4. <u>የክዋኔ ኦዲት ግኝቶች እና የማሻሻያ ሀሳቦች</u>

የክዋኔ ኦዲት መሠረታዊ ተልዕኮ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና ድርጅቶች የተመደበላቸውን የሰው ኃይል፣ ገንዘብና ቁሳቁስ ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ በመጠቀም እንቅስቃሴአቸው በብቃት በማከናወን የተሰጣቸውን የሥራ ኘሮግራም ከግብ በማድረስ የሚጠበቀውን ውጤት ማስገኘታቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት አካሂዶ የታዩ ድክመቶች እንዲስተካከሉ ለሥራ አመራሩ ተገቢውን የማሻሻያ ሃሣብ ማቅረብና ተፈፃሚነታቸውንም በመከታተል ስኬታማ ውጤት እንዲገኝ መርዳት እና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ ነው::

የመንግሥት መ/ቤቶች ያቀዷቸውን ሥራዎች በተመደበላቸው በጀት ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ እና በቅልጥፍና ማከናወናቸውን እንዲሁም የሥራ ኘሮግራሞቻቸው ስኬታማ መሆናቸውን የፌዴራል ዋናው ኦዲተር አጣርቶ ሪፖርት ማቅረብ እንዳለበት በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 4 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ኦዲት አድርጎ፣ ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች የታዩ ጉልህ ድክመቶች ጠቅለል ባለ መልኩ ቀጥሎ ቀርበዋል።

4.1 <u>በውሃ ሀብት ልማት ሚኒስቴር የከሰም ተንዳሆ ግድብና መስኖ ልማት ኘሮጀክት የመስኖ ልማት (Irrigation) በተመለከተ</u>

- በከሰምና ተንዳሆ መስኖ ልማት ላይ የተመረኮዘ ወቅታዊ ሁኔታዎችን የሚያሳይና በጥናት ላይ የተመሰረተ የፕሮጀክት ረቂቅ ሰነድ ያልተዘጋጀለት መሆኑ፣
- ስለማህበራዊ ጉዳዮችም በቅድሚያ ከአካባቢው ነዋሪዎች ጋር ውይይትና የግንዛቤ ማዳበር ስራ አለመሰራቱ፤
- በውኃ ሀብት ሚ/ር የከሰምና ተንዳሆ ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት አስተባባሪ ጽ/ቤት የመስኖ ልማት ግንባታውን የሚቆጣጠርበት፣ የሚከታተልበት እና የሚገመግምበት የፕሮጀክት ሥራ አመራር መመሪያ (Project management manual) ያልተዘጋጀ መሆኑ፤
- የግንባታ ስራቸው የተጠናቀቁ የመስኖ ልማቱ መሬቶች ርክክብ እስኪደረግባቸው ድረስ የሚደረገው የጥበቃ ስርዓት ያልተጠናከረና የተሰራውን ስራ ለአደጋ የሚያጋልጥ መሆኑ፤
- ለፕሮጀክቱ ስራ መጓተት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ካደረጉት ችግሮች መካከል አንዱ ከአካባቢው ህብረተሰብ ጋር የተፈጠረው አለመግባባት እንደሆነ በሥራ ሪፖርቶች ተገልጿል፡፡ ይህንንም ችግር በዋነኘነት ከሚያባብሱት ምክንያቶች አንዱ ማህበራዊ ችግሮችን ለመከላከልና ለአካባቢው ነዋሪዎች እንዲውል የታቀደው የመሠረተ ልማት አውታሮች ግንባታ ቅድሚያ ተሰጥቶት ባለመገንባቱ መሆኑ፤

በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተጠቀሱትን ችግሮች በመፍታት የፕሮጄክቱ አመራር ውጤታማና ስኬታማ ስኬታማ ለማድረግ ተገቢ የሆነ ማሻሻያ ሃሣቦች ተሰጥቷል፡፡

4.2 በትምህርት ሚኒስቴር የዩኒቨርስቲ አቅም ግንባታ ኘሮግራም የአሥራ ሦስት ዩኒቨርስቲዎች ግንባታን በተመለከተ

- የዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ኘሮጀክቱ ሲጀመር ግንባታው የሚከናወንባቸው ቦታዎች ያለውን የማቴሪያል አቅርቦት፣ ብቃት ያለው የሰው ሀይል መኖሩን፣ የትራንስፖርት አመቺነት እንዲሁም በአጠቃላይ ግንባታው በታሰበው ጊዜ፣ ገንዘብና የጥራት ደረጃ ለማከናወን የሚቻል መሆኑን ለመገምገም የሚያስችል የአዋጭነት ጥናት አለመደረጉ፤
- ፕሮጀክቱ ከመጀመሩ በፊት የትምህርት ሚኒስቴር ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች ጋር በቅድሚያ ስምምነት ባለማድረጉ በናሙና ኦዲት ከተደረጉ ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ በአዳማ፣ በዲላ፣ በሶዶና በቴፒ ከፍተኛ የውሃ ችግር መኖሩ፣ በመደወላቡ ዩኒቨርሲቲ አንድ የስልክ መስመር ብቻ እንዳለ እንዲሁም በደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ የኤሌክትሪክ ስርጭት ችግር መኖሩ፤
- የግንባታው ዲዛይን በየጊዜው ለውጥ መደረጉ ተጨማሪ ገንዘብ እንዲወጣ ምክንያት ከመሆኑም በላይ በተማሪዎቹ ላይ ችግር መፍጠሩ፤
- በናሙና ከታዩት ስድስት ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ሶስቱ፣ የሚዛን ቴፒ፣ የመደውላቡና የዲላ ዩኒቨርሲቲዎች የሳይንስ ፋክልቲዎች የላብራቶሪ መሳሪያ ስለሌላቸው ተማሪዎች ወደተለያዩ ክልሎች በመሄድ ለነባር ዩኒቨርሲቲዎች ክፍያ በመክፈል ትምህርት እንዲያገኙ መደረጉ፤
- ትምህርት ሚ/ር ለዩኒቨርሲቲዎቹ ማሰሪያ የሚከፍለውን ወጪ፣ የወጪውን አይነት የገንዘቡን ልክ፣ የግንባታውን ደረጃ እንዲሁም ጊዜውን የሚያሳይ መቆጣጠሪያ መረጃዎች አለመያዙ ፕሮጀክቶችን በሚገባ ለመቆጣጠር የማይቻል መሆኑ፤

- በአብዛኛዎቹ ዩኒቨርስቲዎች ከጊዜያዊ ርክክብ በኋላ በአያያዝ ጉድለት የሚከሰቱ ጥፋቶችን ተከታትሎ ለመጠገን የሚችሉ የጥገና ስራ ክፍሎች ባለመኖራቸው ችግሮቹ ሊባባሱ ችለዋል፡፡
- የግዥውና የግንባታው እቅድ አፈፃፀም ያልተጣጣመ መሆን ተገዝተው የሚመጡ ዕቃዎች አመቺ ባልሆነ ቦታ ተቀምጠው ለብልሽት እንዲጋለጡ ሊያደርግ መቻሉ፤

በመሆኑም ሚ/ር መ/ቤቱ ቀሪው የዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ውጤታማ በሚያደርግ መልኩ በመምራት አስፈላጊው ክትትልና ግምገማ ማድግ እንደሚገባና የተጠቀሱት ስህተቶች ሊታረሙ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.3 በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት በቡና ምርምር ፕሮጀክትን በተመለከተ

- ከአገሪቱ የልማት ፍላጎት ጋር ተገናዝበው የሚነደፉ የግብርና ምርምር ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሥራ ሂደት ወጥነት እንዲኖረው የሚያስችል፣ በአግባቡም ተዘጋጅተው የሚነደፉ ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶችና ያስገኙትን ውጤት ለመገምገምና ተፈጻሚነታቸውንም ለመከታተል የሚያስችል የስራ መመሪያ ያልተዘጋጀ መሆኑ፤
- የምርምር ፕሮጀክቱ በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ስራው መጀመር እና መጠናቀቅ ሲገባው ስራው በተያዘለት የሥራ ዘመን ሊጠናቀቅ አለመቻሉና ተጨማሪ አዳዲስ ተግባራት ታክለውበት የስራ ዘመኑ ለተጨማሪ 5 ዓመታት (ከ1998-2002) የተራዘመ መሆኑን፤ ፕሮጀክቱ ቀደም ብሎ በተያዘለት የሥራ ዘመን መሰረት ያልተጠናቀቀበትን ምክንያት በስራ ዘመኑ ማብቂያም ከዕቅዱ ምን ያህል እንደተጠናቀቀ እና እንዳልተጠናቀቀ፣ ያጋጠሙ ችግሮችና በጎ የስራ ተሞክሮዎች ተለይተው ሪፖርት አለመደረጋቸውና ዝርዝር ሁኔታውን ለመገንዘብ አለመቻሉ፤
- በፌዴራልና በክልል የግብርና ምርምር ማዕከላት የሚከናወኑ የምርምር ፕሮጀክቶች መካከል አላስፈላጊ የሆነ የስራ ድግግሞሽና የሐብት መባከን እንዳይኖር ለመከላከል የሚያስችል የፕሮጀክት ግምገማ ስርዓት አግባብ

ካላቸው የክልል አካላት ጋር በመተባበር መዘርጋት ለኢንስቲትዩቱ የተሰጠ የስራ ኃላፊነት ቢሆንም ወጥነት ያለው ስራ ለመስራት የሚያስችል ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፤

በመሆኑም ኢንስቲትዩቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የተሰጠውን የስራ ኃላፊነት ውጤታማና ስኬታማ ሊያድርግ የሚያስችል የፕሮጀክት ክትትልና ግምገማ ስርዓት ልተዘረጋ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.4 በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆች መከላከልን በተመለከተ

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 4/87 የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆች የሚወገዱበትን መንገድ የማጥናት፣ የማስተባበርና ድጋፍ የመስጠት ኃላፊነት የተሰጠው በመሆኑ በድርጅታዊ መዋቅሩ ውስጥ ለተሀድሶ ጉዳይ መምሪያ ተጠሪ የሆነ የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆች ጉዳይ ቡድን በ1997 ዓ.ም. ተቋቁሞ ነበር፡፡ ሆኖም በመ/ቤቱ በተካሄደው የመሠረታዊ የአሠራር ለውጥ (BPR) ጥናት ይህንን በተመለከተ ያለው ኃላፊነት እንዲወጣ በመደረጉ የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆችን የሚመለከቱ ስራዎች ከ1997 ዓ.ም. ጀምሮ ኦዲቱ እስከተከናወነበት ጊዜ ድረስ ያልተሰሩ መሆኑን በመ/ቤቱ ውስጥ ካገኘናቸው መረጃዎች ለመረዳት ችለናል፡፡ በመሆኑም፤

- የማበራዊ ኑሮ ጠንቆችን የተመለከቱ ስራዎች በመ/ቤቱ ስትራቴጂክ እቅድና አመታዊ እቅዶች ውስጥ አለመካተታቸው፣
- የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆችን በተመለከተ እንዲሰራ ኃላፊነት የተሰጠውና በመ/ቤቱ መወዋቅር ላይ የሚታየው የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆች ቡድን ከ1997 ዓ.ም. ጀምሮ መታጠፍን፣
- መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ግለሰቦች፣ እንዲሁም ህብረተሰቡ የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆችን ለመከላከል ለመቆጣጠርና ለማቃለል ለሚዘረጓቸው ፕሮግራሞች ድጋፍና እገዛ የሚያደርግ አካል አለመኖሩን፣

- የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆች በአገሪቱ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ የሚያሳዩ የጥናትና ምርምር ተግባሮች አለመከናወናቸው፣ የስታትስቲክስ መረጃዎች አለመኖራቸው፣
- የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ህጎችና መመሪያዎች አለመውጣታቸው፣
- በማህበራዊ ኑሮ ጠንቆች የተጠቃውን የህብረተሰብ ክፍል ከሚገኝበት ችግር ለማላቀቅ የሚያስችሉ የተሀድሶ፣ የሙያ ስልጠና እንዲሁም የስራ ስምሪት አገልግሎቶች የሚያገኙበት ሁኔታ አለማመቻቸት፣
- ህብረተሰቡ ለማህበራዊ ኑሮ ጠንቆች መንስኤ ከሆኑ ጎጂ እምነቶች፣ ጎታች ልማዶችና አስተሳሰቦች እንዲላቀቅ የሚያስችሉ የትምህርት ፕሮግራሞች እንዲመቻቹ አለመደረጉ፣
- የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆችን በተመለከተ ኃላፊነት ወስዶ የሚሰራ የፌዴራል መንግስት አካል ሳይኖር ሚኒስቴር መ/ቤቱ ይህንን ሥራ ማቆሙ ለችግሩ መጨመር ምክንያት መሆኑ፤በዳሰሳ ጥናቱ ታይቷል፡፡

ሆኖም የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆችን በተመለከተ የተጀመረው ኦዲት የዳሰሣ ሥራው ተጠናቅቆ ሌሎች ሥራዎችን ለመቀጠል አዋጪ ባለመሆኑ ሥራው ተቋርጧል፣

4.5 <u>በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የአትሌቲክስ ስፖርትን በአገሪቱ በማስፋፋት ብቃት ያላቸውን አትሌቶች ለማፍራት የሚያደርገውን እንቅስቃሴ በተመለከተ</u>

- አትሌቲክስ ስፖርትን ለማስፋፋትና ለማጠናከር ብሎም ሀገሪቱን ወክለው በተለያዩ ዓለም አቀፍ እና አህጉር ደረጃ በሚዘጋጁ የአትሌቲክስ ውድድሮች ላይ የሚወዳደሩ ተተኪ አትሌቶችን ለማፍራት በሁሉም ክልሎች ከታች ከቀበሌ እና ከወረዳ ጀምሮ እስከ ክልል ድረስ ተገቢው ትኩረት ተሠጥቶት ስፖርቱን ለማስፋፋት የሚያስችል አደረጃጀት ባለመዋቀሩ፤ በአትሌቲክስ ስፖርቱ ዙሪያ

ለሚከሠቱ ችግሮች ተገቢውን ወቅታዊ መፍትሔ የመስጠት ድክመት መታየቱ፤

- ለታዳጊ ወጣቶች ኘሮጀክቶች ሥልጠና፣ ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርጉ የባለድርሻ አካላት አደረጃጀት ተግባርና ኃላፊነት በግልጽ ያልተቀመጠ ሲሆን፣ ስፖርቱ በህብረተሰቡ ዘንድ እንዲዘወተር እና እንዲስፋፋ ለማድረግ የተቀናጀ እና ወጥ አሠራርን የተከተለ የአተገባበር ስልት ለመቀየሱ፤
- በዓለም አቀፍ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን (IAAF–International Amateur Athletics Federetion) በሚያዘጋጃቸው የተለያዩ ሥልጠናዎች እና አውደ ጥናቶች ለሚካፈሉ ተሳታፊዎች የተሸሻሉ መመሪያዎችና ሌሎች መረጃች ቢሠጡም፤ መረጃዎቹን የወሠዱት ተሳታፊዎቸ ለሚመለከተው አካል መድረሳቸውን ከአገር አቀፍ ፌዴሬሽኑ ጀምሮ እስከ ታች ድረስ ያሉ አስፈጻሚ አካላት ያላቸው የቅንጅታዊ አሠራር፣ የክትትል እና የቁጥጥር ሥርዓት ደካማ በመሆኑ፤
- ፌዴሬሽኑ የአትሌቲክስ ስፖርትን ለማስፋፋት ተገቢ የገቢ ማሰባሰቢያ ስልት ነድፎ መንቀሳቀስ ሲገባው፤ የገቢ ዕቅዱ ሁኔታዎችን ባገናዘበ መልኩ ያለመያዙ፤ ከአቅም በላይ የሆነ የሥራ ዕቅድ እንዲያዝና አፈፃፀሙም እንዲዛባ የሚያደርግ መሆኑ፤
- ለሰንዳፋ አትሌቲክስ መንደር ግንባታ ገንዘብ ለመለገስ ቀደም ሲል ቃል የተገባና የተለያዩ የገቢ ማስገኘ ዘዴዎች ቢቀየሱም ተግባራዊ ያልተደረጉና ቃል የተገባውም ገንዘቡ እንዲሰበሰብ በቂ ጥረት አለመደረጉ፤
- በአጭር ርቀትና በሌሎቹም ዝቅተኛ ተሳትፎ በሚደረግባቸው እና ምንም ተሳትፎ በሌለባቸው የአትሌቲክስ ዘርፎች ላይ ትኩረት ተሠጥቶ እየተሠራ ካለመሆኑም በላይ፤ በክልል እና በክለቦች ተገቢው የሥልጠና ቁሳቁሶችና መሣሪያዎች ባለሚለታቸው፤ በነዚህ ዘርፎች ተሰጥኦ ያላቸው አትሌቶች ያላቸውን ችሎታ አሻሽለው የተሻለ ውጤት ለማምጣት እንዳይችሉና አገሪቱ በዚህ ዘርፍ ውጤት እንዳታስመዘግብ የሚገደብ መሆኑ፤

- በብሔራዊ አትሌትነት የሚታቀፉ አትሌቶች መምረጫ መስፈርት በየዓመቱ እንደ አዲስ እየተዘጋጀ ምርጫ የሚከናወን ቢሆንም፤ ለ2001 ዓ.ም ሀገርን ወክለው በተለያዩ ዓለም አቀፍ እና በአህጉር ደረጃ በሚዘጋጁ ውድድሮች ላይ የሚወዳደሩ አትሌቶች ያስመዘገቡት የተሻለ ሰዓት ተሟልቶ ያልተገለፀና የተመረጡትን አትሌቶች የሚያሳየው መረጃም በሚመለከተው የፌዴሬሽኑ አካል መጽደቁን እና ትክክለኛነቱን የሚያሳይ ማረጋገጫ ባለመኖሩ፤ የመምረጫ መስፈርት ተጠብቆ ምርጫው ግልጽነትን የተከተለ መሆኑን ለማረጋገጥ የማያስችልና ለተለያዩ የአሠራር ድክመቶች መንገድ የሚከፍት መሆኑ፤
- በየውድድር ዘርፉ የብሔራዊ ቡድን አትሌቶችን እና አገርን ወክለው የሚወዳደሩ አትሌቶችን የሚያሰለጥኑ አሠልጣኞችን ለመመደብ ፌዴሬሽኑ ከዘጋጀው የመምረጫ መስፈርት ውስጥ ዋነኛው የአሠልጣኞች የትምህርት ደረጃ ቢሆንም፣ ከመስፈርቱ በታች በተለያዩ ደረጃዎች አሰጠልጣኞች የተመደቡ መሆኑና፤ በሌለው የሥራ መደብ አሰልጣኞቹን መመደቡ በአሰልጣኞች ዙሪያ የጎላ ክፍተት ከመፍጠሩም በላይ ለብልሹ አሠራር መንገድ የሚከፍት መሆኑ፤
- በፌዴሬሽኑ ተዘጋጅተው የሚሰጡ ሥልጠናዎች ላይ የሚሰጥ ፈተና ማዕከላዊነትን በጠበቀ እና ገለልተኛ በሆነ አካል እንዲዘጋጅ እና እንዲታረም አለመደረጉ ፈተናውና ምዘናው ወጥ እና ሠልጣኞችን በእኩል ደረጃ ለመመዘን የማያስችል ከመሆኑም፤ በላይ ሥልጠናውን ማጠናቀቃቸውን በማረጋገጥ የሚሰጠው ሠርቴፊኬትም አንድ ወጥ እና ሚዛናዊነትን የተከተለ እንዳይሆን የሚያደርገው መሆኑ፤
- የአትሌቲክስ ፌዴሬሽኑ በቅድሚያ የክልሎችን እና የክለቦችን የሥልጠና ፍላጐት ሳያካትት የሥልጠና መረሐ ግብር ካወጣ በኂላ እንዲያውቁት ብቻ ስለሚልክ፤ የእነዚህ አካላት የስልጠና ፍላጐትን ያላገናዘበ ከመሆኑ፤
- ፌዴሬሽኑ ለአትሌቲክስ ስፖርት አሠልጣኞች የሙያ ደረጃ አውጥቶ በየደረጃው ፈቃድ ለመስጠት በ1999 በጀት ዓመትና በቀጣይ ዓመታትም በዕቅድ ተይዞ ተግባራዊ አለመደረጉ፣ በተለያየ ደረጃ የሚገኙ አትሌቶች ደረጃቸውን በጠበቁ አሠልጣኞች ሰልጥነው ተፈላጊውን ውጤት ለማስገኘት የሚያስችል ተገቢ

ስልጠና እንዳያገኙ የሚያደርግ በመሆኑ ብቃት ያላቸውን አትሌቶች ለማፍራት የማያስችል መሆኑ፤

- ፌዴሬሽኑ ከክልል፣ ከዞንና ከወረዳ ስፖርት አመራር አካላት ጋር በመተጋገዝና በመቀናጀት በታዳጊ ወጣቶች የአትሌቲክስ ኘሮጀክቶች ላይ በፕሮጀክት ሰነዱ ላይ በተቀመጠው መሠረት በየጊዜው የክትትል እና የግምገማ ተግባር ባለመከናወኑ፤ የፕሮጀክቱ ዓላማ የተቀመጠውን ሀገርን ወክለው በአህጉርም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሊወዳደሩ የሚችሉ ብቃት ያላቸው ተተኪ አትሌቶች ለማፍራት የሚደረገውን ጥረት ውጤታማነት የሚቀንስ መሆኑ፤
- በክልል የታዳጊ ወጣቶች የአትሌቲክስ ኘሮጀክት ጣቢያዎች የሚሰጠውን የአትሌቲክስ ስፖርት ሥልጠናን ከዓለም አቀፍ የሥልጠና መርሆዎች ጋር አጣጥሞ ለማካሄድ የሚያስችል የታዳጊዎችን የጾታ፣ የዕድሜ እና የአካባቢ ሁኔታ ያገናዘበ የሥልጠና መመሪያ ያልተዘጋጀ ሲሆን፤በተለያዩ ክልሎችና ከተሞች ላይ የተቋቋሙት የታዳጊ ወጣቶች የአትሌቲክስ ኘሮጀክቶች የታዳጊዎቹን ነባዊ ሁኔታ በአገናዘበ መልኩ ሥልጠና እንዳያገኙ የሚያደርግ መሆኑ፤
- በአብዛኛዎቹ የታዳጊ ወጣቶች የሥልጠና ጣቢያዎች ታዳጊ ሠልጣኞች ከሥልጠና ጋር በተያያዘ ለሚያጋጥማቸው ጉዳት የህክምና አገልግሎት የሚያገኙበት ሁኔታ ስላልተመቻቸ፤ ሠልጣኞች በስልጠና ወቅት የአካልም ሆነ የአዕምሮ ጤንነት ችግር ሲያጋጥማቸው በአፋጣኝ የጤና አገልግሎት አለማግኘታቸው ራሣቸውን በብቃት አዘጋጅተው በተለያዩ ውድድሮች ለመቅረብና ለመሣተፍ እንዳይችሉ በተከታታይ ከሥልጠና የመቅረት ብሎም እንዲያቋርጡ የሚያደርግ መሆኑ፤
- በአሠልጣኝነትም ሆነ በየደረጃው በሚገኙ የአመራር ቦታዎችና በIAAF ህግ መሠረት ከሚመረጡ ኮሚቴዎች ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ እንዲጠናከር ተገቢው ትኩረት እንዲሰጠው አለመደረጉ ሴቶች በዘርፉ ሊያበረክቱ የሚችሉትን አስተዋጽኦ በብቃት እንዲያከናውኑ የሚገድብ ከመሆኑም በላይ፣ በዚህ ዙሪያ ሴቶች ለሚያቀርቡአቸው ጥያቄዎች ፍታዊ ምላሽ እንዳያገኙም ተጽዕኖ ማሳደሩ፤

- በፀረ ዶፒንግ /አበረታች መድሐኒቶች/ ኮንቬንሽንን (convention) መሰረት ፌዴሬሽኑ በሚያዘጋጃቸው የሀገር ውስጥ ውድድሮች በሚሳተፉ አትሌቶች ላይ ቁጥጥር የሚረደረግበት ስርዓት እንድዘረጋ አለመደረጉ፤ በፌዴሬሽኑ የሚደረጉ ውድድሮች አለም አቀፍ ይዘት እንዳይኖራቸው ከማድረጉም በላይ ሀገሪቷ የምታፈራቸው አትሌቶች በአለም አቀፍ አትሌቲክስ ውድድሮች ተቀባይነት የሌላቸውን ሁኔታዎች ያልተላመዱ መሆናቸውን በወቅቱ ለመከታተል እና እርምጃ ለመውሰድ የማያስችል መሆኑ፤

- በአትሌቲክስ ስፖርት ዙሪያ በአትሌቶችም ሆነ በሌሎች አካላት የሚነሱ ቅሬታዎችንና የሚቀርቡ ክሶችን የሚሠማ ገለልተኛ አካል (ኮሚቴ) በፌዴሬሽኑ ባለመቋቋሙ፤ በአትሌቲክሱ ዙሪያ በየጊዜው ለሚከሰቱ ችግሮች እና ቅሬታዎች ተቀባይነት ያለው ውሳኔ በዘላቂነት ለመስጠት የማያስችል መሆኑ፤

- ፌዴሬሽኑ በአትሌቲክስ ዙሪያ ሊይዛቸው የሚገቡ መረጃዎች በማንዋል እንጂ በዳታ ቤዝ ያልተያዙ፤ በማንዋል የተያዘውም ቢሆን የመረጃ አያያዙ ግልጽ እና መረጃውን በተፈለገ ወቅት ለማግኘት በሚያስችል መልኩ ስለአልተቀመጠ ፌዴሬሽኑን የሚመለከቱ ማናቸውም መረጃዎች ወቅታዊ እና ዘመናዊ መንገድን በተከተለ እና በተፈለጉ ጊዜ ለማግኘት በሚቻልበት ሁኔታ አለመቀመጣቸው፤

- የአትሌቲክስ ስፖርትን ለማስፋፋትና ተተኪ ወጣቶችን ለማፍራት ፌዴሬሽኑ ባደረገው የብር 2.8 ሚሊየን ድጋፍ በአራት ክልሎች የተጀመሩ የወጣቶች የአትሌቲክስ ማሠልጠኛ ማዕከላት የግንባታ ሥራዎች በታቀደላቸው ወቅት ያልተጠናቀቁ ሲሆን፣ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችም ያልተሟሉላቸው መሆኑ፤

- በየክልሉ በተቋቋሙ የወጣት ማሠልጠኛ ማዕከላትም ሆነ የታዳጊ ወጣቶች ፕሮጀክቶች አካባቢ በተፈጥሮ የተገኙ የስፖርት ማዘውተሪያ ሜዳዎች ያሉ ቢሆንም፤ እነዚህ የተፈጥሮ ሜዳዎች ለአትሌቲክስ ስፖርቱ በሚያስፈልግ መልኩ ማለትም ለተለያዩ የአትሌቲክስ ዘርፎችን (events) በሚያመች ሁኔታ ተስተካክለው የተዘጋጁና ችግሩን ለማቃለል ከባለ ሀብቶች ወይም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ የመሥራት ሁኔታ ትኩረት ያልተሰጠው መሆኑ፤

- ዓለም አቀፍ ደረጃን በጠበቀ ሁኔታ ሊገነባ የታሠበው የሠንዳፋ አትሌቲክስ መንደር ሥራን ለማስጀመር ብር 1.74 ሚሊየን የተመደበ ቢሆንም፤ አጥር ከማጠር ውጪ ምንም እንቅስቃሴ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቀ የአትሌቲክስ መንደር አለመገንባቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሚደረጉ ውድድሮች አትሌቶች ደረጃውን የጠበቀ እና ሳይንሳዊ መንገድን የተከተለ ሥልጠና በማግኘት በስነልቦናም ሆነ በብቃት የተሟሉ ሆነው እንዳይገኙ እና የተለየ ተሰጥኦ ያላቸው አትሌቶች በብዛት ለማፍራት እንዳይቻል ማድረጉ፤
- በተለያዩ ክለቦች የታቀፉ አትሌቶች በትራክ ላይ ልምምድ ባለማድረጋቸው በተለያዩ ውድድሮች ላይ ሲሳተፉ አዲስ መሆን እና ግር መሠኘት እያጋጠማቸው ባለበት ሁኔታ ትራኩ ከተሠራበት ዓላማ ውጪ በሆኑ የተለያዩ ዝግጅቶች ምክንያት በከፍተኛ ሁኔታ እየተጎዳ መሆኑ፤

በመሆኑም ፌዴሬሽኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ወቅታዊ መረጃዎችን በተገቢው መንገድ በመለዋወጥና፤በመተባበር የተጠቀሱትን ችግሮች በማስወገድ አገርቷ በዘርፉ ሊታገኝ የሚገባትን ውጤት ለማሳካት ጥረት ሊያደርግ ይገባል፡፡

4.6 <u>የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት አፈፃፀም እና ውጤታማነትን በተመለከተ</u>

- የትምህርት ሚኒስቴር በከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ዙሪያ በአዋጁ የተሰጠውን ሥልጣንና ኃላፊነት በብቃት እና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማስፈፀም፣ ለመከታተል፣ ለመቆጣጠር እና ተግባራዊነቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል አደረጃጀት ያልዘረጋ መሆኑ፤
- የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ለወጪ መጋራት ሥራ በባለሙያ ደረጃ ባስቀመጠው ሦስት መደብ ላይ የሠው ኃይል ያልመደበ በመሆኑ፣ የወጪ መጋራትን የተመለከቱ ሥራዎችን በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት በተደራቢነት ክፍያ ሊፈጽሙ የሚመጡ ተጠቃሚዎችን ብቻ በማስተናገድ የሚሰራ መሆኑ፤

- ትምህርት ሚኒስቴር በስትራቴጂክ ዕቅዱ ውስጥ ከከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት የሚሰበሰበውን ገንዘብ እንደገቢ ምንጭ ቢያሳይም፣ በዚህ ዙሪያ ሊሠሩ የሚገባቸውን ተግባራት ከስትራቴጂክ ዕቅድ በመመንዘር በዓመታዊ ዕቅዱ እና የዕቅድ ክንውን ሪፖርቱ ውስጥ ያላካተተ መሆኑ፣

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከ1998-2002 ዓ.ም ባወጣው የትምህርት ሴክተር ልማት ፕሮግራም ስትራቴጂክ ዕቅድ ውስጥ የወጪ መጋራትን በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ በማድረግ ከ1999-2002 ዓ.ም. ከወጪ መጋራት በሚገኝ ብር 273,130,000 የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል አቅዶ የነበረ ቢሆንም፣ የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ከ1998-2002 ዓ.ም ከወጪ መጋራት የሰበሰበው ገንዘብ ብር 23,180,384 ብቻ መሆኑ፣

- ተቋማት በደንቡ በተሰጣቸው ሥልጣን እና ኃላፊነት ወሰን መሠረት ግዴታቸውን ሊወጡ እና የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች ያለባቸውን ዕዳ ማጠናቀቃቸውን አረጋግጠው ለቀጣይ ከፍተኛ ትምህርት መቀበል ሲገባቸው፣ በናሙና ከታዩ ተቋማት ውስጥ ግዴታቸውን በክፍያ ሳይወጡ በጎንደር ዩኒቨርሲቲ 6፣ በባህርዳር ዩኒቨርስቲ 10፣ በሀዋሣ ዩንቨርሲቲ 5 እና በዲላ ዩኒቨርስቲ 7 ተጠቃሚዎች የወጪ መጋራት ዕዳን ስለማጠናቀቃቸው ሳይረጋገጥ፣ እንዲሁም የስፖንሰር ሺፕ ደብዳቤ እና ኦፊሻል ትራንስክሪፕት ሣያስዙ ለሁለተኛ ዲግሪ ቀጥለው በመማር ላይ የሚገኙ መሆኑ፣

- በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የወጪ መጋራት ደንብ ከወጣ በኋላ 1515 የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች ካለምንም ክፍያ እና አገልግሎት ዋናውን የትምህርት ማስረጃ ወስደው የተገኙና ከነኝህም ውስጥ 147ቱ የጤና ተመራቂዎች መሆናቸው፣

- የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር የሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት የመግባቢያ ሰነድ (Memorandum of understanding) የሌለው ሲሆን የወጪ መጋራት ክፍያ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶም በቅርንጫፍ መ/ቤቶች እና ውክልና በሰጣቸው ከተማ/ክልል ፋይናንስ ቢሮዎች የወጪ መጋራት ክፍያ መሰብሰቡን እና ፈሠስ

መደረጉን በየ6 ወሩ መከታተል የማይከታተልና ፈሠስ የሚያደርጉለትን እና የማያደርጉለትን ክልሎችም ለይቶ ያልያዘ መሆኑ፤፡

- በናሙና ከታዩ 3 የክልል/ከተማ ገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮና 2 ድርጅቶች ብቻ ከወጪ መጋራት የተሰበሰበውን ብር 10,859,248.66 ለኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ፈሠስ ሳይደረጉ እንደየራሣቸው ክልል ገቢ በመቁጠር ተጠቅመውበት ወይም ፈሠስ የሚያደርግበትን የባንክ ሂሣብ ቁጥር ባለማወቃቸው ገንዘቡ ሥራ ላይ ሳይውል እና ፈሠስ ሳይደረግ በአደራ ወይም በተከፋይ ሂሣብ ይዘውት የሚገኝ መሆኑ፤

- ባለሥልጣኑ የወጪ መጋራት ክፍያን የፈፀሙ/እየፈፀሙ ያሉ ተጠቃሚዎችን፣ የአሠሪ ድርጅቶች፣እንዲሁም የተመራቂ ተማሪዎችን ዝርዝር መረጃ በተሟላ ሁኔታ በዳታ ቤዝ ባለመያዙ በሀገሪቱ ካሉት 22 ተቋማት እስከ 2002 ዓ.ም. ድረስ ያስመረቋቸውን ተጠቃሚዎች ዝርዝር መረጃ በተሟላ ሁኔታ ለባለሥልጣኑ የላኩት 7ቱ ብቻ መሆናቸው፤

- በባለሥልጣኑ የተጠቃሚ ተመራቂዎች ዝርዝር በተሟላ ሁኔታ ባለመያዙ ከአሠሪ ድርጅቶች እና ተጠቃሚዎች የወጪ መጋራት መጠን እና ወርሃዊ ክፍያን በተመለከተ ጥያቄ በሚቀርብለት ጊዜ የተሟላ መረጃ ለመስጠት አስቸጋሪ መሆኑ፤

- አሠሪ ድርጅቶች የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ተጠቃሚ ከሆኑ ሠራተኞቻቸው ደመወዝ በየወሩ 10 በመቶ (1/3ኛ) እየቀነሱ ለኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን መ/ቤት ገቢ ሊያደርጉ ሲገባ፤ በናሙና ተመርጠው ኦዲት የተደረጉ 3 ሚኒስቴር መ/ቤቶች በጠቅላላ የወጪ መጋራት ተጠቃሚ ከሆኑ ሠራተኞቻቸው በደንቡ መሠረት ከደመወዛቸው 10% (1/3ኛ) ተቀናሽ አድርገው ለባሥልጣን መ/ቤቱ ገቢ እንደማያደርጉ፤

- ከነዚሁ መ/ቤቶች ውስጥ የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራትን የመከታተል እና የማስፈጸም ኃላፊነት የተሰጠው ትምህርት ሚኒስቴርም የወጪ መጋራት ከሚመለከታቸው ከሠራተኞቹ ደመወዝ የወጪ መጋራት ክፍያ ተቀናሽ የማያደርግ ሲሆን፣ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የወጪ መጋራት ክፍያ

በሀገር አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ ባለመደረጉ እና ሠራተኞቹ እንዳይለቁ በሚል ከወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች የሰበሰበውን ክፍያ ሂሣብ መልሶ ለተጠቃሚዎቹ ተመላሽ ማድረጉ፤

- የወጪ መጋራትን ለማስፈፀም ሥልጣን እና ኃላፊነት የተሰጣቸው ባለድርሻ አካላት በከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት አፈፃፀም እና በአፈፃፀሙ ዙሪያ ስለሚያጋጥሙ ችግሮች የመወያያ መድረክ በመፍጠር የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ያልተሰራ መሆኑ፤
- ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በየትምህርት ዘመኑ ያቋረጡ እና የተመረቁ የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች ዝርዝርን በተመረቁ በ3 ወራት ውስጥ በአገልግሎት እና ክፍያ ለይተው ለኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን በአብዛኛው ሪፖርት የማያደርጉ በመሆኑ፣
- የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ከ1996 ዓ.ም.ጀምሮ ባለው ጊዜ ውስጥ በ2002 ዓ.ም.በተቋማት ውስጥ የሚገኙ የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎችን አሻራ የሰበሰበ ቢሆንም፤ ከ2002 ዓ.ም.በፊት ለነበሩ ተጠቃሚዎችም ሆነ በ2002 አሻራ ለሰጡ ተማሪዎች የግብር መለያ ቁጥር ያልሰጠ መሆኑ፤
- የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን በኦዲቱ ወቅት ለታዩት ለሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የወጪ መጋራት ክፍያን እንዲሰበስቡ ውክልና የሰጣቸውን የክልል/ከተማ ፋይናንስ አስተዳደር ቢሮዎችን ዝርዝር የማያሳውቅና፣ ውክልና ለሰጣቸው የክልል/ከተማ ፋይናንስ ቢሮዎች በሙሉ ከተቋማት የተላከለትን የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎችን ዝርዝር መረጃ የወጪ መጋራት ከተጀመረበት ከ1996 ዓ.ም.ጀምሮ ኦዲቱ እስከ ተከናወነበት 2003 ዓ.ም.ድረስ ልኮ የማያውቅ መሆኑ፤
- በናሙና ኦዲት ከተደረጉ 11 አሰሪ ድርጅቶች ውስጥ 7ቱ (64%) እና ቃለ-መጠይቅ ከተበተነላቸው 22 አሰሪ ድርጅቶች ውስጥ 10 (45%) በደንቡ እና መመሪያ መሠረት የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ተጠቃሚን በሚቀጥሩበት ጊዜ ከተጠቃሚው፣ ከተመረቀበት ተቋም ወይም ከባለሥልጣን

መ/ቤቱ የሚፈለግበትን የክፍያ ሂሳብ /የአገልግሎት/ ጊዜ የሚገልጽ ማስረጃ የማይጠይቁ መሆኑንና፣ 46 የሚሆኑ አሰሪ ድርጅቶች የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ተጠቃሚ ሠራተኞቻቸውን ዝርዝር በየ3 ወሩ ለባለሥልጣን መ/ቤት የማያሳውቁ መሆኑ፤

በመሆኑም ትምህርት ሚ/ር እና የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፤እንዲሁም ባለድርሻ አካላት ተገቢውን አደረጃጀት ፈጥረው በመንቀሳቀስ ለከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት መራጃ ልውውጥና ገቢ አሰባሰብ ትኩረት በመስጠት በወጡት ሕግ፤ ደንብና መመሪያዎች መሰረት በማስፈጸምና ተግባራዊ ማድረግ ይገባቸዋል፡፡

4.7 በግብርና ሚኒስቴር ፀረ-ተባይ መድኃኒቶች ግዥ፣ አጠባበቅ እና አወጋገድ የተከናወነ

- የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ማከማቻ መጋዘኖች በሚገነቡበት ወቅት ከጠንካራ ማቴሪያሎች (Galvanized iron, cement stone, brick etc) እና የመጋዘኑ ስፋት ከ50 ስኩዌር ሜትር ያላነሠ፣ የመጋዘኑ መሬት ከሲሚንቶ የተሠራ፣ የበሩ መጠን ቢያንስ 3 ሜትር ስፋት X 12 ሜትር ርዝመት፣ ከመሬት እስከጣሪያው ያለው ርዝመት ቢያንስ 3 ሜትር፣ በቂ የአየር ማስገቢያ (Ventilation)፣ የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ መሰጫ እና የእሳት አደጋ መከላከያ አሟልተው መገንባት ሲገባቸው ፤በናሙና ተመርጠው ከታዩት 12 የግል ፀረ-ተባይ ኬሚካል አስመጪ ድርጅቶች፣ የኦሮሚያ እና የደቡብ ክልሎች፣ አማራ ክልሎች፣ 7 ዞኖች እና 18 ወረዳዎች እንዲሁም የሊሙ ኮሳ ቡና ተክል እርሻ ልማት ድርጅት፣ አራት የአበባ እርሻ ድርጅቶች የተጠቀሰውን መስፈርት የማያሟሉ መሆኑ፤
- በናሙና ተመርጠው ከታዩ 12 የግል ፀረ-ተባይ አስመጪ ድርጅቶች፣ በአማራ፣ በኦሮሚያ እና በደቡብ ክልሎች በ7 ዞኖች እና በ18 ወረዳ ግብርና ቢሮዎች የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ማከማቻ መጋዘኖች ሠውና እንስሳት በሚገኙበት አካባቢ የተገነቡ በመሆኑ፤ በህብርተሰቡና በአካባቢ ላይ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል መሆኑ፤

- በናሙና ተመርጠው ከታዩ 12 የግል ፀረ-ተባይ አስመጪ ድርጅቶች፤ የአማራ፣ የኦሮሚያ እና የደቡብ ክልሎች፣ ዞኖች እና ወረዳ ግብርና ቢሮዎች እና የሊሙ ኮሳ ቡና ተክል እርሻ ልማት የፀረ-ተባይ አስመጪዎች እና ተጠቃሚዎች ለሠራተኞቻቸው አስፈላጊውን የመከላከያ ቁሣቁስ አለማሟላታቸው፤

- ለወረርሽኝ አገልግሎት ከውጭ ሀገር የሚገቡትም ሆነ በአዳሚ ቱሉ የፀረ-ተባይ ማደራጃ የሚቀርቡ ፀረ-ተባይ ኬሚካል መያዣ ዕቃዎች ባብዛኛው በበርሜል የሚዘጋጁ በመሆናቸው ፀረ-ተባዩን ለመጠቀም የማቀናነሻ መሣሪያዎች እና የመከላከያ ትጥቅ ባልተሟሉባቸው አካባቢዎች በሠራተኞች ላይ ችግር እየፈጠረ መሆኑን፤

- ለአጠቃቀም አመቺ ያልሆኑ እና የማቀናነሻ መሣሪያዎች ባልተሟሉባቸው አካባቢዎች የፀረ-ተባይ ኬሚካሉን በሚያከፋፍሉ በአንዳንድ የክልል፣ የዞን እና የወረዳ ሠራተኞች ላይ ጤና ጉዳት እያስከተለ መሆኑ ታውቋል፡፡

- በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ የአበባ እርሻዎች መካከል ስኘሪት ፍላወር፣ጐልደን ሮዝ፣ ኦሮሚያ ወንደርስ የፀረ-ተባይ ኬሚካሉን ባህሪ የሚገልጽ ጽሁፍ የአለም የጤና ጥበቃ ድርጅት በወሰነው ምደባ መሠረት አደገኛነቱን የሚያስጠነቅቅ የጽሑፍና ስዕላዊ መግለጫ፣ በአደጋ ጊዜ ሊወሰድ የሚገባውን የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ አሠጣጥ፣ የተመረተበት ቀን እና የአገልግሎት እድሜውን በሚያሳይ መልኩ በፀረ-ተባይ ኬሚካል ማሸጊያዎች ላይ መመሪያው በሚያዘው በአማርኛና በእንግሊዝኛ መፃፍ ሲገባቸው በሌላ ቋንቋ ማለትም በቻይንኛ እና በስዋህሊ ተጽፎመገኘቱ፤

- ማንኛውም በፀረ-ተባይ ኬሚካል በማስመጣት ላይ የተሰማራ ነጋዴ ያልተመዘገበ ፀረ-ተባይ ማምረት፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት መሸጥ ወይም መጠቀም የተከለከለ ቢሆንም፤ ምዝገባ ሳይደረግላቸው ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ የፀረ-ተባይ ኬሚካል አይነቶችን በኦዲት ወቅት ለማጣራት በተደረገው ሂደት ውስጥ እ.ኤ.አ ከ2007 እስከ 2009 ድረስ 125 የፀረ-ተባይ ኬሚካል

አይነቶች በ19 ድርጅቶች 37563 ኪ.ግ እና 87726 ሊትር ሳይመዘገቡ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ መሆኑን፤

- የፀረ-ተባይ የፍቱንነት ሙከራ ሪፖርቶች (Efficacy test) ወጥነት ያሌላቸውና በተለያዩ የምርምር ማዕከላትና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በኩል የሚላኩት የፍቱንነት ማረጋገጫ ሙከራ ሪፖርቶች ወጥነት እንደሌላቸው መሆኑ፤
- የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ወደ ሀገር ውስጥ በብዛት በሚገቡበት ወቅት ናሙና ተወስዶ በቀረበው ናሙና መሠረት የፍቱንነት ደረጃቸው ስለመጠበቁ የላብራቶሪ ፍተሻ እንደማይከናወን፤ ይህንንም ሥራ ሾላ የሚገኘው በእንስሳት እጽዋት ጤናና ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት የኬሚስትሪ ላብራቶሪ የፀረ-ተባይ ውህድ እና ቅሪት ትንተና (Chemical residue and formulation analysis) በዋናነት የሚያከናውን የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ሠዓት ሥራውን ያቋረጠ መሆኑን፤
- ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡበት ወቅት በላብራቶሪ ፍተሻ ባለመደረጉ በብዛት ጥቅም ላይ በሚውሉ በተለይም 2,4-D በመሣሠሉ ምርቶች አስመዝጋቢዎች ለምዝገባ የሚያመጡት ናሙና እና ከተመዘገቡ በኋላ በብዛት ገብተው ወደ አርሶ አደሩ ሲደርሱ ፍቱንነታቸው የመቀነስ ሁኔታ የሚታይባቸው መሆኑ፤
- በአለም የምግብ እና የእርሻ ድርጅት መመሪያ መሠረት ጥቅም የሰጡ የፀረ-ተባይ ኬሚካል መያዣዎች ዳግም ለሌላ ሥራ አገልግሎት መስጠት እንደሌለባቸው፤ ይህን አሠራር ተግባራዊ ለማድረግ በአለም የምግብና የእርሻ ድርጅት ድጋፍ ተገዝቶ በግብርና ሚኒስቴር የፀረ-ተባይ መጋዘን ቅጥር ግቢ ውስጥ ተገጥሞ የነበረው የበርሜል መቆራረጫ (Drum crusher) ኦዲቱ እስከተከናወነበት ወቅት ድረስ ጥቅም ላይ ያልዋለ መሆኑ፤
- ስለፀረ-ተባይ ምዝገባና ቁጥጥር በወጣው አዋጅ ቁጥር 674/2002 መሠረት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተወካይ በፀረ-ተባይ አማካሪ ቦርድ ውስጥ አባል በመሆን፤ የግብርና ሚኒስትሩን ከፀረ-ተባይ አያያዝና አጠቃቀም አኳያ የሚቀረጹ ብሔራዊ ፖሊሲዎችን፣ ደንቦችን፣ መመሪያዎችንና የአገልግሎት ክፍያዎችን በተመለከተ ማማከር፣ እንዲሁም ፀረ-ተባይን የሚመለከቱ

የዓለም ዓቀፍ ስምምነቶችን ከመተግበር አኳያ እና የፀረ-ተባይ ኬሚካል ሥርዓት ውስጥ ማለትም ስለፈቃድ አሰጣጥ፣ የአጠቃቀምና የአወጋገድ ሥርዓትን በተመለከተ በማማከርና በመተባበር መሥራት እንደሚገባው ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በአማካሪ ቦርድ ውስጥ አለመሳተፉ፤ ሊያበረክት ይችል የነበረው አስተዋጽኦ እንዳያበረክት ማድረጉ፤

- የግብርና ሚኒስትር ከአማካሪ ኮሚቴ አባላት ጋር ማለትም የጤና ጥበቃ ሚ/ር፣ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን፣ የጥራትና ደረጃዎች ባለስልጣን፣ የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቱትዩት፣ የብዝሀ ህይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት፣ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ተወካዮች ጋር ተጠያቂነት ሊያጠናክር የሚችል እና ለአማካሪ ኮሚቴው በአዋጅ የተሠጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ ያልተፈራረመ መሆኑ፤
- በአማራ ክልል የግብርና ቢሮ፣ የኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ እና የአምቦ የእጽዋት ጥበቃ ምርምር ማዕከል የተቀናጀ የተባይ መከላከያ ስልትን (Integrated Pest Management) በአሁኑ ወቅት በበቂ ሁኔታ ተግባራዊ እያደረጉ እንዳልሆነና የተቀናጀ የተባይ መከላከያ ስልትን አርሶ አደሮች በስፋት እንዲጠቀሙ ባለመደረጉ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች በአካባቢና በሕብረሰተሰቡ ጤና ላይ ሊያደርሱ የሚችሉትን ጉዳት ለመቀነስ እና በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው ምርት ከማቅረብ አንፃር ሊገኝ ይችል የነበረውን አስተዋጽኦ ሊቀንሰው የሚችል መሆኑ፤
- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የፀረ-ተባይ ፍላጐት ከየክልሎቹ በየአመቱ የሚያሰባስብ ቢሆንም የተሰበሰቡትን መረጃዎች በማጠናቀር ሀገራዊ የፍላጐት ዳሰሳ ጥናት የማያጠናቅርና አስመጪዎችም ሀገራዊ ፍላጐቱን መሠረት ባደረገ መልኩ እንዲያስመጡ ስለማያደርግ አስመጪዎች ከፍላጐት በላይ የውጭ ግዢ በመፈፀም በሀገር ደረጃ አላስፈላጊ የፀረ-ተባይ ኬሚካል ክምችት እንዲኖርና እና አገልግሎት ላይ ሳይውሉ የመጠቀሚያ ጊዜው እንዲያልፍ ሊያደርግ የሚችል መሆኑ፤

- የፀረ-ተባይ ኬሚካል አጠቃላይ መረጃዎች በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በዳታ ቤዝ ሥርዓት ባለመያዛቸው ወደ ሀገር ውስጥ የገቡት፣ በኢትዮጵያ የተመረቱና ጥቅም ላይ የዋሉ የፀረ-ተባይ ኬሚካል አይነቶችን፣ በመንግስና በግል ይዞታ ሥር ባሉ መጋዘኖች የሚገኙ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን፣ በክምችት ወይም በግብይት ሂደት እያሉ ጥቅም ላይ የማይውሉበት ደረጃ የደረሱትን አስመልክቶ ለውሣኔ አሰጣጥ የሚያስፈልገውን ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት የማያስችል መሆኑ፤
- በኦዲቱ ወቅት በአማራ፣ በኦሮሚያ እና በደቡብ ክልል በ7 ዞኖች እና በ18 ወረዳ ግብርና ቢሮዎች በተሰበሰበው መረጃ የትኞቹ የፀረ-ተባይ አይነቶች እገዳ የተጣለባቸው፤ የትኞቹ የፀረ-ተባይ አይነቶች ደግሞ አገልግሎት መስጠት እንደሚገባቸው የሚያውቁበት አሰራር እንደሌለና ከላይ የተጠቀሱት መረጃዎች በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ድረ-ገጽ ያልተለቀቀ መሆኑ፤
- በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እና በተለያዩ ባለድርሻ አካላት መካከል የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን አጠቃቀምና ግብይትን አስመልክቶ የተጠናከረ የመረጃ ሥርዓት አለመኖሩና ህገወጥ የፀረ-ተባይ ኬሚካል ሽያጭን እና ዝውውርን አስመልክቶ የሪፖርቲንግና የግብረ መልስ ሥርዓት ባለመዘርጋቱ፤ በዘርፉ የሚያጋጥሙ የአሠራር ችግሮችን በአፋጣኝ በመለየት ወቅታዊ የመፍትሔ እርምጃ ለመውሰድና ጠቃሚ የፖሊሲ ሀሣቦችን ለመለየት የማያስችል መሆኑ፤
- በግብርና ሚኒስቴር የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ብቃት ደረጃ በየጊዜው የሚፈተሽበት (post registration control) አሠራር የሌለ በመሆኑ፤ ተመዝግበው ጥቅም ላይ የዋሉ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች በሁለት ዓመት አንድ ጊዜ ውጤታማነታቸው አለመገምገሙ ሥራ ላይ ከዋሉ በኋላ የሚጠበቀውን ያክል ውጤት ያስገኙ መሆናቸውን በትክክል ለማረጋገጥ የማያስችል መሆኑ፤
- ለሰብልና ለእጽዋት አገልግሎት ላይ መዋል የማይገባቸው አደገኛ ኬሚካሎች በህገ ወጥ መንገድ ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ከሚመለከታቸው

ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል ባለመደረጉ፤ በአማራ ክልል፣ በኦሮሚያ ክልል፣ በደቡብ ክልል እና በአዳማ ከተማ በአደገኛነቱ የሚታወቀው DDT በግልጽ በገበያ ላይ እንደሚሸጥ እና አርሶ አደሮች ለተባይ መከላከያነት በጫት ማሳዎች፣ በጓያ፣ በበቆሎ፣ በማሽላ እና በሽንብራ ላይ እየቀሙበት በመሆኑ፤ በሕብረተሰቡ ጤና፣ በእንስሳት እና በአካባቢ ላይ እጅግ የከፋ አደጋ ሊያስከትል እና አገሪቱ ወደ ውጭ በምትልካቸው የግብርና ምርቶች ገበያ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያስከትል የሚችል መሆኑ፤

- ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ህገ-ወጥ የፀረ-ተባይ ግብይትን ማስቆምን በተመለከተ፣ በአማራ እና በኦሮሚያ ክልሎች በ7 ዞኖች እና በ18 ወረዳዎች የህገ ወጥ የፀረ-ተባይ ግብይት የቁጥጥር ሥርዓት አለመኖሩን፤ በአዲስ አበባ ከተማ መርካቶ አካባቢ፣ በባህርዳር፣ ሐዋሳ እና በጅማ ከተሞች በሸቀጣሸቀጥ ሱቆች ውስጥ 2,4D የተባለው የፀረ-አረም ኬሚካል በግልጽ የሚሸጥ መሆኑ፤
- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከክልሎች እና ፀረ-ተባይ ወደ ሀገር ውስጥ ከሚያስገቡ ድርጅቶች ጋር የፀረ-ተባይ አያያዝና አጠባበቅን በተመለከተ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ አለመዘጋጀቱ እና በራሪ ጽሑፎችን በማዘጋጀት እንዲደርሳቸው አለማድረጉ የፀረ ተባይ አያያዝና አጠቃቀምን በተመለከተ ተገቢው ግንዛቤ እንዳይኖራቸው አስተዋጽኦ የሚኖረው መሆኑ፤
- ለኦዲት በተመረጡ የግብርና ጽ/ቤቶችና ድርጅቶች የፀረ-ተባይ ኬሚካል መጋዘን ውስጥ ጊዜያቸው ያለፈባቸው (Obsolete) ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ጥቅም ከሚሰጥ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ጋር አንድ ላይ ተከማችቶ የተገኙ ሲሆን፤ ይህም አገልግሎት የሚሰጡትን ኬሚካሎች የአገልግሎት ዘመን እንዲያጥር፣ የፍቱንነት ደረጃም እንዲቀንስ ከመደረጉም በላይ በሰው ጤና ላይ ችግር ሊያስከትል የሚችል መሆኑ፤
- በኦዲት ወቅት መረጃ በተሰበሰበባቸው ክልሎች ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች አያያዝና አጠቃቀምን አስመልክቶ ለሚመለከታቸው

የክልል እና የዞን ግብርና ባለሙያዎች በቂ እና ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ድጋፍ አለማድረጉ፤

- በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የፀረ-ተባይ ኬሚካል ማከማቻ መጋዘን ውስጥ ጊዜው ያለፈበት 9767 ሊትር ማላታይን እና 200 ኪ.ግ የሚጠጋ DDT ደረጃውን ባልጠበቀና ሊወድቅ በደረሰ ቤት ውስጥ፤ እንዲሁም ትምህርት ቤት በአቅራቢያው በሚገኝ አካባቢ ተከማችቶ መገኘቱ፤
- በግብርና ሚኒስቴር የፀረ-ተባይ ኬሚካል ማከማቻ መጋዘን ቅጥር ጊቢ ውስጥ የሚገኙ አገልግሎት የማይሰጡ የፀረ-ተባይ መርጫ መሣሪያዎች እና የተለያዩ ቁሣቁሶች ከፀረ-ተባይ ኬሚካል መጋዘኑ ጀርባ ሜዳ ላይ ተከማችተው እንደሚገኙ፤
- በሁለተኛው ዙር ጊዜያቸው ያለፈባቸውን ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች በመከላከል እና ለማስወገድ እ.ኤ.አ በ24 ኤፕሪል 2003 ፕሮጀክት ቀርጾ ከቤልጂየም መንግስት ጋር ከተፈራረመው $4,070,000 (ዶላር) ውስጥ በወቅቱ ጥቅም ላይ ሳይውል የቀረ ብር 1,211,405.00 ለቤልጂየም መንግስት ተመላሽ ማድረጉ፤

በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበርና በማስተባበር በመፍታት የጸረ-ተባይ ኬሚካሎች በአካባቢውና በህብረተሰቡ ጤና ላይ ጉዳት ሳያደርሱ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቷል፡፡

4.8 <u>በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን የቅርስ ጥናትና ጥበቃን በተመለከተ</u>

- ባለሥልጣኑ የማይዳሰሱ (intangible) ቅርሶች መመዝገቢያ መመሪያ ያዘጋጀ ቢሆንም ለተንቀሳቃሽ እና ለቋሚ ቅርሶች በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥ የሆነ የቅርስ ምዝገባ ለማከናወን የሚያስችል ወጥ የሆነ መመሪያ ባለመውጣቱ የቅርስ አመዘጋገብ ሥራው ጥራቱን የጠበቀ እንዳይሆን ከማድረጉም በላይ ለቀጣይ የቅርስ አጠባበቅ፣ ጥገና እና እንክብካቤ ሥራ ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ መፍጠሩ፤

- በባለሥልጣኑ በኩል ከ1972 ዓ.ም.እስከ 1985 ዓ.ም.ባለው ጊዜ ውስጥ ወደ ሰባ ሺ.ህ የሚጠጉ በተለያዩ ተቋማት እና በግለሰቦች እጅ የሚገኙ የማይንቀሳቀሱ እና ተንቀሳቃሽ ቅርሶች የተመዘገቡበት ሁኔታ ያለ ቢሆንም፤ በባለሥልጣኑ እና በክልሎች መካከል በቅርስ አመዘጋገብ የሥራ ሂደት ላይ ግልጽ የሆነ ኃላፊነት እንዲቀመጥ ባለመደረጉ፤ እንዲሁም ቅርሱን በሚያስተዳድሩ አካላት እና ግለሰቦች የሚደረገው ትብብር አናሳ በመሆኑ ከ1985 ዓ.ም ጀምሮ በባለሥልጣኑ አማካኝነት ተንቀሳቃሽ እና ቋሚ ቅርሶች ላይ ሊደረግ የሚገባው የምዝገባ ሥራ ትኩረት ተሰጥቶት በአግባቡ ያልተከናወኑ መሆኑ፤
- በንጽጽር በቋሚ ቅርሶች ላይ የተሻለ የመለየት እና የመመዝገብ ሥራ ቢከናወንም፤ በተንቀሳቃሽ ቅርሶች ላይ የሚደረገው የምዝገባ ሥራ የተፈለገውን ያህል እንዳልተከናወነና፤ በተለይም በግለሰቦች እጅ ተይዘው የሚገኙ ተንቀሳቃሽ ቅርሶችን የመመዝገብ ተግባር የሚጠበቀውን ያህል አለመሥራቱን፤
- ባለሥልጣኑ በተወሰኑ ክልሎች በማይዳሰሱ ቅርሶች ላይ ምዝገባ ያከናወነ ቢሆንም፤ በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍል ያልተመዘገቡበት ሁኔታና የማይዳሰሱ (intangable) ቅርሶች ምዝገባ በሀገር አቀፍ ደረጃ ሲታይ በአብዛኛው በአንድ ክልል ላይ ማተኮሩ በሌሎች የሀገረቱ አካባቢዎች የሚገኙ የተለያዩ ብሔረሰቦች የማይዳሰሱ ባሕላዊ ቅርሶች ትኩረት አለመስጠቱ፤
- የአርኪዮሎጂ ጥናት ሊከናወንባቸው የሚችሉ ቦታዎች ለምሳሌ ትክል ድንጋዮች የሚገኙባቸውን ቦታዎች የመለየትና የመመዝገብ ሥራ በተወሰነ ደረጃ የተከናወነ ቢሆንም፤ የአርኪዮሎጂ ጥናት እየተከናወነ የሚገኝባቸው ሆኑ ሊከናወንባቸው የሚችሉ ቦታዎች ሙሉ ለሙሉ ተጠንተው እና ተጠናቀው አለመመዝገባቸው፤
- በባለሥልጣኑ የቅርስ ጥገና እና እንክብካቤ መስፈርት ያለው ቢሆንም፤ ከአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ጎንደር ደብረብርሃን ስላሴ በመስፈርቱ መሠረት ቅርስነቱን ጠብቆ በኖራ መታደስ ሲገባው በሲሚንቶና በጭቃ የተጠገነ መሆኑ፤

- ባለሥልጣኑ በቅርሶች ጥበቃ፣ እንክብካቤና ጥገና ዙሪያ በተገልጋዮች ለሚቀርቡ የድጋፍ ጥያቄዎች ወቅታዊ ምላሽ ስለማይሰጥ በዓለም አቀፍ ቅርስነት የተመዘገቡ እና በጎንደር ከተማ እና ዙሪያ የሚገኙ ቋሚ ቅርሶች (አብያተ ክርስቲያናት፣ ገዳማት፣ ቤተ መንግስታት) ጉዳት እየደረሰባቸው መሆኑ፤

- የቅርስ የላብራቶሪ አጠቃቀም መመሪያ ባለመኖሩ በላቦራቶሪ ውስጥ መከናወን ያለባቸውን የተጠቃሚዎች ሥርዓት እና ደንብ፤ እንዲሁም የላብራቶሪ ተጠቃሚዎች ክፍያ በአግባቡ ህግ እና ደንብን ተከትለው እንዳይከናወኑ ሊያደርግ የሚችል መሆኑ፤

- በሙዚየሞች መካከል ለሚደረጉ የቅርሶች ውሰት መመሪያ ጸድቆ ሥራ ላይ እንዲውል አለመደረጉ በሙዝየሞች መካከል የሚደረጉ የቅርስ ዝውውር ተግባራት አስፈላጊውን ደረጃ ጠብቆ እንዳይከናወን፣ በቅርሶች ውሰት እና አመላለስ ወቅት ቅርሶችን ለጉዳት እና ለስርቆት እንዲጋለጡ፣ ከዚህም በተጨማሪ የሙዚየም ባለሙያዎች ብልሹ አሠራር እና ተጠያቂነት ያልሰፈነበት ተግባር እንዲያከናውኑ በር የሚከፍት መሆኑ፤

- በአንዳንድ ክልሎች ከባለስልጣን መ/ቤቱ ፍቃድ ሳያገኙ በቅርሶች ላይ ጥገና የሚደረግበት ሁኔታ መኖሩንና ይህን ባደረጉ አካላት ላይ ክትትል በማድረግ ይህ ጎጂ ተግባር እንዳይበረታታ ተገቢ የማስተማሪያ እርምጃ አለመወሰዱን፤

- ለቅርስ ጥበቃ ተገቢው ትኩረት ባለመሰጠቱ እና በቅርስ አጠባበቅ ዙሪያ ለሚቀርብ የድጋፍ ጥያቄ ወቅታዊ ምላሽ ባለማግኘቱ ብዛት ያላቸው ቅርሶች ለጥፋት የተጋለጡበት ሁኔታ መታየቱ፤

- በዓለም አቀፍ ቅርስነት ለተመዘገበው (ፋሲል ግቢ) የቅርስ አስተዳደር ሰነድ ቢዘጋጅም ያልፀደቀ መሆኑን፣ ለተቀሩት ዓለም አቀፍ የቅርስ ቦታዎች የአስተዳደር ሰነድ (site management plan) ያልተዘጋጀ መሆኑን፤

- በዓለምአቀፍ ቅርስነት ለመያዝ እንደ አንድ ዋነኛ መስፈርት የሚታየው የቅርስ ቦታዎች አስተዳደር ሰነድ አለመኖር፤በሀገሪቷ በዓለም አቀፍ

ቅርስነት ተመዝግበው የሚገኙ የአስተዳደር ሰነድ ያልተሠራላቸውን ቅርሶችን ከዓለም አቀፍ ቅርስነት ሊሰረዙ የሚችሉ ቅርሶች ዝርዝር (endangerd list) ውስጥ እንዲገቡ ሊያደርጋቸው የሚችል መሆኑ፤

- ቅርሶችን መስለው ከሚሸጡ ዕቃዎች ጀርባ ትክክለኛ ቅርሶች ሊሸጡ የሚችሉበት ሁኔታ የሰፋ ከመሆኑም በላይ በስጦታ ወደ ውጭ ሀገር የሚሄዱ እቃዎች ላይ የክትትል እና የቁጥጥር ስርዓት አለመኖሩ፤
- በአርኪዮሎጂ ቦታዎች ላይ የቅርስ ጥናት ከሚያደርጉ አካላት ጋር ከአርኪዮሎጂ ሙያ ጋር ተያያዥ ልምድ የሌለው ሠራተኛ የሚመደብበት ሁኔታ በመኖሩ፤ የአርኪዮሎጂ ጥናት ከሚያካሂዱ ቡድኖች ጋር የሚሄዱ ሠራተኞች ከአርኪዮሎጂ ጥናት ጋር ተያያዥ የሆነ ሙያ ከሌላቸው ወይም ተገቢው ሥልጠና ካልተሰጣቸው ተገቢውን የመስክ ቁጥጥርና ክትትል ለማድረግ የማይችሉ መሆኑ፤
- ከጥናትና ምርምር ባለሙያዎች ከሚገኘው አሥር በመቶ ገቢ ውስጥ ሃምሣ በመቶ ለቅርሱ ቦታ ማልሚያ እንዲውል መመሪያ ቢኖርም፤ ገቢው ለክልሎቹ የማይላክ እና ጠቅላላ የተሰበሰበው አስር በመቶ ባለስልጣኑ የሚያስቀር በመሆኑ፤ከቅርስ ጥናትና ምርምር የሚገኝ ገቢ ለቅርስ ጥበቃ፤ ጥገናና ልማት ካልዋለ በጥበቃና ጥገና እጦት ትልልቅ ቅርሶችን ሙሉ ለሙሉ ወደ ማጣት ሊያመራ የሚችል መሆኑ፤
- የሀገሪቱን ቅርሶች በአግባቡ ለመመዝገብ፣ ለመጠበቅ፣ ለመንከባከብ እና ለማልማት እንዲቻል የባለድርሻ አካላት ዝርዝር በቅርቡ በተጠናው የመሠረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ላይ የተቀመጠ ቢሆንም፤ ኃላፊነት እና ተግባራቸው በጥናት በግልጽ ተለይቶ እንዲያውቁት አለመደረጉ፤ በቅርሶች ላይ እየደረሰ ያለውን ጥፋትና ምዝበራ ለማስወገድ ባለድርሻ አካላት የበኩላቸውን እንዳይወጡ ሊያደርግ የሚችል መሆኑ፤
- ባለስልጣኑ እና ክልሎች በቅርስ አመዘጋገብ፤ አጠባበቅ እና ጥገና ላይ ያላቸው የሥራ ድርሻ በግልፅ ባለመቀመጡ፤ የተቀናጀ ሥራ ለማከናወን እንዳይቻል የሚያደርግና በቅርሶች ዙሪያ ሊሠሩ የሚገቡ ሥራዎች በወቅቱ

እንዳይሠሩ እና ባለቤት እንዲያጡ በማድረግ ለብልሽት እና ለጥፋት የሚያጋልር መሆኑ፣

- የባለስልጣኑ አዋጅ ቁጥር 209/92 አንቀፅ 45 ንዑስ አንቀፅ 2 ላይ የቅርስ ዝርፊያ ለሚፈፅሙ ዘራፊዎች የተለያየ ቅጣት የተደነገገ ቢሆንም፣ ይህ ተግባራዊ አለመደረጉ፣
- ቅርሶች ለምዝበራና ለጥፋት የሚጋለጡበትን ሁኔታ ለመቀነስ ባለስልጣኑ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ወጥ የሆነ መርሐ ግብር ነድፎ በጋራ ባለመስራቱ እና የቅርስ ጥፋትና ምዝብራ ለሚፈፅሙ ዘራፊዎች በአዋጅ ላይ መሰረት ተግባራዊ ባለማድረጉ የቅርስ ዝርፊያ ከቀን ወደ ቀን እየተባባሰ እንዲሄድማድረጉ፣
- በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ስር ከሚገኘው ከዱር እንስሳት ባለስልጣን ጋር ባለስልጣን መ/ቤቱ የሚያከናውኑቸው ተግባሮች ተያያዥነት ያላቸው ከመሆኑ አንፃር የጋራ ዓላማቸውን ለመወጣት በተቀናጀ መልኩ አብሮ የመሥራት ሁኔታ አለመኖሩ ዓላማቸውን በብቃት ለማሳካት እንዳይቻል ተጽዕኖ ማሳደሩ፣
- በባለሥልጣኑ ለክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች በየደረጃው በቅርሶች ዙሪያ ለሚደረጉ ማንኛውም ሥራዎች የሙያ ድጋፍና ስልጠናዎች በተሟላ መልኩ ባለመስጠቱ፣
- በሃይማኖት ተቋማት ያሉ ውድና ልዩ የሆኑ ቅርሶች ለመጠበቅ የሚመደቡት ሠራተኞች በሙያው ስልጠና የሌላቸው መሆኑ፣ በተጨማሪ ቅርሶች በቂ እውቀት በሌላቸው ሠራተኞች አግባብ ባለው መንገድ ባለመቀመጣቸው እና ባለመጠበቃቸው የመበላሸትና የመጥፋት እድል ሊያጋጥማቸው የሚችል መሆኑ፣
- በባህልና ቱሪዝም ሚ/ር የቅርስ ደረጃ ምደባ ደንብ መስፈርቶችን ማሻሻያ እና የማስፈፀሚያ መመሪያ እንዲጸድቅ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት የቀረበ ቢሆንም፣ ባለመፅደቁ የቅርስ ደረጃ ማውጣት ተግባር ያልተከናወነና የቅርሶች ደረጃ ባለመለየቱ በፌዴራል፣ በክልል፣ በዞን ወዘተ... በየደረጃው

የሚገኙ የቅርስ ባለቤቶች ያለባቸውን የስራ ድርሻ ኃላፊነት እንዲያውቁት ባለማድረጉ ቅርሶችን የመጠበቅና የመንከባከብ ተግባር በየደረጃው ባሉ አካላት በብቃት እንዳይከናወን እና ተጠያቂነት እንዳይጠናከር ማድረጉ፤

- ማንኛውም የልማት ሥራ ከመካሄዱ በፊት በቅርስ ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት በባለስልጣኑ በኩል የቅርስ ማዳን ሥራ እንደማይሠራና ለቅርስ ማዳን ስራ የአካባቢ የስጋት ግምገማ (Enviromental impact assessment) ስለማይከናወን ያልታወቁ እና የጎላ ጠቀሜታ ሊኖራቸው የሚችሉ በርካታ ቅርሶች ሊወድሙ የሚችሉ መሆኑ፤
- የቅርስ ጥገና እና እንክብካቤ ለሚያደርጉ ባለሙያዎች የሚሆን የሙያ ስነ ምግባር ደንብ የባለስልጣኑን እና የሀገሪቷን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ያለመዘጋጀቱ፤ ባለሙያዎቹ ተጠያቂነት የሰፈነበት ሥራ እንዳይሠሩ የሚያደርግ መሆኑ፤
- ቅርሶች የሚገኙባቸው የዕምነት ቦታዎች ያላቸውን የቅርስ ብዛት በውል የማይታወቅ ሲሆን፣ መረጃቸው በአግባቡ ስለማይያዝ፤ የተመዘገቡ ተንቀሳቃሽና ቋሚ ቅርሶችን መረጃ ሊይዙ የሚገባቸው አካላት በሙሉ በቅጅ እንዲደርሳቸው አለመደረጉን እና መረጃውን በአግባቡ ሊይዙ የሚችሉበት ሁኔታ አለመመቻቸቱ፤
- ክልሎች ከባለስልጣኑ የመረጃ ቋት ጋር በኔት ወርክ ባለመገናኘታቸው ባለስልጣኑ የቅርሶችን ደህንነት ለመከታተልና ለመቆጣጠር፤እንዲሁም የመረጃ ልውውጥንና ፍሰቱን የተቀላጠፈና ዘመናዊ እንዳይሆን ማድረጉ፤
- የሰሜን ጎንደር ዞን፤ የጌዲዮ እና የባሌ ዞኖች ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤቶች በፌዴራል ደረጃ ቅርስን በሚመለከት የተዘጋጁ ጥናቶች፣ ብሮሸሮች፣ መጽሔቶች ወዘተ እንደማይደርሳቸው የገለጹ ሲሆን፣ በኦሮሚያና በአማራ ክልል የሚላክላቸው ክልሎቹ ካለቸው የዞንና የወረዳ ቁጥር ጋር የማይመጣጠን በመሆኑ ለሁሉም ለማዳረስ አለመቻሉ፤
- በሀገር አቀፍ ደረጃ የተደራጀ እና የቅርስ መረጃዎችን በብቃት ለመለዋወጥ የሚያስችል የድረ-ገፅ አለመኖር ቅርሶችን በአግባቡ መዝግቦ ለመያዝ፣

ለመጠበቅ እና ለማስተዋወቅ እንዲሁም ቅርስ ነክ መረጃዎችን ለሚፈልጉ አካላት የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት የማያስችል መሆኑ፤ ይህንንም በተመለከተ የባለስልጣኑ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና የመረጃ ስርዓት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው ከሶስት ወራት በኋላ እንደሚቋቋም ገልፀዋል፡፡

በመሆኑም ባለስልጣን መ/ቤቱ በቅርስ ዙሪያ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ወጥ የሆነ የመረጃ ልውውጥ በማድረግና በቅንጅት በመስረት ቅርሶች የሚመዘገቡበት፤የሚጠበቁበትና እንክብካቤ የሚያገኙበት ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡

4.9 <u>በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ግዥ አፈጻጸም እና ንብረት አስተዳደርን በተመለከተ</u>

- ኮርፖሬሽኑ የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ (BPR) ጥናትና በ IPA (the consultant) በተባለ የውጭ ድርጅት የኮርፖሬሽኑ አደረጃጀትና ገፅታ የተጠና ቢሆንም፤ ጥናቶችን መሰረት ያደረገ የግዥና የንብረት አስተዳደር መመሪያና ፕሮሲጀር ተዘጋጅቶ እና ተግባራዊ አለማድረጉ ላወጣው ወጪ ተገቢውን ግልጋሎት (value for money) ያላገኘ መሆኑ፤
- የኮርፖሬሽኑ ማኔጅመንት ኃላፊዎችን አስተዳደራዊ ጉዳይ ለመወሰን የሚያገለግል መመሪያ፤ እንዲሁም በኮርፖሬሽኑ የሚቋቋሙ የግዥ፣ የግምገማ እና የክሌም ኮሚቴዎች የሚቋቋሙበት በተጨማሪም የመግባቢያ ሰነድ ለመፈረም የሚያስችል ግልፅ የሆነ መመሪያ ተዘጋጅቶና ተግባራዊ ተደርጎ ያልተገኘ መሆኑ፤
- በዚህም ምክንያት በኮርፖሬሽኑ ውስጥ በኃላፊነት የሚሰሩ ሰራተኞች ለሚፈፅሙት ጥፋቶች አስተዳደራዊ እርምጃ ለመውሰድ እና በየእርከኑ ተጠያቂነትን ለማስፈን ያልተቻለ መሆኑ፤
- በኮርፖሬሽኑ የሚፈፀሙ ቋሚና አላቂ እንዲሁም የአገልግሎትና የፕሮጀክት ግዥዎች ከመፈፀሙ በፊት የመግባቢያ ሰነድ (MOU) ሲፈረም ለቦርድ ቀርቦ የሚጸድቅ ቢሆንም ለነፃ ውድድር ዝግ መሆኑ፤

- በኮርፖሬሽኑ በናሙና በታዩት ስምንት ግዥ ፈፃሚዎች የሚፈጸሙ ግዥዎች በሙሉ በእቅድ (procurement plan) ላይ ያልተመሰረቱና ግዢዎች በየጊዜው በተነጣጠለ ሁኔታ በዋጋ መሰብሰቢያ (ፕሮፎርማ) በ2002 በድምሩ ብር 25,067,961.72 የተገዛ መሆኑ፤
- ኮርፖሬሽኑ የገበያ ጥናት በማድረግ፣ የገበያ መረጃ (data base) እና ወቅታዊ የሆነ የመሀንዲስ ግምት በመከተል የዋጋ ክለሳ ስለማያደርግ በናሙና ከታዩት የሪጅን ግዥዎች ድሬደዋ፣ሀዋሳና ጅማ ከአልባሳት በስተቀር በጥቅል ግዥ የማይፈፀም መሆኑና በየስራ ክፍሎቹም የጥቅል ግዥ አለመኖሩ፤
- የጨረታ ሰነድ ሲዘጋጅ ይዘቱ፣ በግምገማ ወቅት ግልፅ የመወዳደሪያ መስፈርት እና የነጥብ አሰጣጥ ስርአት ሊኖር፣ የጨረታ ሰነዱን እና የግምገማ ውጤቱ ወጥነቱንና በገለልተኛ ገምጋሚ ቡድን መሰራቱን፣ በተወሰነ የጊዜ ገደብ መሰረት መከናወኑንም የሚከታተል የጨረታ ጥራት አረጋጋጭ ቡድን (tender quality assurance team) መቋቋም፤ እንዲሁም የጨረታ ማስታወቂያና ውጤቱ በወቅቱ በመገናኛ ብዙኃንና በታወቁ ድረ-ገፆች መለቀቅ ይኖርበታል፡፡
- የጨረታ ሰነድ ሲዘጋጅ ይዘቱን እና ግልፅ የመወዳደሪያ መስፈርት፣የነጥብ አሰጣጥ ስርአቱ ወጥነት በየጊዜው የማይከለስ እና የጨረታ ሰነድ ገምጋሚ ኮሚቴ አባላት ከግዥው ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያላቸው የፕሮጀክት ማኔጅመንት አባላት በተደጋጋሚ የሚመደቡ መሆኑ፤
- በኮርፖሬሽኑ የሚፈፀሙ ቋሚና አላቂ እንዲሁም የአገልግሎትና የፕሮጀክት ግዥዎች በታቀደላቸው የጊዜ ገደብ፣ የገንዘብ መጠንና የጥራት ደረጃ መሰረት መፈፀም ሲገባ 10 የአገር አቀፍ የኤሌክትሪክ አቅርቦት ፕሮግራም (UEAP) ግዥዎች ውስጥ 4ቱ ከ2ወር እስከ 7ወር መዘግየታቸው በዚህም ምክንያት የ2000 እና 2001 የአገር አቀፍ የኤሌክትሪክ አቅርቦት ፕሮግራም (UEAP) እቅድ ክንውን 69% እና 62.2% ብቻ መሆኑ፤
- የግልገል ጊቤ II በevent 19 ምክንያት ለ18 ወራት መዘግየቱና የ23.5 ሚሊዮን ዩሮ ተጨማሪ ወጪ ማስከተሉ እና IPA የተባለ ድርጅት

በ627,495 ፓውንድ የኮርፖሬሽኑን የወደፊት ገፅታ እንዲያጠና የተቀጠረ ቢሆንም የጥናቱ ሪፖርት ሳያልቅ እና ተግባር ላይ ሳይውል ክፍያ 50% 313,747.50 ፓውንድ ተከፍሎ ኮንትራቱ መቋረጡ፤

- የቅድመ ክፍያ ቆጣሪ (Prepaid meter) ለ50 ሺህ ደንበኞች አገልግሎት እየሰጠ ቢሆንም ካለበት ችግር ውስጥ የsystem soft ware ዋና ቁልፍ (data base key) በአቅራቢው ድርጅት በ El-sewedy (የግብፅ ኩባንያ) እጅ በመሆናቸው ችግሮች ሲከሰቱ ባለሞያዎች ከግብፅ አገር እየመጡ ችግሩን ለመፍታት እንደሚሞክሩ፣ ሂደቱ ረጅም ጊዜና ከፍተኛ ወጪ የሚያስከትል መሆኑ፤
- በናሙና ተመርጠው ከታዩ 14 ግዥዎች ውስጥ በሁሉም ግዥው ከመፈፀሙ በፊት የዕቃዎች ጥራት ለማረጋገጥ ለቴስት ዊትነስ ወደተለያዩ አገራት የሚሄዱ ሰራተኞች ዕቃዎቹ ተገዝተው ንብረት ክፍል ገቢ በሚሆኑበት ወቅት በታየው ስታንዳርድ መሰረት ገቢ መሆናቸውን የማያረጋግጡ በመሆኑ፤
- በኮርፖሬሽኑ ተገዝተው የገቡ ጥራት የጎደላቸው ዋጋቸውም 21,348,320 USD የሆነ 3,384 የዲስትርቢውሽን ትራንስፎርመሮች በጎፋ፣ በድሬዳዋ፣ ሻሸመኔ፣ ባህርዳር እና ግልገል ጊቤ መኖራቸው፤
- በጎፋ የማርኬቲንግና ሽያጭ ስቶር ብዛታቸው 11,374 የሆኑ 100/5A ከረንት ትራንስፎርመሮች በላብራቶሪ ተመርምረው አገልግሎት ላይ ሲውሉ 200/5A በመሆናቸው የኮርፖሬሽኑን ገቢ በግማሽ ያህል የሚቀንሱ በመሆኑ አገልግሎት ላይ እንዳይውሉ መደረጉ፤
- እቃዎች በወቅቱ ባለመቅረባቸው ምክንያት ለደረሰ ኪሳራ (liquidity damage) በወቅቱ ክትትል ተደርጎ ክፍያ የማይጠየቅ በመሆኑ፤ በናሙና ከተመረጡት 10 የአገር አቀፍ የኤሌክትሪክ አቅርቦት ፕሮግራም (UEAP) ግዥዎች ውስጥ 4ቱ ከ2ወር እስከ 7ወር ስለዘገዩ እቃዎቹ በወቅቱ ባለመቅረባቸው ለደረሰው ኪሳራ (liquidity damage) ያልተሰበሰበ ሂሳብ በብር 1,058,135.63 እና በUSD 874,755.40 በወቅቱ ያልተጠየቀና ያልተሰበሰበ መኖሩ፤

- በኮርፖሬሽኑ የቋሚና አላቂ ንብረቶችን ለመጠበቅ፣ ለመጠቀም እና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ መመሪያዎችና ፕሮሲጀሮች የተዘጋጁ ቢሆንም፣ በአግባቡ ስራ ላይ የማይውሉ እና በተወሰነ ጊዜ ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር ለማጣጣም እንዲቻል የክለሳ ስራ የማይሰራ መሆኑ፤

- በናሙና በታዩት አስራ ሁለት ዕቃ ግምጃ ቤቶች ቋሚ ንብረቶች ተዝረክርከው፣ ዝገው፣ ተሰባብረውና፣ በአፈርና በሳር ተሸፍነው የተገኙ፤ እንዲሁም በናሙና በታዩት በሁሉም ዕቃ ግምጃ ቤቶች ከፍተኛና ዝቅተኛ የክምችት መጠን ተወስኖ ተግባራዊ ያለመሆኑ፤

- የኮርፖሬሽኑ የስራ ክፍሎችና ፕሮጀክቶች የዕቃ አቅርቦት ከስራ ዕቅድ ጋር የተመጣጠነ ባለመሆኑ በየዕቃ ግምጃ ቤቶችና ፕሮጀክቶች አዳዲስ ዕቃዎች ሆነው አገልግሎት የማይሰጡ (Obsolete) ንብረቶች በአሰብ ወደብ በኩል ከጃፓኒዝ ኤይድ የተገኙ 8,633 የኤሌክትሪክ ቆጣሪ በጎፋ ዕቃ ግ/ቤት ያለ አገልግሎት ተቀምጠው መገኘታቸው፤

- በናሙና በታዩት አስራ ሁለት ዕቃ ግምጃ ቤቶች ውስጥ በጎፋ፣ በድሬዳዋ፣ ሻሸመኔ፣ ሀዋሳ በሚገኙ ዕቃ ግምጃ ቤቶች በመጋዘን ውስጥ ሊቀመጡ የማይችሉ ንብረቶች ለፀሀይ፣ ለዝናብና ለአፈር ተጋልጠው እና በግቢው ውስጥ ተዝረክርከው ቢጠፉ እንኳን በማይታወቅበት ሁኔታ ሳር በቅሎባቸውና አቧራ ለብሰው ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

- በጎፋ ዕቃ ግ/ቤት ብዛቱ 164 በርሜል ዋጋው ብር 1,640,000 የሆነ ኢንጂን ኦይል በአንድ ጥግ በግቢው ውስጥ ተቀምጦ መገኘቱ፤

- በኮተቤ ዕቃ ግ/ቤት በሰውና በአካባቢ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ የመቀጣጠል፣ የመፈንዳት፣ የመትነን እና መርዛማነት ያላቸው አሞንያ ሶሊሽን እና ሰልፈሪክ አሲድ ጉዳት በሚያደርስ መልኩ ከሌሎች ንብረቶች ጋር ተቀላቅሎ ተቀምጠው መገኘታቸው፤

- በጎፋ የነዳጅ ዲፖዎችና መኖሪያ ቤቶች በጣም በተቀራረበና ለአደጋ በሚያጋልጥ መልኩ የሚገኙ መሆኑ፣ በሻሸመኔ ኬሚካል የመጣባቸው

በርሜሎች እንደማይወገዱና የተቀቀሉ ምሰሶዎች በክረምት ወቅት ኬሚካላቸው እየታጠበ ወደ አካባቢው የሚፈስ መሆኑ፤

- በኮርፖሬሽኑ ከታዩት ዕቃ ግምጃ ቤቶች ውስጥ ስምንቱ (66%) ንብረቶች በዓይነታቸው ተለይተው ያልተቀመጡ መሆናቸው፣ ዕቃዎችን ለማስወጣትና ለማስገባት የሚረዱ መሳሪያዎች፣ ለጥንቃቄ የሚረዱ ፅሁፎች (ምልክቶች)፣ የእሳት አደጋ መከላከያ መሳሪያዎች በተገቢው ቦታ ተሟልተው እና ተቀምጠው አለመገኘታቸው፤
- የጥበቃ ሠራተኞች ለስራቸው የሚገለገሉባቸው መሳሪያዎች ዘመናዊ ያልሆኑ መሆናቸው የጥበቃ ማማ፣ የመገናኛና የጦር መሳሪያ ያልተሟሉ እና ተገቢው ፍተሻ የማይደረግ መሆኑን፤
- ከፕሮጀክቶችም ሆነ ከተለያዩ የስራ ክፍሎች ተመላሽ የሚደረጉ ንብረቶች በተመላሽ ሰነድ ቢመለሱም በአመታዊ የንብረት ቆጠራ እንደማይካተቱና አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉና የማይችሉ ተብለው አለመለየታቸው፤
- በኮተቤ የትራንስሚሽን ሰብስቴሽን ኮንስትራክሽን ዕቃ ግምጃ ቤት ከፕሮጀክት የተመለሱ አዳዲስ ዕቃዎች በዕቃ መመለሻ ሰነድ ገቢ ቢሆኑም፤ የፋይናንስ ኮፒ ወደ ሂሳብ ክፍል ሳይላክ በዕቃ ግምጃ ቤት ኃላፊው እጅ መገኘታቸው፣ የቁጥጥር ስርዓቱ የላላ መሆኑ፤
- በተሽከርካሪዎች ጥገና ክፍል በእድሳት ምክንያት የተቀየሩ ዕቃዎች በአግባቡ ተይዘው ወደ ዕቃ ግምጃ ቤት ገቢ የማይደረጉ መሆኑን፣
- በምዕራብ አዲስ አበባ ሪጅን በመስመር ማዞሪያ ስራ ወቅት የነበሩ ግምታቸው ከብር 2,814,172.84 በላይ የሆነ የመዳብ ሽቦ ፤እንዲሁም ግምታቸው ከብር 491,829.57 የሆኑ ብዛታቸው 279 የሆኑ ሶዲየም ላምፖች እስከነተዛማጅ ዕቃዎቻቸው ወደ ዕቃ ግምጃ ቤት ሳይመለሱ በመቅረታቸው ኮርፖሬሽኑ በጠቅላላ ከብር 3,306,002.41 በላይ ማጣቱ፤
- በምዕራብ አዲስ አበባ ዲስትሪቢዩሽን እና አገልግሎት መስጫ ማዕከላት መረጃዎች በአግባቡ አለመያዛቸውና ስራዎችን ኃላፊነት ወስዶ የሠራቸውን

ሠራተኛ የሚገልፅ ሰነድና መረጃ ባለመኖሩ ተጠያቂውን ማስቀመጥ አለመቻሉ፤

- ኮርፖሬሽኑ በዝውውር፣ በስጦታና በእርዳታ ያገኛቸውን ንብረቶች ከተረከበበት ቀን ጀምሮ ዋጋቸው ተተምኖ የንብረት ገቢ ደረሰኝ እንደማይቆረጥላቸው እና ተከታታይነታቸውን ለመጠበቅ የሚያስችል የንብረት ቁጥር (tag number) እንደማይሰጣቸው፤
- በኮተቤ ዕቃ ግምጃ ቤት ከጣሊያን መንግስት በስጦታ የተገኘ ከሃያ ዓመት በላይ የሆነው ንብረት ዋጋው ተተምኖ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥለት እንዲሁም ሳይከፈት የሚገኝ መሆኑ፤
- በናሙና ከታዩት አስራ ሁለት ዕቃ ግ/ቤቶች በሁለቱ ማለትም በድሬዳዋ እና በጨርቆስ (አሰበተፈሪ) በቋሚ ንብረት መመዝገቢያ ካርዱ የወሰደውን አካል የማያመለክትና የንብረት መለያ ቁጥር የማይገልፅ መሆኑ፤
- በኮርፖሬሽኑ ግዥ ተከናውኖ በርክክብ ወቅት ግልፅ በሆኑ ችግሮች ምክንያት ለደረሰ ኪሳራ በውሉ መሰረት ተገቢው እርምጃ የሚወሰድ ሲሆን፣ ከሚታየው ጉድለት ውጭ ቴክኒካል ችግሮች ሲኖር በባለሞያ ተረጋግጦ እርምጃ እንደማይወሰድ፤
- የማሸጊያ እቃዎች በኮንትራቱ ላይ የሚገለፁ ቢሆንም ደረጃቸውን ያልጠበቁ፣ በቀላሉ የተሰባበሩ የማሸጊያ እቃዎች እና የእንጨት ድራም በድሬዳዋ፣ በጎፋ፣ በኮተቤ እና በካራቆሬ ዕቃ ግምጃ ቤቶች መኖራቸው፤
- በናሙና በታዩት በሁሉም ዕቃ ግ/ቤቶች የተገዙ ንብረቶች በርክክብ ወቅት በባለሞያ እንደማይረጋገጥ እንዲሁም በኮተቤ፣ በጎፋ፣ በካራቆሬ፣ በድሬዳዋ፣ በሀዋሳ፣ በጅማ እና በሻሸመኔ እቃ ግ/ቤቶች የማሸጊያ እቃዎቻቸው የተሰባበሩ እና የተዝረከረኩ እቃዎች መኖራቸው፤
- የኮርፖሬሽኑ ቋሚ ንብረቶች አስፈላጊው የመድህን ዋስትና ሽፋን በተሟላ ሁኔታ የተገባላቸው አለመሆኑ እና የመድህን ዋስትና የተገባላቸውም የንብረቶችን ዋጋ ያላገናዘበ ወይንም በጥናት ያልተደገፈ መሆኑን፤

- የመድህን ዋስትና ሊገባላቸው የሚገባ በኮርፖሬሽኑ አገልግሎት በመስጠት ላይ ያሉ ንብረቶች መሆን ሲገባቸው የሠሌዳ ቁጥር 4-06933 የሆነ በ1998 ዓ.ም በጨረታ የተሸጠ አንድ ከባድ ስካኒያ ተሽከርካሪ በ2001 እና በ2002 ዓ.ም የመድን ዋስትና ሽፋን ተገብቶለት የተገኘና ለዚህም ተጠያቂ የሆነ አካል (የስራ ሃላፊ) አለመኖሩ፤

- በኮርፖሬሽኑ ይዞታ ስር የሚገኙ ተሽከርካሪዎች በዝርዝር ተለይተው በትራንስፖርት ክፍል የማይታወቁና የመድህን ዋስትና ሽፋን በመረጃና በጥናት ላይ የተመረኮዘ ባለመሆኑ ኮርፖሬሽኑ አለአግባብ ለሆነ ወጪ የዳረገው መሆኑ፤

- በኮርፖሬሽኑ የሚገኙ ተሽከርካሪዎችና ተንቀሳቃሽ ማሽነሪዎች ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል አደረጃጀትና መመሪያ የሌለ መሆኑ፣

- የተሽከርካሪ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር (ሊብሬ) ፤እንዲሁም የህይወት ታሪካቸውን የሚገልፅ መረጃ በትራንስፖርት ክፍል ተሟልቶ ያልተገኘ እና በኮርፖሬሽኑ አሰራር መሰረት አደጋ በደረሰ በ24 ሰዓት ውስጥ ሪፖርት ስለማይደረግ፤ ንብረቶቹን ለመቆጣጠር እና ለመከታከል የሚያስችል በቂ የሆነ መረጃ እንዳይኖርና ያሉበትን ሁኔታ በአግባቡ ለመከታተልና ለመቆጣጠር የማያስችል መሆኑ፤

- ለኃይል ማመንጫነት ከሚውሉ ጀኔሬተሮች በናሙና ተመርጠው ከታዩት 3 የኃይል ማመንጫ ጀኔሬተሮች ውስጥ ቃሊቲ የሚገኘው የዲዝል ኃይል ማመንጫ 14.0 ሜጋ ዋት ማመንጨት ሲገባው የሚያመነጨው 3.5 ፣ አዋሽ 7 ኪሎ 35 ሜጋ ዋት ማመንጨት ሲገባው የሚያመነጨው 21 ሜጋ ዋት መሆኑ እና ድሬዳዋ 38 ሜጋ ዋት ማመንጨት ሲገባው ምንም እንደማያመነጭ፤ እንዲሁም የነበረውን የሃይል እጥረት እንዲያቃልሉ ኮርፖሬሽኑ 60 ሜጋ ዋት የሚያመነጩ ጀኔሬተሮችን ተከራይቶ ለኪራይ 10,368,000 USD ወጪ ማድረጉ፣ ነገር ግን የኮርፖሬሽኑ ንብረት የሆኑት ጀኔሬተሮች በሙሉ አቅማቸው አገልግሎት ቢሰጡ 62.5 ሜጋ ዋት ማመንጨት ይችሉ እንደነበረና ለኪራይ የወጣውን ወጪ ሊያስቀር ይችል እንደነበር ተገምግሟል፡፡

- የኮርፖሬሽኑ ተሽከርካሪዎች በኪሎ ሜትር የሚወስዱትን ነዳጅ ፍጆታ ለማወቅ የሚያስችል ስታንዳርድ (ኖርማላይዜሽን) አለመኖሩ፤
- የነዳጅ ዲፖዎች ደህንነታቸውን ለመጠበቅና ከአደጋ በፊት ለቅድመ ጥንቃቄ የሚረዱ ፅሁፎች (እንደ ማጨስ ክልክል ነው፣ማለፍ ክልክል ነው) አለመሟላታቸው እንዲሁም በጎኑ የሚገኘው የነዳጅ ማደያ ዲፖ እና መኖሪያ ቤቶች ተጠጋግተው የሚገኝ መሆኑ፤
- በኮርፖሬሽኑ የማያገለግሉ ንብረቶችን የሚያስወግድ ኮሚቴ ቢቋቋምም አገልግሎት/ጥቅም/ ላይ የማይውሉ ንብረቶች ተለይተው እንደማይቀመጡና የማስወገድ ስራው በአግባቡ የማይከናወን መሆኑ፤
- ኮርፖሬሽኑ በውጭም ሆነ በውስጥ ኦዲተሮች በተሰጡ አስተያየቶች መሰረት እርምጃ ስለማይወሰድ በ1997 ዓ.ም በመስሪያ ቤታችን አሁን በተሰራው የኦዲት አካባቢ ላይ ኦዲት ተከናውኖ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት የቀረበ ቢሆንም፤ በሪፖርቱ በተሰጡ አስተያየቶች መሰረት እርምጃ ያልተወሰደና አሰራሩ ያልተሻሻለ መሆኑ፤

በመሆኑም ኮርፖሬሽኑ የተጠቀሱት በርካታ የግዥ የንብረት አያያዝ ድክመቶች ላይ ተገቢው እርምጃ በመውሰድ እንዲያሻሽልና በአጠቃላይ የንብረት አስደዳደሩን ውጤታማና ስኬታማ በሆነ መልኩ ሊመራ እንደሚገባ ተገቢው የማሻሻያ ሃሣብ ተሰጥቷል፡፡

4.10 <u>የመንግሥት ተሽከርካሪዎች አጠባበቅ፤ አጠቃቀምና አወጋገድን በተመለከተ</u>

- ሀገሪቱ ለሌሎች ተግባራት ከምታወጣው ወጪ ጋር ሲነጻጸር ለመንግስት ተሸከርካሪ ግዥ፣ ጥገና፣ የነዳጅና ቅባት፣ ወዘተ... የሚወጣው ወጪ ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዝ ቢሆንም፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከ30 ዓመታት በፊት የተዘጋጀ የመንግስት ተሽከርካሪዎች የሚያስተዳድሩበት መመሪያ እንዲሻሻል አለመደረጉ ወይም ወቅታዊ የሆነ መመሪያ አለመኖሩ፤ የመንግሥት ተሽከርካሪዎችን አስተዳደር በቁጠባ እና በብቃት

እንዳይከናወን እንዲሁም ክትትል እና ቁጥጥር ለማድረግ እንዳይቻል ማድረጉ፤

- የመንግስት መ/ቤቶች በኃላፊነታቸው ሥር የሚገኙ ተሽከርካሪዎች በምን መልኩ እንደተረከቧቸው፣ የተጓዙበት ኪሎ ሜትር ብዛት፣ የተጠቀሙበትን ነዳጅ፣ ቅባት እና ሌሎች ተዛማጅ ቁሳቁሶችን መጠን፣ የተደረገላቸውን ጥገና እና ተያያዥ ወጪዎችን የሚመለከቱ ዝርዝር መረጃዎች፤ በናሙና ተመርጠው በታዩ የፌዴራል መ/ቤቶች በአግባቡ ተይዘው ያልተገኙ መሆኑ፤
- በናሙና ተመርጠው በታዩ የፌዴራል መ/ቤቶች በአብዛኛው የተሽከርካሪ ማህደሮች ውስጥ የሚያስተዳድሯቸውን ተሽከርካሪዎች በምን መልኩ እንደተረከቧቸው ማለትም በግዥ፣ በእርዳታ፣ በዝውውር ወይም በስጦታ እንደተገኙ የሚያስረዳ ግልጽ መረጃ ያለመኖሩ፤
- በግብርና ሚኒስቴር እያንዳንዱን ተሽከርካሪ ሚኒስቴሩ በምን መልኩ እንደተረከበው ብቻ ሳይሆን ስምሪት፣ ጥገና እና ተያያዥ ሁኔታዎችን የሚገልጹ መረጃዎች በተሽከርካሪዎች ፋይል ውስጥ እንዲያዙ አለመደረጉ፤
- በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን፡ በንብረት አስተዳደር ዙሪያ አንድ ኃላፊ በሌላ ኃላፊ ሲተካ ተሽከርካሪዎች በትክክል ተቆጥረው አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ፣ ተበላሽተው ጥገና ላይ ያሉ፣ ሊወገዱ የተዘጋጁ፣ የጠፉ፣ ወዘተ ተብለው ተለይተው ርክክብ የማይፈፀም በመሆኑ፤ አሁን በንብረት ኃላፊነት ቦታ የሚገኙት ሠራተኛ የተሽከርካሪዎችን ሁኔታ በሚመለከት ለቀረበላቸው ጥያቄ ግልጽ መረጃ ለመስጠት ያልቻሉ መሆኑ፤
- በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን በተሽከርካሪ ላይ አደጋ ሲደርስ የሚሞላው የአደጋ ሪፖርት ባለሙያዎች በቦታው በመገኘትና በጥንቃቄ የአደጋውን መንስዔ በማጣራት እና በተጨባጭ መረጃ በማስደገፍ ሳይሆን፤ በአብዛኛው አሽከርካሪዎች የሚሰጡትን ሪፖርት ብቻ መሠረት በማድረግ ስለሚዘጋጅ፤ አሽከርካሪዎች ጥፋተኛ ሆነው ሲገኙ ራሳቸውን ለማዳን በሚያደርጉት ጥረት ትክክለኛ መረጃ የማይያዝ መሆኑንና አስተዳደራዊ እርምጃ ስለመውሰዱ መረጃ የማያስችል መሆኑ፤

* በናሙና በታዩት መ/ቤቶች የተሸከርካሪዎች የሕይወት ታሪክ ማለትም የባለቤትነት፣ የስምሪት፣ የጥገና፣ የርክክብ እና ሌሎች ተያያዥ መረጃዎች በአግባቡ ተጠናቅረው እንደማይያዙ፤ የተያዙትም መረጃዎች እርስ በእርስ የማይጣጣሙና የሚጣረሱበት ሁኔታ መኖሩን፤ የእነዚህ መረጃዎች በተገቢ ሁኔታ አለመያዝ ተሸከርካሪውን በአግባቡ ለመጠበቅ፣ ለመጠቀም እና ለማስወገድ የሚከናወኑ ተግባራት በቁጠባ እና በብቃት ማከናወን እንዳይቻል ማድረጉ፤
* በናሙና ከታዩት የፌዴራል መ/ቤቶች መካከል የግብርና ሚኒስቴር የሚያስተዳድራቸውን የመንግሥት ተሸከርካሪዎች ቆጠራ የሚያከናወን ቢሆንም የተሸከርካሪዎቹን አጠቃላይ ሁኔታ የሚገልጽ ሪፖርት በየዓመቱ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚንስቴር እንደማያቀርብ፤
* በመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን ደግሞ የተሸከርካሪ ቆጠራ በየዓመቱ ስለማይከናወን፤ ተጠያቂነትና ግልጽነት እንዳይኖር እና በተሸከርካሪ አስተዳደር ዙሪያ የሚታዩ ችግሮች እንዳይታወቁ እና ወቅታዊ ትኩረት እንዳይሰጣቸው አስተዋጽኦ ማድረጉ፤
* በናሙና ከታዩ ስምንት የፌዴራል መ/ቤቶች ውስጥ አምስቱ ከሚያስተዳድሯቸው ተሸከርካሪዎች መካከል የተወሰኑት የተጓዙትን ርቀት የሚለካ ጌጅ የሌላቸው ሲሆን፡ ጌጅ ያላቸውም ሆነ የሌላቸው ተሸከርካሪዎች በሊትር ምን ያህል ኪሎ ሜትር መጓዝ እንደሚችሉ በየጊዜው ጥናት እየተደረገ መረጃ የሚያዝበት ሁኔታ ባለመኖሩ፤ የተሸከርካሪዎችን የነዳጅ ፍጆታ መጠን ከተጓዙበት እርቀት ጋር በማነፃጸር የነዳጅ ፍጆታቸው አዋጪ መሆን አለመሆኑን በማመዛዘን አዋጪ ሆኖ በማይገኝበት ወቅት ተሸከርካሪውን ማስወገድ ወይም መጠቀምን በተመለከተ አግባብነት ያለውን እርምጃ ለመውሰድ የማይቻል መሆኑ፤
* በናሙና ከታዩት የፌዴራል መ/ቤቶች መካከል በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ተሸከርካሪዎች በአካል አለመገኘት፣ መጥፋት፣ ከባለሥልጣኑ እውቅና ውጭ መሸጥ፣ በአሽከርካሪዎች ጥንቃቄ ጉድለት ምክንያት ተሸከርካሪዎች የመገልበጥ፣ የተሸከርካሪ አካሎች መጉደል፣ የተሸከርካሪ

ሞተሮች መጥፋት እና የተሽከርካሪ ሞተሮች በወቅቱ ሳይወገዱ ጥንቃቄ በጎደለው ሁኔታ ለፀሐይ፣ ለዝናብና ለአቧራ ተጋልጠው የሚገኙ መሆኑን ከሰነዶች እና በአካል ተሽከርካሪዎቹ የሚገኙበትን ሁኔታ በማየት ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

- ሦስት የኮንስትራክሽን ተሽከትካሪዎች ያለ መ/ቤቱ እውቅና በሽሬ እንደስላሴ ከተማ አስተዳደር እንዲሸጡ መደረጉን፤
- ሁለት የባለሥልጣኑ የኮንስትራክሽን ሮለሮች በባለሥልጣኑ ሰራተኞች በተቀናጀ መልኩ የስርቆት ሙከራ እንደተደረገባቸው፤
- በአሽከርካሪዎች ተገቢው ጥንቃቄ ባለመደረጉ ምክንያት አራት ተሽከርካሪዎች የመገልበጥ አደጋ በተደጋጋሚ እንደደረሰባቸው፤
- በዓለም ገናዲስትሪክት የሚገኝ የተሽከርካሪ ዕቃዎች መጋዘን ያረጀ፣ ቆርቆሮው የተገነጣጠለ እና በውስጡ የሚገኙ በርካታ የተሽከርካሪ ሞተሮችና አካሎች አንዱ በአንዱ ላይ ተደራርበው እና በአቧራ ተሸፍነው ለብክነት ተጋልጠው የተቀመጡ መሆኑን
- ጎንደር ዲስትሪክት 24 የመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች ሞተሮቻቸውን ጨምሮ ዋና ዋና አካሎቻቸው መጥፋታቸው፤
- በቃሊቲ እና በዓለም ገና ዲስትሪክት በርካታ የተሽከርካሪ ሞተሮች እና ዋና ዋና አካሎች ለፀሐይ፣ ለዝናብና ለአቧራ ተጋልጠው በወቅቱ ሳይወገዱ ሳር በቅሎባቸው የሚገኙ መሆኑን፤
- በተለያዩ መረጃዎች የተገለጸ ቢሆንም ባለሥልጣኑ በነዚህ ጉዳዮች ላይ የወሰደው አስተዳደራዊ እርምጃ ያለመኖሩ፤

በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር መ/ቤት

- ለባለበጀት መ/ቤቶች የተገዙ ሦስት አዳዲስ ተሽከርካሪዎች መጠባበቂያ ጎማዎቻቸው ተሰርቀው እያሉ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ስለ ጉዳዩ ውሳኔ ሳይሰጥበት ከነጉድለታቸው መ/ቤቶቹ በአስረካቢ ኮሚቴው አማካኝነት እንዲረከቡ የተደረገ ሲሆን፣ ጉዳዩን በተመለከተ መ/ቤቱ አስተዳደራዊ እርምጃ ያለመውሰዱ፤

- የሚኒስቴሩ ንብረት የሆነ የሠሌዳ ቁጥር 4-08027 ቶዮታ ራነር በ14/07/2002 ዓ.ም. ዋና ዋና የሞተር አካሎች መስረቃቸው ተጠቅሶ ለፖሊስ ሪፖርት የተደረገ ቢሆንም፤ ለክስ የሚያበቃ በቂ መረጃ አልቀረበም በሚል የክስ መዝገቡ ለጊዜው እንዲዘጋ መደረጉን፣
- በሚኒስቴሩ በተደጋጋሚ የተሽከርካሪ መለዋወጫዎች፤ ዋና ዋና የሞተር አካሎችና የመጠባበቂያ ጎማዎች እየጠፉ ባለበት ሁኔታ የመ/ቤቱ ጥበቃዎች ያለ መ/ቤቱ ፈቃድ በሥራ ሰዓት የጥበቃ ቦታቸውን ክፍት አድርገው ለግል ጉዳያቸው ከመ/ቤቱ ግቢ ውጭ የሚሄዱ መሆኑ፣
- ለባለበጀት መ/ቤቶች የተገዙ አዳዲስ ተሽከርካሪዎች የተለያዩ መለዋወጫ ዕቃዎች ለመቆጣጠር በሚያዳግት ሁኔታ ከሚኒስቴሩ የተሽከርካሪ መለዋወጫ ዕቃዎች ጋር በአንድ መጋዘን አብረው ተቀምጠው መገኘታቸው፤
- በሚኒስቴሩ የሚገኝ የመለዋወጫ መጋዘን ንብረት አስተዳደር ሠራተኛ ስለ ተሽከርካሪ መለዋወጫዎች በቂ እውቀት የሌላቸው በመሆኑ የዕቃ ወጪ መጠየቂያ /ሞዴል 22/ አስሞልተው መለዋወጫ ለማውጣት የሚመጡ ሠራተኞች መጋዘኑ ውስጥ እንዲገቡ በማድረግ የተጠየቀውን መለዋወጫ ዕቃ እራሳቸው ጠያቂዎቹ አንስተው እንዲወስዱ የሚደረግ መሆኑን፤
- በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ጋራዥ በርካታ የመለዋወጫ ዕቃዎችና ለጥገና የገቡ ተሽከርካሪዎች ያሉ ቢሆንም፤ ጋራዡ በጫካ የተዋጠ በመሆኑ ለጥበቃ የማያመች እና ለስርቆት የተጋለጠ መሆኑ፤
- የተሽከርካሪዎች መጥፋት፣ ከመ/ቤቶቹ እውቅና ውጭ መሸጥ፣ በአሽከርካሪዎች ጥንቃቄ ጉድለት ምክንያት የተሽከርካሪዎች መገልበጥ፣ ያልተወገዱ ተሽከርካሪ አካሎች በቦታቸው አለመገኘት፣ የተሽከርካሪ ሞተሮች መጥፋት እና የተሽከርካሪ ሞተሮች ጥንቃቄ በጎደለው ሁኔታ በወቅቱ ሳይወገዱ ለጸሐይ፣ ለዝናብና ለአቧራ ተጋልጠው መገኘት፣ የተሽከርካሪ መለዋወጫዎች አጠባበቅ ላይ ድክመት መታየቱ በጣም ከፍተኛ ዋጋ እና ግምት ያለው ሀብት ለብክንት እንዲዳረግ መንገድ የሚከፍት ከመሆኑም በላይ የመንግስት ተሽከርካሪዎች በኃላፊነት በተረከባቸው አካል በቂ ጥበቃ እየተደረገላቸው አለመሆኑ፤

- በማዕድን ሚኒስቴር የግዢ፣ ፋይናንስ እና ንብረት አስተዳደር የሥራ ሂደት ለስምንት ተሽከርካሪዎች ነዳጅና ቅባት ጥያቄ ሲቀርብለት የሚፈቅድ ቢሆንም፣ እነዚህ ተሽከርካሪዎች የሥራ ሂደቱ በቀጥታ የማይቆጣጠራቸው መሆኑ፤

- በግብርና ሚኒስቴር የተሽከርካሪ ዘይት ወጪ ለማድረግ የሚያዘው እና የሚፈቅደው ዘይቱን በበርሜል ወጪ አድርጎ የተረከበው ሠራተኛ መሆኑን እና ሌላ የሚቆጣጠር አካል አለመኖሩ፤

- በ2001 በጀት ዓመት በሻኮሽ /ቀብሪ ደሀር/ አስፋልት ፕሮጀክት የ8315 ሌትር የናፍጣ ጉድለት የታየ ሲሆን፤ ይህም በስቶክ ካርድ ላይ ባለው የናፍጣ ዋጋ ሲሰላ የብር 74,085.70 ዋጋ ግምት እንዳለው፤

- በአዲግራት ዲስትሪክት ሥር የነዳጅ ወጪ ትኬት ሳይፈረም ነዳጅ የሚወሰድበት ሁኔታ መኖሩ፤

- በመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን የመድህን ሽፋን ያልተገባላቸው ተሽከርካሪዎች መኖራቸው፤ አገልግሎት እየሰጡ ያሉ ተሽከርካሪዎች የመድህን ዋስትና ሽፋን ከሌላቸው በተለይም ያረጁ መኪናዎች ለአደጋ የመጋለጣቸው አጋጣሚ ሰፊ በመሆኑ መ/ቤቱን ላልተጠበቀ ከፍተኛ ወጪ ሊያጋልጠው የሚችል ከመሆኑም በላይ ነዳጅ በአግባቡ ስለማያቃጥሉ ለአካባቢ አየር መበከልም አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡

- አብዛኛዎቹ የመንግስት ተሽከርካሪዎች አዲስ ተገዝተው ሲገቡ አብሯቸው የሚገባ የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሳሪያ (fire extinguisher) ያላቸው ቢሆንም፤ አጠቃቀማቸው የማይታወቅና ሲያልቁና ሲበላሹ እንዲሁም የአገልግሎት ጊዜያቸው ሲያበቃ በየወቅቱ ክትትል የማይደረግላቸው መሆኑ፤

- የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሳሪያ (fire extinguisher) አጠቃቀምን በተመለከተ ለአሽከርካሪዎች ስልጠና አለመሰጠቱ እና የእሳት ማጥፍያ መሳሪያዎቹ የአገልግሎት ጊዜ ላይ ክትትል አለመደረጉ ተሽከርካሪዎቹ ላይ ሊከሰት

የሚችል የእሳት አደጋን በቀላሉ ለመከላከል እንዳይቻል የሚያደርግ መሆኑ፤

- በናሙና መርጠን ካየናቸው መ/ቤቶች ውስጥ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ በውኃና ኢነርጂ ሚኒስቴር፣ በግብርና ሚኒስቴር፣ በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና በመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን የሚገኙ ተሽከርካሪዎች በሁለቱ የጎን በሮቻቸው ላይ የመ/ቤታቸው ዓርማ እንዲለጠፍ ያልተደረመሆኑ፤
- ከ33 የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ውስጥ 20 መ/ቤቶች (60.61%) ተሽከርካሪዎቻቸው በጎን በሮቻቸው ላይ የመ/ቤታቸውን ዓርማ እንዲለጥፉ አለመደረጉ፤ የመንግስት ተሽከርካሪዎች ጥገናን በተመለከተ የውጭ ጋራዥ የመምረጫ መስፈርትን በተመለከተ
- በናሙና ተመርጠው ከታዩ መ/ቤቶች ውስጥ በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር፣ በውኃና ኢነርጂ ሚኒስቴር እና በማዕድን ሚኒስቴር ከአቅም በላይ የሆኑ እና በራሳቸው ጋራዦች ሊጠገኑ የማይችሉ ብልሽቶች ሲገጥሙ ለተሽከርካሪዎች ተገቢውን ጥገና መሰጠት የሚችል የውጭ ጋራዥ የመምረጫ መስፈርት የሌላቸው መሆኑ፤
- ከ33 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች መካከል 8 መ/ቤቶች (24.24%) ተሽከርካሪዎቻቸውን ከመ/ቤታቸው ጋራዥ ውጭ የጥገና አገልግሎት ለማግኘት የሚያስችል የውጭ ጋራዥ የመምረጫ መስፈርት የሌላቸው መሆኑ፤
- የመንግሥት ተሽከርካሪዎች ጥገና እንዲደረግላቸው ጥያቄ ሲቀርብ ጥገና ከመደረጉ በፊት የደረሰባቸው ብልሽት እና አስፈላጊው ጥገና ተሽከርካሪውን ከሚጠቀመው እና ጥገናውን ከሚያደርገው አካል ገለልተኛ በሆነ ባለሙያ ተሽከርካሪዎቻቸው ለጥገና ጋራዥ ከመግባታቸው በፊት የደረሰባቸውን ብልሽት የሚያረጋግጥ ገለልተኛ የቴክኒክ ኢንስፔክተር የሌላቸው በመሆኑ፤ በትክክል ጥገና የሚያስፈልጋቸው፤ የሚያስፈልጋቸውን የመለዋወጫ አይነት እና ብዛት፤ ለጥገና የሚያስፈልጋቸው ወጪ እና የጥገና ጊዜን በአግባቡ

ለማረጋገጥ እና ለመቆጣጠር የማያስችልና አላስፈላጊ ጥገና እንዲከናወን፣ በመለዋወጫ አጠቃቀም ላይ ብክነት እንዲፈጠር፣ ከሚፈለገው ጊዜ በላይ በጥገና ስም ተሽከርካሪዎች አገልግሎት ሳይሰጡ እንዲቆዩ ለሚያደርግ እና ለብልሹ አሠራር በር የሚከፍት መሆኑ፤

- በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ከባድ አደጋ ደርሶባቸው ጋራዥ የገቡ የተወሰኑ ተሽከርካሪዎች ለ43 ወራት (ሦስት ዓመት ከሰባት ወራት) ጋራዥ የቆዩበት ሁኔታ እንዳለ፣ ጥገና የተደረገላቸው 53 ተሽከርካሪዎች በናሙና ተወስደው በአማካኝ 16.58 ወራት (1 አመት ከ4 ½ ወራት) ተጠግነው ሥራ ላይ እስኪውሉ ጋራዥ ውስጥ እንደሚቆዩ፤ በዚህም ምክንያት መ/ቤቱ ሥራውን ለማከናወን ለተሽከርካሪ ኪራይ የሚያወጣው ወጪ ከፍተኛ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
- በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ብልሽት የደረሰባቸው ተሽከርካሪዎች ከመ/ቤቱ ጋራዥ ውጭ እንዲጠገኑ /out source/ ተደረገው በበጀት እጥረት ምክንያት በወቅቱ ተጠግነው የሚፈለገውን አገልግሎት ሳይሰጡ ለበርካታ ወራት በጋራዥ ውስጥ ቆመው የሚገኙ መሆኑን ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
- የመንግስት ተሽከርካሪዎች ያገልገሎት ዘመን ለመወሰን የሚያስችል መመሪያ ባለመኖሩ፤መ/ቤቶቹ ካላቸው የተሽከርካሪ እጥረት እና ያስወገዱቸውን ተሽከርካሪዎች ለመተካት በወቅቱ ስለማይገዛላቸው ያሏቸውን ተሽከርካሪዎች ያለጊዜ ገደብ ደጋግመው የሚጠቀሙ መሆኑ፤
- በመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን የተሽከርካሪዎች የአገልገሎት ዘመን ምን ያህል እንደሆነ በጥናት በተደገፈ መረጃ እንዲታወቅ ባለመደረጉ፤ ተሽከርካሪዎች ረጅም ጊዜ በማገልገላቸው ምክንያት የሚጠይቁት የነዳጅና የጥገና ወጪ ከሚሰጡት አገልግሎት ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ የሚሆን፣ በሰውና በንብረት ላይ አደጋ የማድረስ እድላቸው የሰፋ እንዲሆን የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ ተሽከርካሪዎቹ በሚያወጡት ከፍተኛ በአግባቡ ያልተቃጠለ ጭስ አካባቢን በስፋት የሚበክሉበት ሁኔታ የሚፈጥር መሆኑ፤

- በ10 የመንግስት መ/ቤቶች በመንግሥት ንብረት አወጋገድ መመሪያ መሠረት ቢያንስ 3 አባላት ያሉት የተሽከርካሪ አስወጋጅ ኮሚቴ በመ/ቤታቸው የበላይ ኃላፊ ያልተሰየመ መሆኑ፤

- የግብርና ሚኒስቴር በ1997 ዓ.ም 116ና የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በ2002 ዓ.ም ያስወገዳቸው 6 ተሸከርካሪዎች ያስወገዱ ቢሆንም፤ ተሸከርካሪዎቹ በመመሪያው መሠረት ስለመወገዳቸው የሚያስረዳ መረጃአለመቅረቡ፤

- የመንግስት መ/ቤቶች የሚወገዱ የመንግስት ተሽከርካሪዎችን ለማስወገድ የሚረዱ ዝርዝር መረጃዎችን ማለትም የተሽከርካሪው ሞዴል፣ የተሠራበትና የተገዛበት ዘመን፣ የተገዛበት ዋጋ፤ የቻሲ፣ የሞተርና የሰሌዳ ቁጥሮች፣ የነዳጅ አይነት፣ ለጥገና የወጣው ወጪ፣ አገልግሎት ያቋረጠበት ምክንያትና ጊዜ በተሟላ መልኩ አጠናቅረው እንደማያደራጁና ለአስወጋጅ ኮሚቴው የማያስረክቡ መሆኑ፤

- የመንግስት ተሽከርካሪዎች በልዩ ልዩ ምክንያት ከአገልግሎት ውጪ ሲሆኑ ወይም አገልግሎት በብቃት መስጠት የማይችሉበት ደረጃ ላይ ሲደርሱ በንብረት አወጋገድ መመሪያው መሠረት ወቅታዊ እርምጃ ሊወሰድ የሚገባ ቢሆንም፤ በየመ/ቤቱ በርካታ መወገድ የሚገባቸው የመንግስት ተሽከርካሪዎች ለፀሀይ እና ለዝናብ ተጋልጠው በአቧራ ተሸፍነውና ሳር በቅሎባቸው ለረዥም ዓመታት ሳይወገዱ ለብክነት ተዳርገው እንደሚገኙ መሆኑ፤

- በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ሶስት ኒሳን ፒክአፕ፣ እና አንድ ገልባጭ መኪናዎች በተለያዩ ምክንየት የጠፉ ወይም መልሶ ማግኘት እነደመይቻል መረጃዎች ቢጠቁሙም ባለሥልጣኑ በነዚህ ተሽከርካሪዎች ላይ አስተዳደራዊ ውሣኔ ሳይሰጥ ለ20 ዓመታት ያህል ተሽከርካሪዎቹን በንብረትነት መዝግቦ መያዙ፤

- መጠይቅ ከተላከላቸው 33 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች በ4 መ/ቤቶች (12.12%) የተወገዱ ተሽከርካሪዎች ከመዝገብ እንዲሰረዙ አለመደረጉ፤

- በመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን፣ በማዕድን ሚኒስቴር፣ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር፣ በግብርና ሚኒስቴር፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና በውኃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የተሽከርካሪ ርክክብ፣ የስምሪትና፣ የነዳጅ ቁጥጥር ፤እንዲሁም የጥገና አገልግሎት በአግባቡና በተቀላጠፈ ሁኔታ ለማከናወን የሚያስችል የተሟላ የሰው ኃይል የሌላቸው መሆኑ፤

የመንግስት ተሽከርካሪዎች በብቃትና በቁጠባ ለመጠቀም እና ለመጠበቅ የሚያስችል የተሟላ የሰው ኃይል በመመደብ ተሽከርካሪዎችን በአግባቡ ለማስተዳደር፤ ደንብና መመሪያዎችን ወቅታዊና ተግባራዊ በመድረግና የመንግስት ተሽከርካሪዎችን መረጃ በተገቢው መንገድ በማጠናቀር ውጤታማ ሥርዓት ሊዘረገ ይገባል፡፡

4.11 ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተመደበው ሀብት ለታቀደለት ዓላማ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን በተመለከተ

- በአስፈጻሚ አካላት የቀረቡት ዕቅዶች በሀገር ደረጃ የተውጣጡ ባለሙያዎች የመከለሻ እና ማጽደቂያ ጊዜያቶች ተግባራዊ አለመደረጉ፤ እንደዚሁም አስፈጻሚ አካላት የሚያቀርቡት ፕሮጀክት ፕሮፖዛል ለማጽደቅ በሚደረገዉ ሂደት ላይ፤ በአገር ደረጃ የተውጣጡ የዕቅድ ገምጋሚ ባለሙያዎች ጋር ከመቅረባቸዉ በፊት፣ በቅድሚያ አስፈላጊዉ ሁሉ መሟላቱን የማስተባበሪያ ክፍል /ዩኒት/ ሳያረጋግጥ የሚቀርብ ሲሆን፣ ገቢ ሲደረግም ገቢ የተደረገበት ቀን እና መለያ ቁጥር ተሰጥቶት ተመዝግቦ አለመገኘቱ፤
- ከክልል የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መከ/መቆ/ ጽ/ቤቶች ለ2001 በጀት አመት ዕቅዳቸውን ሳያቀርቡና በሪቪው ቦርድ ሳይታይ፤ ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ለደም ባንክ ማቋቋሚያ፤ ለመድኃኒት ማከማቻ መጋዘን ግንባታ እና ለጤና አስተዳደር መረጃ ሥርዓት (HMIS) በድምሩ ብር 81,421,318፤ ለ195 ጤና ተቋማት ግንባታና ማስፋፊያ የኮንትራት ዋጋ ሳይቀርብ የአሜሪካን ዶላር 35,735,553.00 ስራዉ በየትኞቹ ክልሎች ምን ያህል ተቋማት እንደሚገነቡ፣ የኮንትራት ዋጋቸውን የሚያሳይ መረጃ ሳይኖር፤ እንዲሁም

ለሁሉም የክልል የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መከ/መቆ/ ጽ/ቤቶች ከአለም ባንክ (EMSAP II) ብር 16,700,000.00 የተጠየቀው ገንዘብ መለቀቁ፣

- የግሎባል ፈንድ ሰባተኛ ዙር አንደኛ ዓመት ቫይረሱ ከእናት ወደፅንስ/ልጅ እንዳይተላፍ ለመከላከል አገልግሎት፣ ከፌዴራል የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ጽ/ቤት በጥር ወር መጨረሻ እና በየካቲት ወር መጀመሪያ 2001 ዓ.ም. ለክልል የኤች.አይ.ቪ/.ኤድስ መከ/መቆ/ጽ/ቤት የተላለፈ ብር 18,892,689.00 እስከ ህዳር 27 ቀን 2003 ዓ.ም. ለወረዳ ጤና ጽ/ቤት እና ለጤና ተቋማት መተላለፍ ሲገባው አለመተላለፉ፣
- የሀገር አቀፉን የማስተባበሪያ ዘዴ ቢሮ ፈቃድ ሳያገኝ በአጠቃላይ ብር 201,449,630.00 እና የአሜሪካ ዶላር 1,623,466 በተለያዩ መ/ቤቶች እና በክልል ጽ/ቤቶች ከተፈቀደለት ተግባር ውጭ ወደ ሌላ እንዲተላለፍ መደረጉ፣
- ክልሎችም ሆነ ለሌሎች አስፈጻሚ አካላት ፈንድ ሲጠይቁ የሚሰሩትን ሥራ በዝርዝር የሚያቀርቡ ቢሆንም፣ ለእያንዳንዱ ሥራ ግን ምን ያህል ወጪ እንደሚፈልጉ ዝርዝር እንደማያቀርቡ ፣ከግሎባል ፈንድ 2ኛ ዙር እና 4ኛ ዙር በድምሩ የአሜሪካን ዶላር 34,837,308.00) ሂሳብ በወቅቱ ባለማወራረዱ የተነሳ ገንዘቡ ሳይለቀቅ የጊዜ ገደቡ ማለፉ፣
- ከግሎባል ፈንድ ተገኝቶ ለአስፈጻሚ አካት ተሰጥቶ ሳይወራረድ የቆየ (የዕርዳታ ውል ስምምነት ጊዜው የተጠናቀቀ) በድምሩ ብር 752,420,349.00 ሲኖር ከዚህ ውስጥ በድምሩ ብር 624,324,142 ማለትም ካልተወራረደው ገንዘብ 83% የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና በሥሩ ያሉ መ/ቤቶችን መያዙ፣
- ለተጓዳኝ በሽታዎች መድኃኒት መግዣ (የአባላዘር በሽታዎችን ጨምሮ) ብር 175,492,922.00 ተመድቧል፡፡ ነገር ግን የስምምነቱ ጊዜ ካለፈ በኋላ ከተመደበው ገንዘብ ውስጥ ብር 166,922,559.00 ማለትም 94% የሚሆነው ሂሳብ እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2003 ዓ.ም. (ሴፕቴምበር 9 2010) ድረስ ያልተወራረደ መሆኑ፣

- በሀገሪቱ በፌዴራል ደረጃ እና በአንዳንድ ክልሎች በኤች.አይቪ. ኤድስ ዙሪያ አገልግሎት የሚፈልጉ ወገኖች ዙሪያ የተጠና ጥናት የለም፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ሕዝብን መሰረት ያደረገ የኤች.አይ.ቪ. ጥናት (Population Base HIV Survey) ለማካሄድ የአሜሪካን ዶላር 546,395 ተመድቧል፡፡ ነገር ግን ከተመደበው ገንዘብ ውስጥ የአሜሪካን ዶላር 300,000 የሚሆነው ውሉ ተሰርዞ ወደ ሌላ ተግባር እንዲዞር ተደርጓል፣ በቀሪውም አሜሪካን ዶላር 246,395.00 የተጠና ጥናት ወይም የተሰራ ሥራ ለመኖሩመረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤

- ለኤድስ ይበልጥ ተጋላጭ በሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን የቫይረሱ ስርጭት የሚዳስስ ጥናት ከአማራ ክልል በስተቀር በሌሎቹ ክልሎችም ሆነ በአገር አቀፍ ደረጃ የተጠና ጥናት የለም፡ እንዲሁም ይበልጥ ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚያገለግል የአፈፃፀም መመሪያ አልተዘጋጀም፡፡ እንደዚሁም ለአደጋ ተጋላጭና ወላጅ ላጡ ህፃናት (OVC situation analysis) ላይ የተባበሩት መንግስታት የሕጻናት መርጃ ድርጅት (UNICEF) ጥናት እንዲጠና ብር 1,000,000.00 (አንድ ሚሊዮን ብር) ለቀድሞው የሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የተሰጠ ቢሆንም ሥራ ላይ አለመዋሉ፤

- በቅድሚያ በአገሪቱ የተጓዳኝ በሽታ መድኃኒት እጥረት መኖሩና የእጥረቱ መጠን ታውቆ ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ ወገኖች ለሁሉም እንዲዳረስ ለማድረግ ጽ/ቤቱ በዕቅድ ይዞት የነበረ ቢሆንም ይህን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የተዘረጋ ሥርዓት አለመኖሩ ታውቋል፡፡ ለተጓዳኝ በሽታዎች መድኃኒት መግዣ (የአባላዘር በሽታዎችን ጨምሮ) ብር 175,492,922.00) ተመድቧል፡፡ ነገር ግን የስምምነቱ ጊዜ ካለፈ በኋላ ከተመደበው ገንዘብ ውስጥ ብር 166,922,559.00 ማለትም 94% በሚሆነው ገንዘብ እስከ ህዳር 30 ቀን 2003 ዓ.ም. መድኃኒቱ ለመገዛቱ ማስረጃ ያልቀረበና ሂሳቡም ያልተወራረደ መሆኑ፤

- ቫይረሱ በደማቸው ከሚገኝ እናቶችና አገልግሎቱን ማግኘት ከሚገባቸው በ2002 ዓ.ም. አገልግሎቱን ለመስጠት በዕቅድ የተያዘ ቢሆንም 8.3% እናቶች ብቻ አገልግሎቱን ያገኙ መሆኑ፤ በአንፃሩ ደግሞ ኤች.አይ.ቪ.

በደማቸዉ ዉስጥ ያለ ነፍሰጡር እናቶች ቫይረሱ ከእናት ወደ ፅንስ/ልጅ እንዳይተላለፍ ለመከላከል አገልግሎት ሥራ ተብሎ ለትግራይ ክልል የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መከ/መቆ ጽ/ቤት የተመደበው ገንዘብ ወደ ጤና ተቋማት ግንባታ የዞረ መሆኑ፤

- ተገቢው መረጃ የማይቀርብና ያሉትንም መረጃዎች በወቅቱ ያለመላክ ችግር መኖሩ፤ እንደዚሁም ለጤና መረጃ አያያዝ ስርዓት ዝርጋታ (Health Managemnet Information System, HMIS) ብር 26,644,800.00 የሚሆን ፈንድ ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የተለቀቀ ቢሆንም፣ የጤና ቢሮዎች ላይም ሆነ በየጤና ተቋማቱ ሥርዓቱ ተዘርግቶ ሥራ ላይ አለመዋሉ፤
- በኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ዙሪያ በተከናወኑ የፋይናንሻልም ሆነ የፊዚካል ሪፖርቶች ወጥና ተከታታይ ያለመሆን፣ ድግግሞሽ ያለባቸው እና በየሦስት ወሩ ወቅቱን ጠብቀው እንደማይላኩ፤ በአስፈጻሚ አካላት በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ ለሚሠሩ ሥራዎች ጥራቱን የጠበቀ ሪፖርት እየተጠናቀረ በየሶስት ወሩ አለመላኩ፤
- ጽ/ቤቱ ከ2000-2003 ዓ.ም. ድረስ ተግባራዊ የሚደረግ የስትራቴጂክ ዕቅዱ አፈጻጸም ሲታይ እንደሚከተለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡
  - ከ2000 እስከ በ2002 ዓ.ም 846,500,000 ኮንዶሞች ለማሰራጨት እና በ2010 መጨረሻ በአገሪቱ ያለውን የኮንደም ስርጭትን ወደ 60 ከመቶ ለማሳደግ በዕቅድ የተያዘ ቢሆንም፣ የተሰራጨው 286,500,000 ወይንም 33.8% ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የሴት ኮንዶም አቅርቦት ከስትራቴጂክ ዕቅድ 5 በመቶ ብቻ ሲሆን የኮንደም ስርጭቱ ይበልጥ ተጋላጭ በሆኑት የህብረተሰብ ክፍሎች ትኩረት ተሰጥቶት አለመሠራቱ፤
  - በአገሪቱ ውስጥ በሚገኙ የመለዮ ለባሾችና ማረሚያ ቤቶች ውስጥ 15 የማሰልጠኛ ተቋማት እና በሌሎች አስፈላጊ ቁሳቁሶች አቅማቸውን ለማጠናከር በዕቅድ ተይዞ የነበረ ቢሆንም፣ ለሚደረገው እንቅስቃሴ ትኩረት ተሰጥቶት የክትትልና የግምገማ ሥራ አለመሠራቱ፤

- ለፖሊስ 2000 ለመከላከያ 5000 እና ለቀን ሰራተኞች 5000 በድምሩ 12,000 የመረጃ ማዕከላት በ2001-2002 ዓ.ም ለማቋቋም በዕቅድ የተያዘ ቢሆንም የመረጃ ማዕከላቱ ተቋቁመው አለመገኘቱ፤
- ለበጎ ፈቃደኞች የፀረ-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ አራማጆች ተዛማጅ ግንዛቤ መስጫ ቁሳቁሶች ማዘጋጀትና መሰራጨት በሚል በዕቅድ የተያዘ ቢሆንም ቁሳቁሶቹ ተዘጋጅተውና ተሰራጭተው አለመገኘቱ፤

- በፌዴራል ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ ጽ/ቤት መጋዘን ገቢ የተደረጉ 1,500 የሕዝብ ንቅናቄ ማስፈጸሚያ መመሪያዎች የተገኙ ሲሆን፣ ጉብኝት በተደረገባቸው ክልሎች መመሪያዎቹ አለመገኘታቸው፤
- የተለያዩ የመንግስት ሴክተሮችና የተለያዩ አስፈጻሚ አካላት ለፀረ ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ተግባራት የተላከላቸውን ገንዘብ በወቅቱ እንደማይጠቀሙ፣ ተገቢውን ክትትል የማያደርጉ፤ የማወራረጃ ጊዜ ገደብ ሲቃረብ ብቻ በመሯሯጥ ገንዘብ ለመጠቀም ጥረት ስለሚያደርጉ አፈጻጸማቸው ዝቅተኛ መሆኑ፤
- ጽ/ቤቱ ከግሎባል ፈንድ ካገኘው ገንዘብ ውስጥ በጽ/ቤቱ እና በክልሎች አማካኝነት ሥልጠናና ወርክሾፕ ለማዘጋጀት በ2000 ዓ.ም. ብር 51,227,448.00፣ በ2001 ብር 90,766,434.00 በጀት የተያዘ ሲሆን ለ2002 በጀት ዓመት ለሥልጠና የተመደበው በጀት ለኦዲቱ አልቀረበም፡፡ በአጠቃላይ ምን ያህል ሠልጣኞች፣ ምን አይነት ሥልጠና መቼ እና ለምን ያህል ጊዜ እንደወሰዱ የሚያሳይ ራሱን የቻለ ዳታ ቤዝ በፌዴራልም ሆነ በክልል ተዘጋጅቶ መረጃዎቹ አለመያዙ፤
- በአገር አቀፍ ደረጃ በፌዴራል ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት አማካኝነት ወጥ የሆነ ገቢ ማስገኛ፣ የምግብ ድጋፍ እና የእንክብካቤ አገልግሎት መስጫ ደረጃ ተዘጋጅቶ አለመሰራጨቱ፤

ታውቋል፡፡

በመሆኑም ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተመደበውና የተገኘው ሀብት በታቀደለት ጊዜ ለታቀደለት አላማ በአግባቡ ሥራ ላይ

እንዲውል ለማድረግ ጽ/ቤቱ ሕግና ደንብን ተከተሎ መፈጸምና የሚመለከታቸው አካላትም ተግባረዊ ማድረጋቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡

4.12 የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን የግዥና ንብረት አስተዳደር የዕቃና አገልግሎት ግዥን በተመለከተ

- ኮርፖሬሽኑ ለሚያከናውነው የቋሚና አላቂ ዕቃዎች እንዲሁም ለአገልግሎት ግዥ የሚያገለግል ወቅታዊ የሆነ የግዥ መመሪያ ለረዥም ጊዜ ወቅታዊ አለመደረጉ፤
- ግዢ ከመፈጸሙ በፊት ከተጠቃሚ ክፍሎች የተሰበሰበውን ፍላጎት፣ አይነት እና ፍጆታን (አጠቃቀምን) ባገናዘበ ሁኔታ ግልጽና ሊለካ የሚችል የግዥ መርሀግብር (እቅድ) ስለመሆኑ በኦዲቱ ወቅት መረጃ እንዲቀርብ ተጠይቆ ሊቀርብ አለመቻሉ፤
- ኮርፖሬሽኑ የብር 2,898,003 የክሬዲት ቢል እና የካሽ ቢል ፎርማቶች ግዢ ሲፈጽም ከሶስት ያነሱ ተጫራቾች ሲቀርቡ ጨረታው እንደገና መውጣት ሲኖርበት ሁለት ተጫራቾች ብቻ በማሳተፍ አንዱ ማለፍ ባለመቻሉ ከአንዱ ግዢ ተፈጸሞ መገኘቱ፤
- ኮርፖሬሽኑ ግዥዎችን ሲፈፀም በዓመቱ ለመግዛት በግዥ ዕቅድ ባስቀመጠው ፍላጎት መሠረት የዋጋ ቅናሽ ተጠቃሚ እንዲሆን ግዥዎችን በጥቅል (bulk) ሊያከናውን፤
- በኮርፖሬሽኑ ዋና መ/ቤት በሃገር ውስጥ ግዢ ዋና ክፍል የብር 4,570,491.24፣ በውጭ ግዢ ዋና ክፍል USD 5,059,266.52 የሚያወጣ interim solution rent for transponder በጥቅል (bulk) ግዢ የዋጋ የቅናሽ ተጠቃሚ ሳይሆን የቀጥታ ግዢ በተናጠል ተፈፅመ መገኘቱ፡
- በሪጅን እና በዞን ጽ/ቤቶች እንደዚሁም በማዕከላዊ ዕቃ ግምጃ ቤት ንብረት ገቢና ወጪ እንዲሆን የሚፈቅዱ ኃላፊዎች የፊርማ ናሙና ለሚመለከታቸው ሰራተኞች ያልደረሰ መሆኑ፤

- በንብረት አስተዳደር ሥራ ላይ ለተመደቡ ነባር ሠራተኞች ከረጅም ዓመታት በፊት የስራ ድርሻ መዘርዝር (job description) የተሰጣቸው ቢሆንም፤ ሪጅኖች እና ዞኖች ለሚገኙ አዲስ በንብረት አስተዳደር ሥራ ለተመደቡ ሠራተኞች ያልደረሳቸው መሆኑን ፤
- ንብረት ወጪ የሚያደርግ ሠራተኛ በቀረበው የዕቃ መጠየቂያ መሰረት የዕቃ ወጪ ደረሰኝ (SIV) ከተሞላ በኋላ ዕቃውን ወጭ አድርጎ ፈርሞ መውሰድ ሲገባው፤ የዕቃው ዝርዝር በዕቃ ወጪ ደረሰኝ (SIV) ሳይሞላ በባዶ ደረሰኝ ላይ እንዲፈርም በማድረግ ዕቃ ወጪ የሚደረግ መሆኑ ፤
- በኮርፖሬሽኑ በዞንና በሪጅን ጽ/ቤት ለሚገኙ በርካታ የቢሮ መገልገያን ብረቶች ከማዕከል የመለያ ቁጥር የሚሰጥ ሲሆን፣ መለያ ቁጥሩ በተሟላ ሁኔታ ለሁሉም የዞንና የሪጅን ጽ/ቤት እንዲደርስ አለመደረጉ፣
- ሪጅኖችና የዞን ጽ/ቤቶች በሥራቸው ስለሚገኙ ንብረቶች አጠቃቀም አጠባበቅና አወጋገድ በየጊዜው ያጋጠሙ ችግሮችን በተመለከተ ለማዕከል ወቅቱን የጠበቀ ሪፖርት ለማድረጋቸው ማስረጃ አለመቅረቡ፤
- ከ 2000 ዓ.ም በኋላ በማእከል እንዲሁም የደቡብ ምስራቅ እና የምስራቅ ሪጅን ጽ/ቤቶች ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ተደርጎ ለሚመለከተው ክፍል ሪፖርት አለመቅረቡ፤ እንዲሁም በማዕከላዊ ዕቃ ግምጃ ቤት በተደረገው ቆጠራ በድምሩ ብር 2,644,528.80 ብልጫ፤ እንዲሁም ብር 279,328.43 ጉድለት ታይቶ ሪፖርት የቀረበ ቢሆንም፤ የተወሰደ እርምጃ ያመኖሩ፤
- ኮርፖሬሽኑ አቃቂ ከተማ ለነበረው ሬዲዮ መገናኛ ከጥር 14/1963 ዓ.ም. ጀምሮ ከተለያዩ ግለሰቦች ግምት እየተሰጠና በምሪት ያገኘው ስፋቱ 112.5 ሄክታር (1,125,118 ሜ.ካ) መሬት ዙሪያው 4 ኪ.ሜ. በግንብ የታጠረ፤ በአሁኑ ወቅት የቀድሞ ሬዲዮ መገናኛ አሮጌ መሣሪያዎች ያለበት፤ ጥቂት መጋዘኖችና ቤቶች የሚገኙበት የሚወገዱ ዕቃዎች የሚከማቹበት በጣም ሰፊ የሆነው መሬት ያለአገልግሎት ለ40 ዓመታት ያለበቂ አገልግሎት ያለአግባብ የተቀመጠ መሆኑን፤

- በማዕከላዊ ዕቃ ግምጃ ቤት በመጋዝን የቢሮ ዕቃዎች፣ መመርመሪያ መሣሪያዎች፣ የውሃ ፓምፕ፣ ስቶቭ፤ ከእንጨትና ከብረት የተሰሩ ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎች፣ ቁምሳጥን ፣ ሼልፍ የመሳሰሉት የቢሮ ዕቃዎች በሜዳ ላይ ተቀምጠው መገኘታቸው፤ በአቃቂ ሬድዮ ጣቢያና በጅማ በር ምሶሶ መንከሪያ ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚገኙ የጀኔሬተር ዕቃዎች፣ የኤሌትሪክ ቫልቮች፣ የአቭየሽን ላምፖች፣ ካፓሲተሮች እና የመሳሰሉት የተለያዩ የፓወር ዕቃዎች በመበላሸት ላይ የሚገኙ መሆናቸውን፤
- በግል ተቋራጮች ተሰርተው የተጠናቀቁ ሕንፃዎች ርክክብ ሳይፈፀም ሥራ የጀመሩና መሆናቸውንና፣ ሕንፃዎቹም በኮርፖሬሽኑ የቤቶች አስተዳደር ክፍል በንብረትነት ያልተመዘገቡ እና የመድህን ዋስትና ሽፋን ያልተገባላቸው መሆኑን፤ እንደዚሁም በተጨማሪም ሕንፃዎች፤ በረንዳቸው በዝናብ ወቅት የቢሮዎቹ ጣሪያ በገባው የዝናብ ውሃ ምክንያት የክፍሎቹ ግድግዳ በመሰነጣጠቅ ላይ መሆኑን እና ኮርኒሱ ከጣራው በገባው የዝናብ ውሃ ምክንያት መበላሸቱን፣

በመሆኑም ኮርፖሬሽኑየግዥና ንብረት አስተዳደሩን ዘመናዊ በማድረግና በአግባቡ በመጠቀም ውጤታማ ሊያደርገው በሚችል መልኩ ሊያከናውን ይገባል፡፡

4.13 በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የመንግሥት ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ላይ የተከናወነ

- የፕሮጀክቶች አፈጻጸምና ክትትል መመሪያ (guidelines) በበርካታ በፕሮጀክት አስፈጻሚዎች ተግባራዊ አለመደረጉና የግንዛቤ ማዳበሪያ ስልጠናም በቅድመ ትግበራ ግምገማ መመሪያ /Appraisal Guide line/ ላይ ብቻ ከ30-40 ለሚሆኑ ከተለያዩ መ/ቤቶች ለተውጣጡ ባለሙያዎች የተሰጠ ቢሆንም፣ በፕሮጀክት ዝግጅት (preparation)፣ ግምገማና ክትትል /monitoring & Evaluation/ ላይ ስልጠና አለመሠጠቱ፣

- አስራ ስምንት የመንግስት የልማት ፕሮጀክቶች ሁሉም የቅድመ ትግበራ ግምገማ (appraisal) ሳይከናወንባቸው ወደ ትግበራ የገቡ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

- ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት የሥራ ማከናወኛ በጀት ከመፈቀዱ በፊት፣ የግምገማ ሥራውን ከሚያከናውነው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ክፍል በግምገማ ወቅት በተሰጠ አስተያየት መሠረት የተስተካከለ ለመሆኑ በጽሁፍ የተደገፈ ማረጋገጫ (approval) እንዲቀርብ የሚደረግበት አሰራር ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፤

- የፕሮጀክት አስፈጻሚ አካላት በቅድመ ትግበራ ግምገማ ታይተው የማሻሻያ ሀሳብ የተሰጣቸውን ሰነዶች በስንት ጊዜ ውስጥ ማስተካከያውን አሟልተው ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ማቅረብ እንዳለባቸው የተገለጸ እና ተግባራዊ የተደረገ የጊዜ ገደብ አለመኖሩ፤

- በእያንዳንዱ የልማት ፕሮጀክት ጥናት ሰነድ ላይ በሚከናወነው የቅድመ ትግበራ ግምገማ ላይ የፕሮጀክቱ ባለድርሻ አካላት (stakeholders) ዝርዝር ኃላፊነት እና የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ተዘጋጅቶ እንዲፈረም አይደረግም፡፡ ለትላልቅ ፕሮጀክቶች የጥናት ሰነዶች የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት ለአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ቀርቦ ተቀባይነት ለማግኘቱም የሚረጋገጥበት አሰራር ተግባራዊ አለመደረጉ፤

- ለልማት ፕሮጀክቶች በሚመደብላቸው የፋይናንስ መጠን፣ በባህሪያቸው፣ በውስብስብነታቸውና በመሳሰሉት ደረጃ ለመስጠት መሥፈርት ሊዘጋጅላቸውና የደረጃ አሠጣጡም በአስፈጻሚዎች ሊታወቅ ይገባል፡፡

- በሚኒስቴር መ/ቤቱ አሠራር ለልማት ፕሮጀክቶች ለማስፈጸም የሚያስፈልገውን የፋይናንስ መጠን መሰረት በማድረግ ከፍተኛ፣ መካከለኛ እና አነስተኛ ተብለው ፕሮጀክቶች በልማት እቅድና ጥናት ዳይሬክቶሬት መስፈርት ተቀምጦላቸው በደረጃ የተከፋፈሉ መሆኑንና መስፈርቱንም ሌሎች መመዘኛዎችን እንደማያካትት እንዲሁም የደረጃ አመዳደቡ በፕሮጄክት አስፈጻሚዎች ዘንድ እንደማይታወቅ ፤

- ማንኛውም የልማት ፕሮጀክት ስራ ከመጀመሩ በፊት በፕሮጀክት አፈጻጸም መመሪያው መሰረት የአዋጭነት ጥናት እና የዝርዝር ንድፍ (ዲዛይን) ሥራ ሳይሰራላቸው ወደ ግንባታ ሥራ የገቡ ሆነው መገኘታቸው፤
- የልማት ፕሮጀክቶቹ በተዘጋጀለት የጥናትሰነድ ላይ በተመለከተው የጊዜ ሰሌዳ፤ በተያዘለት የጊዜ ገደብ እና የገንዘብ መጠን መሰረት እንዳልተጠናቀቁና ተጨማሪ ጊዜ እንደወሰዱ፤
- የልማት ኘሮጀክቶች አዋጪ መሆን ወይም አለመሆናቸው ዝርዝር ጥናት ከተደረገበት በኋላ ከፍተኛ ወጪ ተደርጎበት የፕሮጀክት ዝግጅቱ ሁለተኛ ደረጃ (phase) ላይ ሲደርስ እንዲቋረጥ መደረጉ፤
- የፕሮጀክቶችን ሥራ በሚከታተሉት የልማት ፕሮጀክቶች የቅድመ ትግበራ ግምገማ፣ እንዲሁም የክትትልና ግምገማ ሥራ በሚያከናውኑት የልማት እቅድና ጥናት ዳይሬክቶሬት እና የበጀት ዝግጅትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት መካከል ቅንጅታዊ አሰራር አለመኖሩ፤
- በፕሮጀክት አስፈጻሚ አካላት ስለ ፕሮጀክቶች የስራ አፈጻጸም ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚቀርበውን የሩብ ዓመት የፋይናንስ እና የፊዚካል አፈጻጸም የግምገማ እና የተጠቃለለ ሪፖርትና የግምገማ ውጤት ለሚኒስትሮች ም/ቤት የማይቀርብ መሆኑ፤
- ከጤና ሴክተር፣ ከትምህርት ሴክተር እና ከግብርና ሴክተር አስፈጻሚዎች ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር የሚቀርበው የፕሮጀክት የፊዚካል እና የፋይናንስ አፈጻጸም ሪፖርት በሚ/ር መ/ቤቱ በተዘጋጀው የሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ (ፎርማት) መሰረት ወጥነት የሌለውና፤ የሚቀርበውም ሪፖርትም በየሩብ አመቱ መሆን ሲገባው፣ በየ6 ወር ወይም በአመት አንድ ጊዜ ብቻ ሆኖ መገኘቱ፤
- የመንገድ ስራ ፕሮጀክቶችን፣ የትምህርት ሴክተር ፕሮጀክቶችን፣ የግብርና ሴክተር ፕሮጀክቶችን እና የጤና ሴክተር ፕሮጀክቶችን የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ከየፕሮጀክቱ ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የክትትል እና የማጠናቀቂያ ግምገማ (monitoring and completion evaluation) የማይከናወን መሆኑ፤

- የውሃ ሴክተር ፕሮጀክቶች የጥናት ሰነዶችና የተጠናቀሩ መረጃዎች በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ለኦዲቱ እንዲቀርብ ተጠይቆ ሊቀርብ አለመቻሉ፣
- ይህን መረጃ አለመያዙ ለፕሮጀክቶች ከኮንትራት ውል ዋጋ በላይ ክፍያ እንዲፈጸም አድርጎታል፡፡ ለዚህም የእንዳቶ ጋሰራ መንገድ ሥራ ፕሮጀክት ከመጀመሪያ የተገባው የፕሮጀክት የኮንትራት ውል ብር 390, 347,766.96 ሲሆን ከገ/ኢ/ል/ሚ/ር የበጀት ዝግጅትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ፕሮጀክት ፕሮፋይል የተገኘው የፕሮጀክት ዋጋ መረጃ የሚያመለክተው ደግሞ ብር 408,344,000.00 መሆኑን ያሳያል፡፡ ነገር ግን ለዚሁ ፕሮጀክት በትሬዠሪ ዳይሬክቶሬት ከ2000 በጀት ዓመት እስከ ጥቅምት 30 /2003 ዓ.ም. የተፈጸመ ክፍያ በድምሩ ብር 649,553,938.00 ሆኖ መገኘቱ፤
- ከፍተኛ የኢኮኖሚና ማህበራዊ አስተዋጽኦ አላቸው ተብለው በተለዩት ፕሮጀክቶች ላይ የድህረ ትግበራ ግምገማ (ex-post evaluation) ፕሮጀክቱ ተጠናቆ ሥራ ከጀመረ ጥቂት ዓመታት በኋላ ቀደም ብለው በተቀመጡ የፕሮጀክቱ በአካባቢ ላይ ሊያስከትሉ የሚችሉት ተጨማሪ ፋይዳ መሠረት፣ የተገኙ የግብ ስኬቶች እና ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ለውጦች) እንደማይከናወን፤

  ታውቋል፡፡

በመሆኑም ከፍተኛ የኢኮኖሚና ማህበራዊ አስተዋፅኦ ያላቸው ፕሮጀክቶች በቅድሚያ እየተለዩና የድህረ ትግበራ ግምገማ የሚያስፈልጋቸው መሆኑም በቅድሚያ እንዲታወቁ በማድረግ፣ እቅድ በማዘጋጀትና ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት ተሣታፊ በማድረግ የድህረ ትግበራ ግምገማ የሚከናወንበት ሥርዓት እንዲዘረጋ በማድረግ፤ የግምገማ ውጤቱም ሪፖርት ተዘጋጅቶለት ለውሣኔ ሰጪ አካላት ሊቀርብና በመረጃነትም ሊጠበቅ ይገባል፡

4.14 <u>በግብርና ሚኒስቴር የዳልጋ ከብት ሀብት ልማት በተመለከተ</u>

- የእንስሳት ሀብት ልማትን ለማፋጠንና ምርታማነትን ለማሳደግ ንዲያስችል የተመጣጠነ የከብት መኖ አቅርቦት በየትኛውም ፍላጐት ባለበት አካባቢ በመሟላት በየአካባቢው ካለው ፍላጐት ጋር የተመጣጠነ የዳልጋ ከብት መኖ

አቅርቦት በእጅጉ ያነሰና የሰብል ተረፈ ምርት የማቀነባበርና ለገበያ የማቅረብ ሥርዓትም ያልተዘረጋ መሆኑ፤

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአደጋ ጊዜ የዳልጋ ከብቶችን ለተወሰነ ጊዜ መመገብ የሚያስችል የመኖ ባንኮች በመኖ ክምችት እንዲለሙ የማድረግ ተግባር ውስን መሆኑን፤ ቢኖሩም አብዛኛዎቹ ደረጃቸውን የጠበቁ አለመሆናቸውን፤
- በትግራይ ክልል ከተጀመረው እንቅስቃሴ በስተቀር በሌሎቹ በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች ልቅ ግጦሽን የመቆጣጠርና በዘመናዊ የግጦሽ አስተዳደር ሥርዓት የመተካት ሥራ አለመከናወኑ፤
- የግጦሽ መሬቶችን ከአረም የመከላከል ተግባራት የማይከናወኑ መሆኑን፤ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በ5 ዓመት ስትራቴጂ ዕቅድ /1999-2003/ ውስጥ በአርብቶአደሩና ከፊል አርብቶ አደሩ አካባቢ ያለውን በአገር ውስጥ ና መጤ አረሞች /ቁጥቋጦዎች/ የተሸፈኑትን የግጦሽ መሬቶች ተመንጥሮ ለግጦሽ እንዲውል ማድረግን ያካተተ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት የተከለሱ መረጃዎችና የኦዲት ቡድኑ በአካል በተመለከታቸው ኦሮሚያና አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አላስፈላጊ የሆኑ ቁጥቋጦዎችና አረሞች በግጦሽ መሬት ላይ በስፋት መታየታቸው፤
- የኦሮሚያ እና አማራ ክልላዊ መስተዳድሮች በኦሮሚያ ቦረና ዞን ያቤሎ ወረዳ ሐሮበኬ ቀበሌ እና ከቡሌ ሆራ ወረዳ ቆማ ሐራ ቀበሌ በስተቀር በሌሎች የተመለከትናቸው ዞንና ወረዳዎች በግጦሽ ሥፍራዎች ለዳልጋ ከብቶች የሚሆን የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት አለመኖሩን፤
- የዳልጋ ከብቶችን ከበሽታ ለመከላከልና በጤና ጉድለት ምክንያት የሚከሰተውን ሞት ለመግታት የሚያስችል የጤና አገልግሎት ሥርዓት አለመዳረሱ እና አጥጋቢ አለመሆኑ፤
- በሀገር ውስጥ በስጋ ምርታቸው የተሻለ ምርት በሚሰጡት ላይ ጥናት ተደርጎ በደረጃ የቦረና የፎገራ የከረዩ የመሳሰሉት ጥሩ ምርት መስጠት እንደሚችሉ ቢታወቅም፤ በሥጋ ምርት ዙሪያ የዝርያ ማሻሻያ ተግባር ግን አለመጀመሩ፤
- በየክልሉ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫዎች ለአርብቶ አደሮች፤ ከፊል አርብቶ አደሮች እና አርሶ አደሮች፤ በተወሰነ ደረጃም ለሞያተኞች የሚሰጥ ሥልጠና

መኖሩን ለመገንዘብ ተችሏል። ይሁን እንጂ የሚሰጡት የግንዛቤ ማስጨበጫ እና ሥልጠናዎች በቅድሚያ የመነሻ ጥናት /የሥልጠናዎቹን አስፈላጊነት፣ በምን አይነት ጉዳይ ላይ ክፍተት እንዳለ፣ ቅድሚያ የሚሰጠውን የመለየት፣ ለነማንና ለምን ያህል ሰልጣኞች፣ ሥልጠናውን ማን ይስጥ፣ ወዘተ/ የሚለው የማይከናወን፣ የተሰጡት የግንዛቤ ማስጨበጫዎችና ሥልጠናዎች ለውጥ ማምጣታቸው ክትትል የማይደረግበት፣ ሥልጠናውም ወጥነት ያለው ሳይሆን ሥልጠናውን በሚሰጠው አካል የሚወሰን መሆኑ፤

- በእንስሳት ሐብት ልማት ዙሪያ ብቻ ኃላፊነት ያላቸው የፌዴራል እና የክልል መ/ቤቶችን በመደበኛነት የሚያገናኝ የጋራ ጉባኤ /የምክክር መድረክ/ ያልመሠረተ መሆኑን፤
- በክልል ቢሮዎችና በፌዴራል ግብርና ሚኒስቴር ከእንስሳት ሀብት ልማት ጋር በተያያዘ መረጃ የሚጠናቀርበት፣ ልውውጥ የሚደረግበትና ለተጠቃሚዎችም ዝግጁ የሚሆንበት ሥርዓት ያልተዘረጋ፤

መሆኑ ታውቋል፡

በመሆኑም በእንስሳት ሀብት ልማቱ የሚጠበቀውን ውጤት ለማምጣት እንዲያስችል በእንስሳት ሀብት ልማቱ ላይ የሚመክር ብሔራዊ የጋራ የምክክር መድረክ ቢቋቋም በዘርፉ ላይ ያሉ መሠረታዊ ችግሮች እና አንገብጋቢ ጉዳዮችን በቅደም ተከተሉ የሚለይበት፣ የመፍትሔ እርምጃ በጋራ እና በተናጠል የሚወሰድበት ሥልት የመንደፍና ተፈፃሚ የማድረግ አቅምን ለመፍጠር ከማስቻሉም በላይ የሥራ ድግግሞሽንና የሀብት መባከንን ሊያስቀር ይችላል።

5. <u>ልዩ ኦዲት</u>

<u>በልዩ ኦዲት የተከናወኑ ኦዲቶች ውጤት</u>

- መ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ከልዩ ልዩ የመንግሥት አካላት የሚቀርቡለትን ጥያቄዎች እየገመገመና ካለው የሰው ኃይል አንፃር እያገናዘበ ልዩ ኦዲት የሚያከናውን መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህም መሠረት ከጥር 2002 እስከ ታህሣሥ 2003 5 ልዩ ኦዲት በጥያቄ ተሠርቶ ሪፖርቱም ለጠያቂው አካል ተልኳል፡፡

እነርሱም :-

- በፌዴራል ሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጥያቄ፤
    - የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት የተንዳሆ ግድብና መስኖ ሥራ ፕሮጀክት የሲሚንቶና ብረታ ብረት ግዥ እና በአገር አቀፍ ኤሌክትሪክ አቅርቦት ፕሮግራም ለድሬዳዋ ገጠር ከተሞች የኤሌክትሪክ ማስፋፊያ የተገዙ ትራንስፎርመሮችና አሉሚኒየሞች በተመለከተ የተከናወነ ልዩ ኦዲት፤
    - በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን በአገር አቀፍ ኤሌክትሪክ አቅርቦት ፕሮግራም ለድሬዳዋ ገጠር ከተሞች ለሚከናወነው የኤሌክትሪክ ማስፋፊያ ስራ ከህንድና ከሌሎች ውጭ አገራት ተገዝተው ድሬዳዋ UEAP ስቶር የተራገፉ ትራንስፎርመሮች እና አሉሚኒየሞችን በተመለከተ የተከናወነ የልዩ ኦዲት ውጤት
- በሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ጥያቄ የቀድሞው የአዲስ አበባ የማገዶ እንጨት ተሸካሚ ሴቶች ማሕበር ሂሳብ ላይ የተከናወነ ልዩ ኦዲት፤

ልዩ ኦዲት ተከናውኖ ዝርዝር ሪፖርቱ በልዩ ልዩ መንግሥታዊ መ/ቤቶች ሪፖርት ጥራዝ 1 ገጽ 174 ላይ ቀርቧል፡፡

6. <u>ሌሎች ሥራዎች</u>

6.1<u>የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠትን በተመለከተ</u>

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ለግል ኦዲተሮች እና ለሂሣብ አዋቂዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የመስጠት፣ የማደስና የመሠረዝ ሥልጣን፤ እንዲሁም በማናቸውም የፌዴራል መ/ቤትና ድርጅት የውስጥ ኦዲተር ከመመደቡ በፊት ተመዳቢው አስፈላጊ የሙያ ብቃት ያለው መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

በዚህም መሠረት በበጀት ዓመት ውስጥ፣

- 7 የተፈቀደላቸው ኦዲተሮች የኦዲተርነት እና 80 የተፈቀደላቸው የሂሣብ አዋቂዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ተሰጥቷል፡፡

- 47 የተፈቀደላቸው ኦዲተሮችና 323 የሂሣብ አዋቂዎች በተፈቀደላቸው የጊዜ ገደብ የሙያ ብቃት ሰርተፊኬታቸውን በ2003 ያሣደሱ ሲሆን የስም ዝርዝራቸውን በመ/ቤቱ ዌብ ሣይትና፣ በጋዜጣ እንደዚሁም በደብዳቤ የሚመለከታቸው ድርጅቶች እንዲያውቁት ተደርጓል፡፡

- የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በጠየቁት መሠረት በየደረጃው ለሚገኙ 58 የውስጥ ኦዲተሮች የሙያ ደረጃ ማረጋገጫ ተሰጥቷል፡፡

- የሂሣብ አዋቂዎችና ኦዲተሮች የዓመታዊ የሰርተፍኬት ዕድሳት ሥራ ተሠርቷል፡፡

- የአገር አቀፍ ሠርቲፊኬሽን ኮሚቴ በተለያዩ ጊዜያት ባደረገው ስብሰባ ልዩ ልዩ የዲስፕሊን ጉድለት በታየባቸው ባለሙያዎች ላይ ውሣኔ እንዲሰጥባቸው ተደርጓል፡

6.2 <u>የመ/ቤቱ የውስጥና የውጭ ግንኙነት እና ሥልጠና</u>

- በሕዝብ ተወካዮች መ/ቤት የመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት በሙሉና ከሌሎች ቋሚ ኮሚቴ ለተወከሉ አባላት ስለኦዲትና የመንግስት ሂሳብ አያያዝ ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

- መ/ቤታችን በአዲሱ አሠራር ከኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ጋር መኖር ስለሚገባው የሥራ ግንኙነት አስመልክቶ የአንድ ቀን ገለጻና ውይይት ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ስለዋና ኦዲተር ስልጣንና ኃላፊነት ያለቸውን ግንዛቤ ለማስረጽ የሚረዳ ተፕሮቶኮል ተዘጋጅቶ ለእያንዳንዱ የኦዲት ተደራጊ መ/ቤት በአድራሻ እንዲደርስ ተደርጓል፡

- የህንድ መንግሥት በሰጠው የስልጠና እድል የዘጠኝ ሠራተኞች ፎርማሊቲ ተሟልቶ ወደ ህንድ ኤምባሲ የተላከ ሲሆን ሁለት ሠራተኞች ደግሞ ሥልጠናውን ተከታትለው ተመልሷል፣

- የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ከመሠረታዊ አገልግሎቶች ማስከበር (PBS) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ መሠረት አንድ የመ/ቤታችን ሠራተኛ በ CIA በመሰልጠን ላይ ይገኛል፡፡

- ከዲሞክራሲዊ ተቋማት ግንባታ (DIP) ከዓለም ባንክ እንዲሁም ከየዳይሬክቶሬቱ የተሰበሰበውን የስልጠና ፍላጐት በማጠናቀር ዓመታዊ የስልጠና የድርጊት መርሀ ግብር ተዘጋጅቷል፡፡
- የቢሮ ረዳቶችና ሾፌሮች ስልጠና እንዲወስዱ ፕሮግራም የተያዘ ሲሆን ለ1 ሾፌር የሾፌሮች መካኒክነት ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- 48 የመ/ቤቱ ሠራተኞች የACCA በመማር ላይ ሲሆኑ፣ ሌሎች 65 ሠራተኞች ደግሞ ለመማር ተመዝግበዋል 34 ሠራተኞች ትምህርታቸውን እንዲያሻሽሉ ድጋፍ ተደርጓል፣
- ሁለት የሰው ሀብትና ሥራ አመራር ሠራተኞች የኢንፎርሜሽን ሲስተም ሰርቪስ በሰጠው የኮምፒውተር ስልጠና ላይ ለ15 ቀናት ተከታትለዋል፣
- የመ/ቤቱን የሰው ሀብት ልማት አፈጻፀም መመሪያ ረቂቅ ላይ ውይይት ተካሂዶ አስተያየት ከተሰጠ በኋላ የመጨረሻ ቅርፁን እንዲይዝ ተደርጓል፡፡
- መ/ቤቱ በአዲስ መልክ ያዘጋጀውን የሥነ ምግባር ደንብ ለ378 ሠራተኞች እንዲሠራጭ አድርጓል፡፡
- በዩናይትድ ኪንግደም ብሔራዊ ኦዲት ኦፊስ ድጋፍ የተዘጋጀውን የሰው ሀብት ሥራ አመራር ልማት ስትራቴጂ እንዲፀድቅ ተደርጓል፡፡
- በመ/ቤታችን አስተባባሪነት የዲሞክራሲ ተቋማት አቅምን ለመገንባት በተደረገው የፍላጐት ጥናት ሂደቱን በመከታተል ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች እና አገልግሎቶች ለኮንሰልታንቶች እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡
- የዲሞክራሲ ተቋማት አቅምን ለመገንባት በተዘጋጀው የፍላጐት ጥናት መሠረት የመጀመሪያ ረቂቅ የእስትራቴጂና እቅድ ሰነድ ላይ ለመሥራት የሚያስችል ወርክ ሾፕ በማዘጋጀት የጥናት ሰነዱን ለማዳበር የሚያስችል መረጃ እንዲሰበሰብ ተደርጓል፡፡
- ለመሠረታዊ አገልግሎቶች ማስከበር (PBS II) ማስፈፀሚያ ከዓለም ባንክ በተሰጠው እርዳታ የፌዴራል እና የክልል ኦዲት መ/ቤቶች ተጠቃሚ

የሚሆኑበትን የጋራ የስልጠና መስኮች በዝርዝር አጥንቶ ለውይይት በማቅረብ ውሣኔ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡

- ከናሽናል ኦዲት ኦፊስ (NAO) ለመጡ የሰው ሀብት (HR) ባለሙያ የመ/ቤቱን የሰው ሀብት (HR) ስትራቴጂ እና ፖሊሲ ለማዘጋጀት የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍና እገዛ ተደርጓል፡፡
- መ/ቤታችን በአዲሱ አሠራር ከኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ጋር መኖር ስለሚገባው የሥራ ግንኙነት አስመልክቶ የአንድ ቀን ገለጻና ውይይት ተደርጓል፡፡እንዲሁም ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ስለዋና ኦዲተር ስልጣንና ኃላፊነት ያለቸውን ግንዛቤ ለማስረጽ የሚረዳ ተፕሮቶኮል ተዘጋጅቶ ለእያንዳንዱ የኦዲት ተደራጊ መ/ቤት በአድራሻ እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

ለክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች የተሰጠ የስልጠና ድጋፍ

የክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች በሥልጠና ረገድ የድጋፍ ጥያቄ ሲያቀርቡ መ/ቤታችን አስፈላጊውን እገዛ በማድረግ ላይ ይገኛል ረገድ በዚህ፣

- የፌዴራልና የክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች በዲሞክራሲ አቅም ግንባታ ኘሮግራም (DIP) አማካኝነት በ2003 እና በ2004 ለማከናወን የሚፈልጓቸውን በመለየት እቅድ አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ በማድረግ እቅዱን አንድ ላይ በማጠናቀር ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር እና ለእርዳታ ሰጪ አካላት አቅርቦ በማስተቸት ተገቢውን ማስተካከያ በማድረግ ፀድቆ በሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡በሕዝብ ተወካዮች መ/ቤት የመንግስት ወጪ አሰስተዳደርና ቁጥጥር ቋሚ ኮሚቴ አባላት በሙሉና ከሌሎች ቋሚ ኮሚቴ ለተወከሉ አባላት ስለኦዲትና የመንግስት ሂሳብ አያያዝ ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

በኢንፎርሜሽን ሰርቪስ የተሠሩ ዋና ዋና ሥራዎች

- IBEX ስልጠናን በተመለከተ በገ/ኢ/ል/ሚ ባለሙያዎች ጋር ግንኙነት ከመ/ቤቱ ለተውጣጡ ባለሙያዎች /ከመረጃ አገልግሎት ዋና ክፍል እና ከኦዲተሮች/ በአንድ ሣምንት ሥልጠናውን እንዲወስዱ ተደርጓል፣

- Information Technology self Assessment (ITSA) Work Shop ላይ በመ/ቤታችን ስልጠናው ተካሂዷል፣
- ደቡብ አፍሪካ በተካሄደው Information System work Shop ላይ ከመ/ቤቱ ሁለት ሰልጣኞች ተወክለው ሠልጥነው ተመልሰዋል፣
- የላይብረሪ፣ የመዝገብ ቤትና የሰው ሀብት አውቶሜሽን ሥራ ተጠናቋል፣
- ከ National Audit Office (NAO) ለመጡ ባለሙያዎች ከተዘጋጀው የ5 ዓመታት የIT Strategic እቅድ በመነሳት የ6 ወራት እቅድ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡
- በመሠረታዊ የኮምፒዮተር ሥልጠና ላይ ለ21 የመ/ቤታችን ሠራተኞች ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡
- የኢትዮጵያ ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ልማት ኤጀንሲ ባዘጋጀው በHardware maintenance፣ በOracle 10g እና በAdvanced Networking ሥልጠና ላይ ሦስት የክፍሉ ባለሙያዎች ሥልጠናውን እንዲካፈሉ ተደርጓል፡፡
- በመ/ቤቱ ውስጥ በተካሄደው የሰራተኞች የስራ ቦታ ድልድል ምክንያት የኔትወርክ መስመር ላልተዘረጋላቸው ሰራተኞች 24 ተጨማሪ የኔትወርክ መስመር ተዘርግቷል፡፡
- TeamMate ሶፍትዌርን ወደ ተግባር ለማሸጋገርና የኦዲቱን ሥራ በይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ የስልጠና ድጋፍ ከCIDA የተገኘ በመሆኑ ለዚሁ የሚረዳ TOR ተዘጋጅቶል፡፡ በተዘጋጀው TOR ላይ ከCIDA ባለሙያዎች ጋር ውይይት የተደረገ ሲሆን በተሰጠው የማሻሻያ ሀሣብ መሠረት እንዲስተካከል በማድረግ የመጨረሻውን ቅርጽ እንዲይዝ በማድረግ ለ CIDA ተልኳል፡፡
- የመ/ቤቱን ድረገጽ ለማሻሻል፣ ኢንትራኔት እና እንዲሁም የዶክሜንት ማኔጅመንት ስርዓት ለማሰራት የሚያስችል መረጃ ለመሰብሰብ በINSA ጉብኝት የተደረገ ሲሆን ለመነሻ የሚሆን TOR ተዘጋጅቷል፡፡ በቀጣይም እነዚህን ሶፍትዌሮች ለማሰራት በዝግጅት ላይ እንገኛለን

- ለመ/ቤታችን ፀሐፊዎች ስለ መ/ቤታችን የኔት ወርክ አጠቃቀምና የኮምፒውተር አያያዝ በተመለከተ ግንዛቤ የማሣደግ ስልጠና ተሰጥቷቸዋል፡፡

7. ያጋጠሙ ችግሮች

ሥራውን በተጠናው የመሰረታዊ አሰራር ለውጥ (BPR) መሠረት በጥራትና በብዛት ለመስራት ልምድ ያለው የሰው ኃይል በሚፈለገው መጠን አለመገኘትና ከገበያ ለመቅጠርም በደመወዙ አነስተኛነት ምክንያት ማግኘት አለመቻል፡፡

የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የሥራ ኃላፊዎች ለልዩ ልዩ ማብራሪያዎችና ጉዳዮች ሲፈለጉ በወቅቱ አለመገኘትና ለኦዲተሮች ሥራ የሚያስፈልግ ቢሮ በወቅቱ ያለመስጠት፣

የሚሉ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

8. የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

ያለውን የሰው ኃይል በማሰልጠን የማብቃተ ሥራዎችን በማከናወን፣ በየወቅቱ ክትትል በማድረግና ከገበያም የተገኘውን ያህል በመቅጠር ክፍተቱን ለመሙላት ጥረት ተደርጓል፡፡

ከኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ጋርም የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ፕሮቶኮል በመዘጋጀትና በማሰራጨት እንዲሁም የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራም በማዘጋጀትና ማወያየት ድጋፍና ትብብሩ እንዲጎለብት ጥረት ተደርጓል፡፡

9. ማጠቃለያ

በሪፖርቱ እንደተመለከተው በ2002 በጀት ዓመት ሂሣብ ላይ የተካሄደው የኦዲት ሽፋን ከ87% በላይ ደርሷል፡፡ ውዝፍ የኦዲት ሥራ ባለመኖሩ ወቅታዊ የኦዲት መረጃን ማመንጨት ተችሏል፡፡ በዚህ ረገድ የተገኘው ውጤት የሀገራችንን የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት የተሻለ ደረጃ ላይ መድረሱን የሚያመለክት ቢሆንም በኦዲቱ ሂዳት የተገኙት ዋና ዋና ግድፈቶች በአፋጣኝ እርምጃ ሊወሰድባቸው ይገባል፡፡ ዝርዝር ሪፖርቱ በሁለት ጥራዝ ተዘጋጅቶ የቀረበ በመሆኑ ም/ቤቱ

በመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በኩል በጥልቀት መርምሮ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

በዚህ ረገድ እርምጃ ሳይወሰድባቸው በዓመት ወደ ዓመት የሚተላለፉ የሠነድ ሂሣቦች፣ ደንብና መመሪያን ሳይጠብቁ የሚፈጸሙ ግዥዎች፣ ከመንግሥት ገቢ አተማመንና አሰባሰብ ጋር ተያይዞ በየዓመቱ የሚታይ ተመሳሳይ ችግሮችና ከውስጥ ገቢ አሰባሰብና ሪፖርት አደራረግ አንፃር የሚታዩ ችግሮች እንደዚሁም ከመንግሥት ንብረት አያያዝና አጠቃቀም ላይ የሚታዩ ችግሮች ላይ ትኩረት አግኝተው መርሀ-ግብር ወጥቶላቸው እርምጃ ሊወሰድባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው፡፡

በመጨረሻም የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የቀረፃቸውን የአሠራር ማሻሻያዎችና ስትራቴጂዎችን በሚገባ በመተግበር ይበልጥ እንዲጠናከረና የምክር ቤቱን የክትትልና የቁጥጥር ተግባር በተሻለ ደረጃ እንዲያግዝ ሁሉን አቀፍ ድጋፍና ክትትል እንዲደረግለት እንጠይቃለን፡፡

የ2002 በጀት ዓመት የመንግሥት ልማት ድርጅቶች፣ ፕሮጀክቶችና የእርዳታ ሂሳቦች ኦዲት

1. መግቢያ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ በተሰጠው ኃላፊነት በመንግሥት በጀት የሚተዳደሩ እና በራሳቸው ገቢ የሚተዳደሩ የመንግሥት ድርጅቶችን፣ በመንግሥትና በውጭ ሀገር መንግሥት ድጋፍ የሚከናወኑትን ፕሮጀክቶችን፣ እንዲሁም የዕርዳታ ሂሳቦችን ኦዲት እንደሚያደርግ ይታወቃል። ሆኖም በመ/ቤቱ የአቅም ውስንነት የተነሳ ራሱ ከሚሰራው በተጨማሪ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን፣ ፕሮጀክቶችንና የዕርዳታ ሂሰቦች በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና ከመ/ቤቱ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶች ኦዲት በመደረግ ላይ ይገኛሉ። በኦዲት ድርጅቶቹ ኦዲት ተደርገው በሚቀርቡ ሪፖርት መነሻነት መሻሻል ያለባቸው ጉዳዮች አስፈላጊው ማሻሻያዎችና እርምጃዎች እንዲወሰዱ ለኦዲት ተደራጊው ድርጅት፣ ለሥራ አመራር ቦርድና ለተቆጣጣሪ የበላይ መ/ቤቶች በደብዳቤ አስፈላጊው ማሳሰቢያ ይሰጣል።

በ2002 በጀት ዓመት ኦዲት የተደረጉት የመንግሥት የልማት ድርጅቶችና በሽርክና የተቋቋሙ ድርጅቶች 99 ሲሆኑ፣ በኢትዮጵያ መንግሥትና በውጭ መንግሥታት የጋራ ትብብር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ሂሳብ ደግሞ 131 በድምሩ 230 (ይህ ቁጥር በአንድ በጀት ዓመት የሁለት እና ከዚያ በላይ ያሉትን በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት የተደረገ ከሆነ የቅርቡን በጀት ዓመት ብቻ እንደ አንድ በመቁጠር የተወሰደ ነው) ናቸው።

ይህ ሪፖርት የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን የኦዲት ዓመት ስለማይከተል ከሀሐምሌ 1/2001 እስከ ሰኔ 30/2002 በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል የኦዲት ድርጅቶች ተከናውነው የኦዲት ሪፖርታቸው ለመ/ቤታችን የደረሱት የሚመለከት ሲሆን፣የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የ2002 በጀት ዓመት የሥራ እንቅስቃሰ ሕና ኦዲት ድርጅቶቹ በተከናወነው ኦዲት የተገኙ ጎላ ጎላ ያሉ ግኝቶች ቀጥለው ቀርበዋል።

2. የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የ2002 በጀት ዓመት የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት

2.1የኮርፖሬሽኑ ዓላማ

የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የተቋቋመው በአዋጅ ቁጥር 126/1969 ሲሆን የመንግሥት የሆኑ ወይም አብዛኛው ድርሻቸው በመንግሥት ለተያዘ የማምረቻና የማከፋፈያ እና የአገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ሂሣብ ኦዲት ማድረግና የኦዲት ሙያን ማዳበር ሲሆን፣ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ራሳቸውን ችለው በአዋጅ ቁጥር
25/1984 እንዲተዳደሩ ከተወሰነ ወዲህ ግን፣ የኦዲት ሥራውን በጨረታ ካሸነፈ፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችንም ሆነ የግል ድርጅቶችን ሂሣብ ኦዲት በማድረግ ላይ ይገኛል።

2.2የኦዲት ሪፖርት ዝግጅትና ስርጭት

የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ኦዲት ሪፖርቶችን ለድርጅቱ የበላይ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ወይም ለሥራ አመራር ቦርድ ሲልክ በግልባጭ ለተመርማሪው ድርጅት ያሳውቃል።

በተጨማሪም ለፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት እና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርቱን ተመልክተው አስፈላጊውን መረጃ እንዲያገኙና ክትትል እንዲያደርጉ በግልባጭ እንዲያውቁት ይደረጋል።

አንድ የፋይናንስ ኦዲት ከተከናወነ በኋላ የሚዘጋጁት ሪፖርቶች ሁለት ዓይነት ሲሆኑ እነርሱም አጭርና ረዥም /ዝርዝር/ ሪፖርት በመባል ይታወቃሉ።

በአጭር ሪፖርት የሚሰጡ አስተያየቶች ዋና ዓላማ በአንድ ድርጅት ተዘጋጅተው የቀረቡ የሂሣብ መግለጫዎች በአለም አቀፍ ተቀባይነት ያላቸውን የኦዲት ደረጃዎች መሠረት በማድረግ በቂ በሆነ ናሙና /በአልፎ አልፎ የኦዲት ዘዴ/ በመጠቀም ኦዲት ከተደረጉ በኋላ መግለጫዎቹ ትክክለኛውን የፋይናንስ ሁኔታ ማሣየት ወይም አለማሳየታቸውን በመግለፅ ኦዲተሩ አስተያየት የሚሰጥባቸው ናቸው።

በረጅም ሪፖርት ላይ የሚሰጡ አስተያየቶች በኦዲቱ ወቅት የተደረሰባቸውን የገንዘብና የንብረት ጉድለቶች፣ የቁጥጥርና የአሠራር ድክመቶች በመጠቆም እነዚህን ጉድለቶችና ድክመቶች ለማስወገድ ምን ዓይነት እርምጃ መወሰድ እንዳለበት በመግለጽ የማሻሻያ ሃሣብ የሚሰጥበት ነው::

2.3የሥራ ዕቅድና ክንውን

ኮርፖሬሽኑ በ2002 በጀት ዓመት በዕቅድ የያዛቸውና ያከናወናቸዉ የሂሣብ ምርመራ ተግባራት እንደሚከተለው ቀርበዋል::

ተራ ቁ.	መግለጫ	የ2002 በጀት ዓመት		የ2001 በጀት ዓመት ክንውን
		ዕቅድ	ክንውን	
1	የአምራች ድርጅቶች ኦዲት መምሪያ	169	154	119
2	የአገልግሎት ሰጪና የማከፋፈያ ድርጅቶች ኦዲት መምሪያ	88	68	71
	ድምር	257	222	190

ከላይ እንደተመለከተው የ2002 ክንውን በሪፖርት ብዛት ከዕቅዱ ጋር ሲነፃር በ35 (32%) ሪፖርቶች ዝቅ ያለ ሲሆን፣ ለዚህም ምክንያቱ እንደተጠበቀው ከኦዲት ተደራጊ ድርጅቶች ረቂቅ የሂሣብ መግለጫዎች ለምርመራ ባለመቅረባቸውና ምርመራውም ተጠናቆና ሪፖርቶች ተዘጋጅተው ነገር ግን ውይይቱ በበጀት ዓመቱ ባለመጠናቀቁ ወደሚቀጥለው በጀት ዓመት በመተላለፋቸው ነው፡፡ ከዚህም በላይ በበጀት ዕቅዱ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ሰራተኞች ድንገት ሳያሳውቁ በፈቃዳቸው ሥራ በመልቀቃቸው የሰው ኃይሉ በመሳሳቱ ነው፡፡ ሆኖም ከ2001 በጀት ዓመት ጋር ሲነፃር በ32 ሪፖርት ወይም በ17% ብልጫ አሳይተል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በመንግስት ጥያቄ የሁለት የፈረሱ ድርጅቶችን ሂሳብ ማጣራት እያገባደደ ይገኛል፡፡

2.4 የኮርፖሬሽኑ የሰው ኃይል ሁኔታ

በ2001 በጀት ዓመት መጨረሻ የሠራተኛው ብዛት 122 የነበረ ሲሆን፣ በ2002 በጀት ዓመት ውስጥ 3 የተቀጠሩ፣ 7 ከምድብ ሥራቸው ላይ የጠፉ 2 በጡረታ የተገለለ 4 በፈቃዳቸው የተሰናበቱ በመሆኑ በ2002 በጀት ዓመት መጨረሻ 112 ሠራተኞች እንደነበሩ ታውቋል፡፡

በ2002 በጀት ዓመት መጨረሻ የነበረው የሰው ኃይል በሙያ ሲተነተን 70 ፕሮፌሽናል ኦዲተሮች፣ 41 የአስተዳደር እና አንድ የትምህርትና ስልጠና ሠራተኞች እንደሆኑ ታውቋል፡፡

2.5 የሰው ኃይል ሥልጠናን በተመለከተ

ኮርፖሬሽኑ ከተቋቋመበት ዓላማ አንደኛው የኦዲት ሙያ በይበልጥ የሚዳብርበትንና አገሪቷ በዚህ ሙያ ረገድ በአጭር ጊዜ ውስጥ ራሷን እንድትችል የሚደረገውን ጥረት ማገዝ እንደሆነ ቀደም ሲል ተገልጿል፡፡

በዚህም መሠረት በእንግሊዝ አገር ከሚገኘው አሶስዬሽንስ ኦፍ ሠርቲፋይድ አካውንታንትስ (ACCA) የሚሰጠውን የተልዕኮ የሙያ ትምህርት የድርጅቱ ኦዲተሮች እንዲከታተሉ በገንዘብና በጊዜ እንዲሁም በመጻሕፍት እየረዳ 22 ሠራተኞችን በማስተማር ላይ ይገኛል፡፡
ከዚህም በተጨማሪ በአገር ውስጥ ባሉ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ትምህርታቸውን በትርፍ ጊዜአቸው ለሚማሩ ሰራተኞች እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ተገቢውን ድጋፍ ሲሰጥ ቆይቷል፡፡

የኦዲት ሙያ ያለ ቀጣይና ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ሊከናወን እንደማይችል በዓለም አቀፍ ደረጃ የታመነበት በመሆኑ ኮርፖሬሽኑ በዚህ ረገድ ለሠራተኛ የሚሠጠው ሥልጠና ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡

2.6 የኮርፖሬሽኑ የፋይናንስ እንቅስቃሴ

የኮርፖሬሽኑ የገቢ ምንጭ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች የኦዲት አገልግሎት በመስጠት የሚያገኘው ገቢ ሲሆን፣ በ2002 በጀት ዓመት በዕቅድ የያዘውና በትክክል አገልግሎቱን አከናውኖ ያገኘው ገቢ እንዲሁም ሥራውን

ለማከናወን ያቀደው ወጪና በአግባቡ ወጪ ያደረገው ሂሣብ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የ2002 የፋይናንስ ዕቅድና ክንውን

መግለጫ	ገቢ ብር	ወጪ ብር	ትርፍ ብር
ዕቅድ	7,806,960	6,790,658	1,016,302
ክንውን	8,529,102	6,155,299	2,373,803
ክንውን በመብለጥ /በማነስ/	722,142	653,359	1,357,501

የ2002 የዕቅድ ክንውን ከ2001 ጋር ሲነፃፀር እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

የበጀት ዘመን	ገቢ ብር	ወጪ ብር	የተጣራ ትርፍ ብር
2002	8,529,102	6,155,299	2,373,803
2001	8,494,172	6,334,854	2,159,318
ልዩነት በመብለጥ /በማነስ/	34,930	(179,555)	214,485

በሰንጠረዡ እንደተመለከተው የ2002 የገቢ ክንውን ከ2001 ጋር ሲነፃፀር ከፍ ያለ ሲሆን የወጪ ክንውን ደግሞ ከ2001 በጀት ዓመት ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡

3. በ2002 በጀት ዓመት በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል የኦዲት ድርጅቶች ኦዲት ተደርጎ የቀረቡ ሪፖርቶች

በ2002 በጀት ዓመት ኦዲት የተደረጉት የመንግሥት የልማት ድርጅቶችና በሽርክና የተቋቋሙ ድርጅቶች 99 ሲሆኑ፣ በኢትዮጵያ መንግሥትና በውጭ መንግሥታት የጋራ ትብብር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ሂሳብ ደግሞ 131 በድምሩ 230 (ይህ ቁጥር በአንድ በጀት ዓመት የሁለት እና ከዚያ በላይ ሂሳብ ኦዲት የተደረገው የቅርቡን በጀት ዓመት ብቻ እንደ አንድ በመቁጠር የተወሰደ ነው) ናቸው፡፡

በእነዚህ ሪፖርቶች የተሰጠው በኦዲት አስተያየት ዓይነት ሲተነተን፣ ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት (Unqualified opinion) የቀረበበት 95፣ ነቀፌታ ያለበት አስተያየት (Qualified opinion) የቀረበበት 129፣ አቋም የማይወሰድበት አስተያየት (Disclaimer opinion) የቀረበበት 6 በድምሩ 230 ነቸው።

4. <u>የኦዲት ዋና ዋና ግኝቶች</u>

በ2002 በጀት ዓመት በኦዲት ሰርቪስ ኮርፖሬሽንና በግል ኦዲት ድርጅቶች ሂሣባቸው ኦዲት ተደረጎ ሪፖርታቸው ለመ/ቤታችን ከደረሱት የመንግሥት ልማት ድርጅቶች የኦዲት ሪፖርቱ ውጤት አቋም ለመውሰድ የማይቻል ነው ተብሎ በኦዲተሮች አስተያየት የተሠጠባቸው ድርጅቶች ሁኔታና ከሁለት ዓመት በላይ ሂሳባቸውን ኦዲት ያላስደረጉ ድርጅቶች ዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

4.1 <u>አቋም ሊወሰድበት የማይቻል የኦዲት አስተያየት የቀረበባቸው</u>

አቋም ሊወሰድበት የማይቻል (Disclaimer opinion) የኦዲት አስተያየት የተሰጠባቸው የመንግሥት ልማት ድርጅቶችና አስተያየቱን ሊያሰጡ የቻሉ ዋና ዋና ድክመትና የሂሳብ አያያዝ ጉድለቶች ቀጥሎ ቀርበዋል፡፡

4.1.1 <u>አቃቂ ጨርቃ ጨርቅ አ.ማ</u>

30 June 2008 እ.ኤ.አ.የተጠናቀቀው የአክስዮን ማህበሩ ሂሳብ ኦዲት ተደርጎ የሚከተሉት ግኝቶች በመኖራቸው ኦዲተሮች በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አስተያየት ለመስጠት አለመቻላቸውን ገልጿል፡፡

- በመጓጓዝ ላይ ያለ ዕቃ ሂሳብ ብር 641,283 ውስጥ ብር 608,820 በኢትዮ-ኤርትራ የድንበር ግጭት ወቅት በአሰብ ወደብ የጠፉና የመጨሻ ውጤት ያልታወቀ መሆኑ፣
- በክምችት ከተያዘው ዕቃ ዋናውን ድርሻ የያዘው የመለዋወጫ ዕቃዎች (spare parts) ብር 13,412,645 በሙሉ የመጠባበቂያ ሂሳብ የተያዘበት ነው፡፡ ሆኖም የማይፈለጉና ስራ ላይ ሊውሉ የማይችሉትን ለማስወሰድ የተደረገ ጥረት ካለመኖሩም በላይ

ቢሸጡ የድርጅቱን የገንዘብ ችግር በመጠኑም ሊያቀልሉ ይችሉ ነበር፡፡

- የIDF ብድር ብር 5,000,000 አልተከፈለም፡፡
- በሀብትና ዕዳ ከተመለከቱት ተከፋይ ሂሳቦች ብር 10,758,415 ሳይከፈል ለበርካታ ዓመታት የቆየ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 8,219,287 ያልተከፈለ ታክስና የጡረታ ሂሳብ ነው፡፡
- በሂሳብ መግለጫዎቹ እንደተመለከተው የኩባንያው የተከፈለ ካፒታል በጠቅላላ አልቋል፡፡ የዓመቱ ሽያጭ ገቢ ብር 3,732,532 ከሽያጭ ውጪ ብር 10,817,233 ጋር ሲነፃፀር ድርጅቱ ከፍተኛ ችግር ውስጥ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ከሁሉም በላይ የቅርብ ተከፋይ ሂሳብ የአሁኑን ጥሬ ገንዘብና እንደ ጥሬ ገንዘብ የሚቆጠሩትን ሀብት በብር 20,869,678 ይበልጣል፡፡ እነዚህ ድርጅቱን ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች ናቸው፡፡ በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አንቀጽ 495(ሐ) እና(ሸ) መሠረት እነዚህ ችግሮች ድርጅቱ መፍረስ ያለበት ሆኖ እያለ የሂሳብ መግለጫዎች የተዘጋጁት ቀጣይ ሕልውናን (Going concern) ታሳቢ በማድረግ መሆኑ፣

የሚሉት ናቸው፡፡

በመሆኑም በእነዚህ በቀረቡት አስተያየቶች ላይ አክስዮን ማህበሩ ያለውን አስተያየትና የተወሰዱ እርምጃዎችን ለፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ እንዲገልጽና ለመ/ቤታችን በግልባጭ እንዲያሳውቅ ቢጠየቅም የተሰጠ ምላሽ የለም፡፡

4.1.2 <u>መካከለኛው አዋሽ እርሻ ልማት ድርጅት</u>

ሰኔ 30 1998 እና ሰኔ 30 1999 የተጠናቀቀው የድርጅቱ ሂሳብ ኦዲት ተደርጎ የቀረበው ኦዲት አስተያየት ተመሳሳይ ሲሆን የሰኔ 30/1999 ሂሳብ ላይ የተሰጠው ቀጥሎ የተመለከተው ነው፡፡

- የድርጅቱ የቋሚ ንብረት አመዘጋገብ ላይ አጥጋቢ የቁጥጥር ሥርዓት ባለመኖሩ በሀብትና ዕዳ መግለጫ ላይ የተመለከተው ሂሳብ በትክክል መመዝገቡን ለማረጋገጥ አልተቻለም፣
- በጉዞ ላይ ላሉ ንብረቶች ከመድረሳቸው የተያዘው ሂሳብ ብር 831,907 ንብረቶቹ ሳይደርሱ ለምን ያልተለመደ ኔጋቲቭ ባላንስ እንደተከሰተና ከቋሚ ንብረት ሊቀነስ እንዲቻል በቂ ማብራሪያ ማግኘት አለመቻሉ፣
- የሌላ መ/ቤት ወይም ድርጅት ያልሆነ የክምችት ዕቃ (stock) በሀብትና ዕዳ መግለጫ ላይ ብር 55,122,730 የተመለከተ ሲሆን ስለብዛቱና ዋጋው የሚያረጋግጥ በቂ የኦዲት ማስረጃ አለመገኘቱ፣
- በጉዞ ላይ ያለ የክምችት ዕቃ ሂሳብ ብር 1,033,584 የሚያወጣ ኔጋቲቭ ባላንስ ለምን ሊከሰት እንደቻለና ከመድረሳቸው በፊት ከክምችት ዕቃ ሂሳብ ላይ ለምን ተቀንሶ በሀብትና ዕዳ መግለጫው እንደታየ አለመታወቁ፣
- በግምት ብር 82,000,000 የሚሆን ተከፋይ ሂሳብ በሀብትና ዕዳ መግለጫ የተመለከተና ለረጅም ዓመታት የቆየው ለምን እንዳልተከፈለና እውነተኛ የድርጅቱ ዕዳ መሆኑን ለማረጋገጥ፣ አለመቻሉ፣
- በሀብትና ዕዳ መግለጫው ላይ በረጅም ጊዜ ብድር የታየው ብር 250,321,090 በትክክል ስለመመዝገቡ ማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- ድርጅቱ ህዳር 10 ቀን 1986 ሲመሠረት የተከፈለ ካፒታል ብር 5,522,000 እንደሚሆን የታወጀ ሲሆን የድርጅቱ መዝገብ በዕለቱ ምንም የተጣራ ሀብት የማያሳይ፣ ነገር ግን የተጣራ ዕዳ ብር 134,881,404 እንዳለበት የሚያሳይ በመሆኑ ልዩነቱ ብር 140,403,404 በምን እንደተካካሰ የሚያሳይ ማስረጃ ማግኘት አለመቻሉ፣

- በሀብትና ዕዳ መግለጫ ከታየው ተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ በግምት ለመጠባበቂያ ብር 90,000,000 መያዝ ነበረበት (ምክንያቱም ሂሳቡ የሚፈለግባቸው ድርጅቶች ተዘግቷል ወይም የሚከፍሉት ገንዘብ እንደሌላቸው በመታወቁ)መጠባበቂያ አለመያዙ፣

- በሰኔ 30 1999 የተረጋገጠው የባንክ ሂሳብ ከወጪ ቀሪና ከድርጅቱ መዝገብ መካከል ብር 484,414 ልዩነት እንዲታረቅ አለመደረጉ፣ እንዲሁም በድርጅቱ (Dollar Account) ተመጣጣኝ ብር 4,285,344 ሂሳብ ለምን እንደተያዘ በቂ ማብራሪያ አለመሰጠቱ፣

- በተዘጋጁ የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አስተያየት ለመስጠት አቋም ለመውሰድ ያስቻሏቸው ጉዳዮች መሆኑን ኦዲተሮቹ ገልጸዋል፡፡ መ/ቤታችን የድርጅቱ የሥራ አመራር ቦርድ በጉዳዩ ላይ የወሰደውን እርምጃ ለፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ እንዲገልጽና በግልባጭ እንዲያሳውቀን በተጠየቀው መሠረት በሰጠው ምላሽ ችግሮቹ የረዥም ጊዜ በመሆናቸው በኦዲት ሪፖርቱም በተደጋጋሚ የቀረቡና ችግሮቹ የበላይ ባለሥልጣን ውሳኔ የሚሹ በመሆናቸው ችግሮቹን በተለያዩ ጊዜያት አቅርበው ምላሽ ያላገኙ ናቸው በማለት ገልጸዋል፡፡

4.1.3 <u>የአቦቦ እርሻ ልማት ድርጅት</u>

ሰኔ 30 ቀን 2002 የተጠናቀቀው የድርጅቱ ሂሳብ ኦዲት ተደርጎ የቀረበው የኦዲት አስተያየት እንደሚከተለው ነው፡፡

- በቋሚ ዕቃ የተካተተው ብር 74,768 በግንባታ ላይ ያለ ንብረት ከ10 ዓመት በላይ የቆየና በቂ ማብራሪያ ያልተሰጠው መሆኑ፣

- በክምችት ዕቃ (stock) ከተያዘው ውስጥ ብር 4,123,452 የጠፋ የክምችት ዕቃ (stock loss) ከብዙ ዓመታት በፊት እየዞረ የመጣ ቢሆንም ከመዝገብ ያልተሠረዘ ወይም በቂ ማብራሪያ አለመሰጠቱ፣

- በጉዞ ላይ ያሉ ንብረቶች ብር 578,500 ከ10 ዓመት በላይ የቆየና እስከ ሂሳብ መዝጊያው ዕለት ሳይጣራ ለምን እንደቆየ አለመታወቁ፣
- የክምችት ዕቃዎች ያልተለመደ ሚዛን (credit balance) ብር 23,548 በሚጣራ ሂሳብ (suspense account) ለብዙ ዓመታት የቆየና በተበላሹና ምንም እንቅስቃሴ ለማያሳዩ የክምችት ዕቃዎች መጠባበቂያ አለመያዙ፣
- በሀብትና ዕዳ መግለጫ ከተያው የተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ ከቀድሞ የፈረሱ መንግሥት መ/ቤቶች /ድርጅቶች/ የሚፈለግ ብር 15,389,580 (Dr) እና ብር 828,209 (Cr) ሚዛን የሚየሳይ ለረጅም ዓመታት የቆዩ መሆኑና ከሠራተኞች ተሰብሳቢ ተብሎ ብር 62,069 (Dr) እና ብር 59,873 (Cr) የሚያሳይ ሰራተኞቹ በሕይወት የሌሉ ወይም ድርጅቱን ባልታወቀ ምክንያት ከለቀቁት የሚፈለግ ሂሳብ መሆኑ፣
- በሂሳብ መግለጫው የተመለከተው ጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ሚዛን ብር 105,304 የተገኘው ብር 163,570 ከተቀነሰ በኋላ ሲሆን፣ ይህም ለረጅም ጊዜ የቆየና የሌለ መሆኑ፣
- በባንክ ሂሳብ ሚዛን ከተመለከተው ውስጥ ብር 153,586 ካለፉት ዓመታት እየዞረ የመጣ የባንክ ሂሳብ ልዩነት ሲሆን ስለመኖሩና የድርጅቱን ባለቤትነት የሚያረጋግጥ ማስረጃ አለመቅረቡ፣ እንዲሁም ያልታረቀ የባንክ ሂሳብ ሚዛን ብር 8,891 መኖሩ፣
- በሀብትና ዕዳ መግለጫ ከተመለከተው ተከፋይ ሂሳቦች በድምሩ 18,786,990 በተለያዩ የቀድሞ ተባባሪ ድርጅቶች (Ex-associated enterprises) ለረጅም ዓመታት የቆየ ሂሳብ መሆኑና ብር 1,383,026 እንደ ተሰብሳቢ የሚቆጠር ነገር ግን credit የሂሳብ ሚዛን ያለውና ለረጅም ጊዜ የቆየ መሆኑ፣

- የረዥም ጊዜ ብድር ብር 13,576,764 እና ተከፋይ ወለድ ብር 16,001,663 እንደተከፋይ ዕዳ ያልተቆጠረና ለረጅም ጊዜ እየተንከባለለ የመጣ ሂሳብ በበቂ ማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑ፣

በኦዲት ወቅቱ በመታየታቸው የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አስተያየት ለመስጠት አለመቻላቸውን ኦዲተሮቹ ገልጸዋል፡፡ በመሆኑም መ/ቤታችን የድርጅቱ የሥራ አመራር ቦርድ በጉዳዩ ላይ የተወሰዱትን የእርምት እርምጃ እንዲገለፅልን በደብዳቤ ጠይቆ የተሰጠን መልስ የለም፡፡

4.1.4 <u>የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ድርጅት</u>

ሰኔ 30/2000 የተጠናቀቀው የድርጅቱ ሂሳብ ኦዲት ተደርጐ የቀረበው የኦዲት አስተያየት እንደሚከተለው ነው፡፡

- በጣም ከፍተኛ መጠን ያለው ነገር ግን በዋጋ መግለጽ ያልተቻለ የክምችት ዕቃዎች አገልግሎት ሊሰጡ የማይችሉ መኖራቸውና ለፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ እንዲወገዱ የተጠየቀ ቢሆንም ምንም መጠባበቂያ ያልታዘዘላቸው መሆኑ፣
- በተሰብሳቢነት ከሚታየው ሂሳብ ውስጥ ከሠራተኞችና ከተለያዩ ሌሎች ተሰብሳቢ ሂሳብ በጠቅላላ ብር 3,022,708 ከረጅም ጊዜ ጀምሮ እየዞረ የመጣና ምንም እንቅስቃሴ የሌለው ነው፡፡ በተጨማሪም ብር 156,616 ለዚህ ሂሳብ ላይሰበሰብ ይችላል ተብሎ የተያዘው መጠባበቂያ በቂ አለመሆኑና፣
- በተከፋይ ከተያዘው ሂሳብ ውስጥ ብር 3,773,510 ለተለያዩ ባለገንዘቦች የሚከፈል ተብሎ ላለፉት ዓመታት የዞረና ምንም እንቅስቃሴ የሌለው መሆኑ፣
- በመንግሥት ልማት ድርጅቶች መቋቋሚያ አዋጅ ቁ 25/1992 አንቀጽ 2/1/ መሠረት የድርጅቱ የተፈቀደ ካፒታል በጠቅላላ ድርጅቱ በተቋቋመ በ5 ዓመታት ውስጥ መከፈል እንዳለበት

ተደንግጓል፡፡ ሆኖም የተፈቀደው የድርጅቱ ካፒታል ብር 8,174,000 እስከአሁን ተሟልቶ አልተከፈለም፡፡ ይህም አዋጁ የሚጠይቀውን መሥፈርት አላሟላም፡፡

- ኦዲት የተደረገው በጀት ዓመት ሂሳብ ጨምሮ የድርጅቱ የተጠራቀመ ኪሣራ ሚዛን ብር 4,793,561 መድረሱን ያሳያል፡፡ ይህን አስመልክቶ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች መቋቋሚያ አዋጅ ቁ.25/1984 አንቀጽ 39/4/ የአንድ ድርጅት የተጠራቀመ ኪሣራ የተከፈለውን ካፒታል 75% ያህል በድርጅቱ ከደረሰ ለድርጅቱ መፍረስ ምክንያት እንደሆነ ይደነግጋል፡፡ ስለዚህ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች የድርጅቱን የቀጣይነት ሕልውና (Going concern) መሠረት አድርገው ስለመሆኑ በቂ ማረጋገጫ ማግኘት ያልተቻለ ሲሆን መንግሥት ሌላ ተጨማሪ ገንዘብ ካልደጐመው በስተቀር የድርጅቱ በሥራ የመቀጠል ሕልውና አጠራጣሪ ሆኖ በመገኘቱ፡

ኦዲተሮቹ በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አስተያየት ከመስጠት ተቆጥቧል፡፡ ድርጅቱ ባለፉት ዓመታትም ተመሳሳይ የኦዲት አስተያየት የተሰጠበት ሲሆን ይህንን በተመለከተ መ/ቤታችን ለድርጅቱ የሥራ አመራር ቦርድ በኦዲት ተደራጊዉ በኩል በቀረበው የኦዲት ሪፖርት ላይ የተወሰደውን እርምጃ እንዲገልፅልን ጠይቀን የተሰጠ ምላሽ የለም፡፡ ሆኖም ነሐሴ 5 ቀን 2002 ከፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በተገኘው መረጃ መሠረት ድርጅቱ በሽያጭ ሂደት ላይ መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

4.1.5 <u>የውሃ ጉድጓድ ሥራ ድርጅት</u>

ሰኔ 30 ቀን 2000 የተጠናቀቀው የድርጅቱ ሂሣብ ኦዲት ተደርጎ የቀረበው ኦዲት አስተያየት ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

- በሰኔ 30/2000 የቋሚ ንብረት ቆጠራ ቢደረግም ውጤቱ ከመዝገብ ጋር እንዲመሳከር አልተደረገም፡፡ በተጨማሪም በርካታ ጉዳት

የደረሰባቸውና ሊያገለግሉ የማይችሉ ቋሚ ዕቃዎች በሂሣብ መዝገብ ውስጥ ተካቷል፤

- በክምችት ዕቃዎች 549,624 በብልጫ የታየው በዋጋ መተመኛው በትክክል ያልተመለከተ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 535,557 ከቀጥተኛ ማምረቻ ዕቃዎች ዋጋ ተቀናሽ ተደርጐ የተያዘው ብር 14,067 በጊዜያዊ ሂሣብ (suspense account) በዕዳነት እንዲያዝ ተደርጓል፤
- በተሰብሳቢ ሂሣብ ከሚታየው ውስጥ ብር 22,842,581 ለረዥም ጊዜ ሳይሰበሰብ መጠባበቂያ ብር 2,912,874.43 የተያዘለት ሲሆን ይህም ለበርካታ ዓመታት ሳይለወጥ የቆየ ነው፤
- ከሠራተኞች የሚሰበሰቡ ሂሣብ ውስጥ ብር 760,467.30 ድርጅቱን ከለቀቁ ሠራተኞች የሚፈለግና ሊሰበሰብ ስለመቻሉ አጠራጣሪ መሆኑ፤
- ትክክለኛ ያልሆነው የተሰብሳቢ ሂሣብ (abnormal balance) ብር 3,476,868 (ብር 404,648 ድርጅቱን ለለቀቁ ጥቂት ሠራተኞች የሚከፈል ተብሎ የተያዘ) ትክክለኛነትና አስተማማኝነት በቂ ምክንያት አለመኖሩ፤
- የጥቃቅን ወጪዎች ገንዘብና የግዥ ፈንድ ሂሣብ ብር 855,384 ስለመኖሩ በቆጠራ አለመረጋገጡ፤
- የተጨማሪ እሴት ታክስ ተካፋይ ሂሣብ መዝገብና ለፌዴራል ሀገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን እንደሚከፈል ከተገለፀው ሂሣብ መካከል የብር 1,576,338 ልዩነት መኖሩ፤
- በተከፋይ ሂሣብ ከተመለከተው ሂሣብ ብር 3,166,525.07 ለረዥም ጊዜ ሳይከፈል የቆየና ብር 877,472.96 ትክክለኛ ያልሆነ ባላንስ (Debit) የሚያሳይ መሆኑ፤
- በሌሎች ተከፋይ ሂሣቦች ውስጥ ከተያዘው ሂሣብ የቀረጥ ተከፋይ ሂሣብ ብር 714,478.16 በበቂ ማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑ፤

የሚሉ ናቸው፡፡

ቀደም ሲል በተደረጉት ኦዲቶች ማስተካከያ ዕርምጃዎቹ በ2001 በጀት ዓመት የሚወሰዱ ናቸው በመባሉ ለዚህ ሪፖርት መ/ቤታችን ምላሽ እንዲሰጡ አልጠየቀም፡፡

4.1.6 <u>አዋሣ ጨርቃጨርቅ አ.ማ.</u>

የአክስዮን ማህበሩ ከ 1 July 2008 - 16 September 2008 የሊዝ ኪራይ ሂሣብ ኦዲት ተደርጎ የቀረበው የኦዲት አስተያየት እንደሚከተለው ነው፡፡

- ከውጭ ከታገዘው የማሽነሪና መለዋወጫ ዕቃዎች የሚፈልግ የቀረጥ ሂሣብ ብር 2,358,057 በዕዳነት አልተያዘም ወይም በቋሚ ንብረት ሂሣብ ላይ በተጨማሪ አልተመዘገበም፡፡ ይህ ቀረጥ ቢያዝ ኖሮ ተከፋይ ዕዳ በዚሁ መጠን በመጨመር የንብረት የእርጅና ተቀናሽ ብር 448,000 በወጭ መያዝ ስለሚገባ የተጣራ ኪሳራ በብር 448,000 ይጨምራል፡፡
- በሀብትና ዕዳ መግለጫ የተመለከተው የተጣራ ተሰብሳቢ ሂሣብ 59,879,446 በ22 July 2005 ለተከራይ የተላለፈ ሲሆን ተከራይ ሊጠቀምበት እንደሚችል የኪራይ ውሉ መብት ሰጥቶታል፡፡ ሆኖም በመጨረሻ ያለው ተሰብሳቢ ሂሣብ ብር 21,341,121 ከተከራይ ስለመሰብሰቡ በውሉ ግልጽ የተቀመጠ ማስረጃ እንቀጽ ባለመኖሩ አጠራጣሪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ምክንያቱም በኪራይ ውሉ አንቀጽ 107 መሠረት በሀብትና ዕዳ መግለጫ ላይ የሚታየው በመጨረሻ ሲዘጋና ሲተላለፍ አከራይና ተከራይ ስለዋጋው በግልጽ የተቀመጠ ስላልሆነና የአከራዩን ጥቅም የማያስጠብቅ ሆኖ ተገኝቷል፤

የሊዝ ኪራይ ውሉ ከ 16 September 2008 ጀምሮ የተቋረጠ ስለሆነ ደብዳቤ አልተጻፈም፡፡

4.1.7 ጥቁር አባይ ኮንስትራክሽን አ.ማ

የአክስዮን ማህበሩ ሰኔ 2001 (30 June 2009) የተጠናቀቀው ሂሣብ ኦዲት ተደርጎ በቀረበው ሪፖርት አ.ማ በኪሣራ ውስጥ መሆኑና ኦዲት በተደረገው የሂሣብ ዓመት መጨረሻ የሚታየው የተጠራቀመ ኪሣራ የካፒታሉን 91% መድረሱ ተገልጿል፡፡ ይህም በ1960 በወጣው የኢትዮጵያ ንግድ ሕግ አንቀጽ 495(1-ለ) መሠረት ለድርጅቱ መፍረስ (Dissolution) በቂ እንደሆነ በመጠቀሱ ይኸው ተገልጾ ይህንን ድርጅት በማስመልከት የፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶተ ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በኩል የተወሰደ እርምጃ ካለ በመ/ቤታችን ተጠይቆ በሰጠው መልስ የድርጅቱን ኪሣራ በመቀነስና ለወደፊት አትራፊ ሆኖ ለመንግሥት ተጨማሪ ገቢ ማስገኘት እንዲችል በኤጀንሲውና በድርጅቱ ሥራ አመራር የተለያዩ ጥረቶች ተደርገው እንደነበር፤ በዚህም ማኔጅመንቱና ቦርዱን የማጠናከር ሥራ እየተሠራ መሆኑንና ድርጅቱ ገቢ ሊያስገኝ የሚችለው ሀብት በመጠቀም የተሻለ ገቢ በማግኘት ኪሳራውን እንዲቀንስና በሂደትም ወደ ትርፋማነት የሚሸጋገርበት እድል ካለ አሟጦ በማየት ጥረት እየተደረገ መሆኑ፤ በሌላም በኩል ድርጅቱ በመንግስት ከልማት አቅጣጫ ትኩረት በተሰጠው ዘርፍ ስለሚንቀሳቀስ በመስኩ የሀገር አቅም እንዲጎለብት የሚጠበቅ ከመሆኑ አንፃር ኪሳራውን ብቻ በማየት ወደ መዝጋት ውሳኔ እንዳልተሄደበት ይህም ሆኖ በሂደት ወደ ግል ይዞታ ለማዛዋወር እንቅስቃሴ እንደተጀመረና እነዚህ ሂደቶች ሁሉ ውጤቱ ካልተቀየረ በሂደት የመዘጋት ውሳኔ የሚያርፍበት እንደሚሆን ተገልጿል፡፡

4.2 ስለድርጅቶች የሂሳብ አያያዝና ንብረት አጠባበቅ በተመለከተ

የድርጅቶች አጠቃላይ የሂሳብ አያያዝ፤ ንብረት አጠባበቅና የፋይናንስ አስተዳደርን በተመለከተ በኦዲት ወቅት የታዩ ዋና ዋና ችግሮችና የተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች የሚከተሉት ናቸው፡፡

4.2.1 በመጋዘን ያሉ እቃዎች

- በመጋዘን ያሉ እቃዎች (stock) በሂሳብ ዓመቱ መጨረሻ ላይ ቆጠራ የማያደርጉ ወይም ከፊል ቆጠራ ብቻ ማድረጋቸውና ሌሎች ደግሞ ቆጠራም ቢያካሂዱ የቆጠራው ውጤት ከሂሳብ መዝገቡ ጋር ተገናዝቦ ልዩነት ካለ አስፈላጊውን ማስተካከያ የማያደርጉ መሆኑ፤
- አንዳንድ ድርጅቶች በመጋዘን ያሉ እቃዎች እንቅስቃሴ የሚከታተሉበት መቆጣጠሪያ መዛግብት (stock card) እንደማይዙ ሌሎች ደግሞ አሟልተው የማይመዘግቡና የምዝባ ስህተቶች ልዩነት ሲያጋጥሟቸው ጉዳዩን ሳያጣሩ በተሰብሳቢ ወይም ተከፋይ ሂሳብ ውስጥ የሚይዙ መሆኑ፣
- በብዙ ድርጅቶች ውስጥ በብልሽትና በተለያዩ ምክንያቶች ጥቅም ላይ ሳይውሉ ለረዥም ጊዜ ተከማችተው የቆዩ እቃዎች መኖራቸውና በአንዳንድ ድርጅቶችም እነዚህ እቃዎች በዝርዝር ተመዝግበው ባለመያዛቸው ለእቃዎች መጠባበቂያ ተብሎ በመዝገብ የሚታየው ሂሳብ ትክክለኛነት ለመገመት የማይቻል መሆኑ፣
- ከሀገር ውጭ በሚገዙ እቃዎች እስከሚደርሱ ድረስ በጉዞ ላይ ያሉ እቃዎች በማል ሂሳብ ውስጥ እስከ 6 ወር ያህል ጊዜ ብቻ መዝግቦ መቆየት የሚቻል ቢሆንም በበርካታ ድርጅቶች በጉዞ ላይ የሚገኙ እቃዎች ተብሎ ከሁለትና ከዚያ በላይ ዓመት የሚቆዩና አንዳንዶቹም በሰነድ ያልተደገፉ ሂሳቦች የጠፉ ወይም የተበላሹ እቃዎች ከሆኑ በወቅቱ የመድን ካሳ ያልተጠየ ቀባቸው መሆኑ፣
- በእቃ ግመጃ ቤት ውስጥ ከረዥም ጊዜ በፊት አንዳንዱም በውርስ ጊዜያቸው ጀምሮ በምርት ኦዲት የነበሩ ወይም ለሌላ አገልግሎት ያልዋሉና በየጊዜው ምንም እንቅስቃሴ የማያሳዩ ለረዥም ጊዜ በመቆየታቸው የተነሳ ጥቅም ላይ ወይም በምርት ተግባር ስለማይውሉ እነዚህ ዓይነት ንብረቶች የመጠባበቂያ ሂሳብ እንዲያዝላቸው ወይም ከሂሳብ መዝገብ ውስጥ እንዲቀነሱ የማይዳረግ መሆኑ፣

በኦዲት ወቅት በተደጋጋሚ የተገኙ ናቸው በመሆኑም ድርጅቶቹ በክምችት እቃዎች ላይ የሚያደርጉት ቁጥጥር እንዲጠናከር የታዩት ችግሮች ላይ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወሰድ በየኦዲቱ ሪፖርት ማስገንዘቢያ ተሰጥቷል፡፡

4.2.2 <u>ተሰብሳቢ ሂሳብ</u>

- አብዛኞቹ ድርጅቶች በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ተሰብሳቢ ሂሳቦችን ሳይሰበስቡ ከዓመት ዓመት እንደሚሸጋገሩ ተሰብሳቢው እየበዛና ጊዜው እየረዘመ በሄደ ቁጥር ባለእዳዎችን በውዴት ወይም በሕጋዊ መንገድ ለማስከፈል ችግር መፍጠሩና ድርጅታቸው በውዝፍ ያሉትን ሂሳቦች ገቢ እንዲደረጉለት ተገቢውን ጥረት የማያደርጉ መሆኑ፣
- አንዳንድ ድርጅቶች ተሰብሳቢ ብለው ከያዙት ሂሳብ ውስጥ ከማን መሰብሰብ እንዳለባቸው የማይታወቁ መኖራቸው እንዲሁም ድርጅቶቹ የሂሳብ ግንኙነት አላቸው መንግሥታዊና የግል ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች የተሟላ አድራሻ ባለመያዛቸዉ በኦዲት ወቅት የተመረጡ ድርጅቶችን በዓመቱ መጨረሻ የነበረው ሂሳብ በቀጥታ ከድርጅቶች ለማጣራት /ማረጋገጫ ለማግኘት የሚደረገው ጥረት አልተሳካም፣
- በብዙ ድርጅቶች ለሠራተኞች ብድርና የቅድሚያ ደመወዝ ብድር መስጠት የተለመደ ቢሆንም አንዳንድ ድርጅቶች ስለ አወሳሰዱ አፈ.ቃቀዱና አሰባሰቡ መመሪያ የሌላቸው መመሪያ ያላቸውም ቢሆኑ በትክክል ስለማይተገብሩ ከፍተኛ የመንግሥት ገንዘብ በሠራተኞች ስም በተሰብሳቢ ይታያል፡፡ ከዚህም ሌላ ብድር ያለባቸው ሠራተኞች ከመ/ቤቱ ሲሰናበቱ ወይም ወደሌላ ድርጅት ሲዛወሩ ያለባቸው እዳ እንዲከፍሉ ወይም እንዲጣራ ስለማይደረግ ለረዥም ጊዜ የቆዩ ብድር ሂሳቦች ሲንከባለሉ የሚታዩ መሆኑ፣
- በአንዳንድ ድርጅቶች ለአንድ ባለእዳ ሀብትና ሶስት ወይም ከዚያ በላይ የሂሳብ ቋት ስለሚከፈት የሂሳቦች መመሰቃቀልና አለመስማማትን የሚያስከትል ሆኖ ይታያል

በመሆኑም በተሰብሳቢው ሂሳብ ላይ ቁጥጥር እንዲጠናከር፣ ሊሰበሰቡ የሚችሉ ሂሳቦች በወቅቱ እንዲሰበሰቡ ይህም ካልተቻለ ከሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ አካል ጋር በመመካከር ሂሳቡ እንዲሰረዝ በማድረግ የተሰብሳቢ ሂሳቦች ትክክለኛው የድርጅቱን የተሰብሳቢ ሂሳብ የሚያሳዩ እንዲሆኑ ማድረግ እንደሚገባ በኦዲቱ ሪፖርት አስተያየት ተሰጥቷል፡፡

4.2.3 በባንክና በካዝና ያለ ገንዘብ

- አንዳንድ ድርጅቶች የሚሰበስቡትን ገንዘብ በወቅቱ ባንክ ገቢ የማያደርጉና ከዚህም ገንዘብ ላይ ክፍያዎች እንደሚፈጽሙና በርካታ ድርጅቶች በባንክ ያላቸውን ሂሳብ በየወሩ ከባንክ ሂሳብ ማስታወቂያ ጋር በወቅቱ በማገናዘብ እንደሚያስታርቁ የባንክ መዝገባቸውና የባንክ ሂሳብ ማስታወቂያ መካከል ልዩነት ቢያጋጥም እንኳ የልዩነቱን መንስኤ እንደማያጣሩና አንዳንዶችም ምንም እንቅስቃሴ የሌላቸው የባንክ ሂሳቦች ውስጥ የተቀመጠ ገንዘብ መኖሩ፣
- በርካታ ድርጅቶች በሂሳብ ዘመኑ መጨረሻ ከካዝና የነበረውን ጥሬ ገንዘብ እንደማይቆጥሩ ቢቆጥሩም በዓመቱ መጨረሻ የሚደረገው የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ከመዛግብቱ ጋር በማመሳከር ልዩነቱ ካለ እንደማይጠፋ በኦዲቱ ወቅት ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም ድርጅቶች በባንክ ያለውን ሂሳብ በትክክል ለመቆጣጠር ከባንክ የሚላከውን ወርሃዊ የባንክ ሂሳብ ማስታወቂያና ዓመታዊ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ከሂሳብ መዝገብ ጋር ማስታረቅና ልዩነቶችና ስሕተቶችን እንዲሁም አላግባብ ወጪ የሆኑ ሂሳቦች ሲኖሩ ወዲያውኑ ተከትትሎ አስፈላጊውን እርምጃ እንደወስድ በሚመለከታቸው ድርጅቶች ተገልጾላቸዋል፡፡

4.2.4 ተከፋይ ሂሳቦች

- በርካታ ድርጅቶች ለመንግሥት መከፈል የሚገባቸውን ግዴታዎች ማለትም ከሰራተኞች ደመወዝ የተቀነሰ የሥራ ግብር፣ የጡረታ

ማዋረጮ እንዲሁም የሽያጭና የንግድ ትርፍ የታክስ ሕጉ በሚያዘው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለግብር ሰብሳቢው እንደማይከፍሉ፣

- አንዳንድ ድርጅቶች ተካፋይ ብለው ከያዙት ሂሳብ ውስጥ ረዘም ላለ ጊዜ ሳይከፍሉ የቆዩና ለማን መክፈል እንዳለባቸው የማይታወቁና ለረዥም ጊዜ ሳይከፍሉ የቆዩ የረዥም ጊዜ ብድሮች እንዳለባቸውና ከአበዳሪዎች ጋርም በየጊዜው የሂሳብ ማግለጫዎች ስለማይለዋወጡ በኦዲት ወቅት ከአበዳሪወች /ተከፋይ ድርጅቶች/ ማረጋገጫ በሚጠየቅበት ጊዜ መልስ የማይሰጡ ቢሰጡም ድርጅቶች አለን ከሚሉት ሂሳብ ጋር ከፍተኛ ልዩነት የሚታይ መሆኑ የሂሳቦቹን ትክክለኛነት አጠራጣሪ ያደርገዋል፡፡

በመሆኑም ድርጅቶች የተከፋይ ሂሳቦችን በተመለከተ በየወቅቱ እንዲከፍሉ ትክክለኛነቱንም እንዲያጣሩ በተላከላቸው ሪፖርት ተገልጿል፡፡

4.2.5 ስለሂሳብና የሰነድ አያያዝ

- አንዳንድ ድርጅቶች ውስጥ ቫውቸሮች በሂሣብ ማሠራተኞች ከተዘጋጁ በኋላ ተገቢው የሥራ ኃላፊ ተመልክቶች ትክክለኛነታቸውን መርምሮ ሳያፀድቅ በሂሣብ መዝገብ እንደሚመዘገቡ፣
- በእያንዳንዱ ድርጅቶች ለሂሣብ ሠነዶች ልዩ የሚያደርጉ ቁጥጥር እናሳ መሆኑና በማተሚያ ቤት ቁጥር ተሰጥቶአቸው የሚወጡ ሰነዶች እንቅስቃሴ እየተመዘገበ ቁጥጥር እንደሚደረግና ከክፍያ ሠነዶች ጋር የተያያዙ የወጪ ደጋፊ ደረሰኞች የተወራረዱ መሆናቸው የሚያረጋግጥ ምንም ዓይነት ምስክት እንደማይደረግባቸውና በአንዳንድ ሂሣቦችም የአርዕሰት አመዘጋገብ ስህተት እንደሚታይ ታውቋል፡፡

የዚህ ዓይነት አሠራር የድርጅቶችን ገንዘብ ለብክነት የሚዳርግ የሂሣብ ደነዶችን በሚፈለጉበት ጊዜ በቀላሉ ለማግኘተ በሚቻል መልኩ

በጥንቃቄ እንዲያዙና ቁጥጥረ ሊደረግ እንደማገባ ለሚመለከተው ሪፖርት ተልኳል፡፡

4.2.6 የንብረት አያያዝና አጠባበቅ

- በርካታ ድርጅቶች የቋሚ ንብረት መቆጣጠሪያ መዝገብ የሌላቸው፣ ያላቸውም ቢኖሩ ምዝገባቸው ያልተሟላ አንዳንዶች ደግሞ የተለያዩ ቋሚ ንብረቶችን አንድ ላይ መዝግበው መገኘታቸው፣
- አንዳንድ ድርጅቶች የቋሚ ንብረት መዝገብ ቢይዙም የግዥ፣ ሽያጭንና ዝውውርን በተመለከተ የተሟላ መረጃ ካለመመዝገባቸው የተነሳ መዝገብ ውስጥ ያለው የዋጋና የአገልግሎት ቅናሽ ሂሳብ በዋናው መዝገብ ጋር በየወቅቱ ባለመመሳከሩ በሁለቱ መዝገቦች መካከል ልዩነቶች እንደሚያጋጥሙ፣
- በመዝገብ የተዘረዘሩት ንብረቶች በእውን መኖራቸውንና ተገቢው እንክብካቤ የሚደረግላቸው ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የሚያስችል የቋሚ ንብረት ቆጠራ እንደማይደረግና የተደረገም ከሆነ ከመዝገቡ ጋር የማይገናዘብ ልዩነትም ከተገኘም እንዲታረቅ የማይደረግ መሆኑ፣
- በውርስና በተለያዩ መንገድ ቋሚ ንብረቶች ከአንድ ድርጅት ወደ ሌላ ሲዛወሩ በተገቢው መንገድ ርክክብ የማይካሄድና በሰነድ ያልተደገፈ በመሆኑ ምክንያት ቋሚ ንብረቶች በተረካቢውም ሆነ በአስረካቢው ድርጅት የሂሳብ መዝገብ ውስጥ በትክክል የማይመዘገቡ መሆኑ፣
- አንዳንድ ድርጅቶች ለቋሚ ንብረቶቻቸው የገዙት የመድን ዋስትና በቂ ያልሆነና በአደጋ ጊዜ ሊደርስ የሚችለውን ጥቶት ሙሉ በሙሉ ሊሸፍን የማይችል ሲሆን ሌሎች ደግሞ ለንብረቶቻቸው የመድን ዋስትና ያልገቡ መሆኑ፣
- አንዳንድ ድርጅቶች የንብረት መጥፋት የተከሰተ መሆኑ ለመረዳት ቢቻልም ንብረቱ የጠፋበት ምክንያት ተጣርቶ እንዲተካ እንደማይደረግ በኦዲት ወቅት ታይቷል፡፡

በመሆኑም ድርጅቶቹ በንብረት ላይ ተገቢውን ቁጥጥር እንዲያደርጉና የንብረት ሂሳባቸው ትክክለኛውን ሂሳብ ለማንጸባረቅ እንዲቻል አስፈላጊውን ሁሉ እንዲደረግ በየኦዲት ሪፖርቱ ማሳሰቢያ ተሰጥቷል፡፡

4.3 የችግሮቹ ምክንያቶችና መፍትሄያቸው

4.3.1 የችግሮቹ ምክንያቶች

በሂሣብ አያያዝና ቁጥጥር ረገድ በሚታዩት ችግሮች ምክንያት ከሆኑት ዋና ዋናዎቹ የሚከቱሉት ናቸው፡፡

- የሰራተኞች በስራቸው ወቅት አስፈላግውን ጥንቃቄ አለማድረግ እና ቸልኝነት፤
- የተዘረገውን የውስጥ ቁጥጥርን አለማክበርና አለማስከበር፤ ለተከሰቱ ችግሮች ወቅታዊ ምላሽ አለመስጠት፤
- የድርጅቶቹ የበላይ ኃላፊዎችና ተቆጣጣሪ መ/ቤቶች በውጭ ኦዲተሮች የሚሰጡ የእርምትና የማሻሻያ ሃሣቦች ላይ ተገቢውን እርምጃ አለመውሰድ ናቸው፡፡

4.3.2 ችግሮቹን ለማቃለል ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃች

- የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት በማንኛውም ድርጅት መዋቅርና የአሠራር ፕላን ውስጥ መዘርጋት ያለበት ሲሆን፣ የድርጅቱ ገንዘብና ንብረት ላይ ሊደርስ የሚችለውን ማንኛውንም የምዝበራና ብኩንነት ሁኔታ ከምንጩ መከልከል እንድያስችል ተግባራዊ ማድረግ፤
- የድርጅቶች የሂሣብ መዛግብትና ሠነዶችና መረጃዎች አስተማማኝ መሆናቸውን ለማረጋገጥ፣
- የሥራ ቅልጥፍናና ጥራት እንዲኖር ጠንካራ የውስጥ ኦዲት እንድኖር ለማድረግ፣
- ማኔጅመንቱ የሚያውቃቸውና ከበላይ አካል የሚወጡ መመሪያዎች ሁሉ ተግባራዊ መሆናቸውን ማረጋገጥ እና

- በውስጥም ሆነ ከውጪ ኦዲተሮች የሚሰጡ ማሻሻያ ሃሣቦችን ተግባራዊ ማድረግና ተቆጣጣሪ መ/ቤቶችም አስፈላጊውን ክትትል ሊያደርጉ ይገባል፡፡

5. <u>ማጠቃለያ</u>

የሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን በአሁኑ ጊዜ ባለበት የሠለጠነ የሰው ኃይል እጥረት አኳያ የተለያዩ ድርጅቶች በየበጀት ዓመቱ መጨረሻ የሚያዘጋጁትን የሂሣብ መግለጫዎች የመመርመር አገልግሎት ብቻ በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡

ሆኖም አሁን ኮርፖሬሽኑ ያለበት የሠለጠነ የሰው ኃይል እጥረት ከተቃለለና ያሉትንም ሠራተኞች የማሠልጠን ተግባር በተከታታይ ከተከናወነ በተጨማሪ የአሠራር ጥራት (Perforamace Audit) የሂሣብ ማጣራት (Liquidation) የልዩ ኦዲት (Investigation) አገልግሎት በስፋት ለመሥራት እና ሌሎችም ተዛማጅ አገልግሎቶችን መስጠት የሚችል ይሆናል፡፡

ስለዚህ በዚህ በኩል ኮርፖሬሽኑ ያለበትን ችግር ለማስወገድ ይቻል ዘንድ በመንግሥት በኩል በተለይም በማያቋርጥ ሥልጠና በኩል አስፈላጊው ድጋፍና ትብብር ቢደረግ ውጤቱ የበለጠ ሊሆን እንደሚችል ይታመናል፡፡